# ሒስኑል - ሙስሊም
## (የሙስሊሞች ምሽግ)
### አዝካር ከቁርአንና ሐዲስ

ጥንቅር

ሰዒድ ኢብን ዓሊ ኢብን ወሀፍ
አል-ቀሕጧኒ

ተርጓሚና አሳታሚ

ሒላል ሊሚትድ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

እንደገና የመረመረው ፡
ዐብደላህ ኸድር
ኢማም ዩኒቨርሲቲ (ፒ.ኤች.ዲ) ሪያድ

---

هذا الكتاب باللغة الأمهرية

---

# حصن المسلم
## من أذكار الكتاب والسنة

تأليف الفقير إلى الله تعالى

سعيد بن علي بن وهف القحطاني

مراجعة : عبدالله خضر بن أحمد

دار الخير للكتب الإسلامية المترجمة جدة: ٦٨٧٠٦٧٩
DAR AL-KHAIR - JEDDAH: 6870679

# ሒስኑል - ሙስሊም
(የሙስሊሞች ምሽግ)

የአማርኛው ትርጉም መብት በሕግ የተጠበቀ
ነው፤ አሳትሞ በነፃ ለማከፋፈል በጽሑፍ
ፍቃድ የሚያገኙ ሲቀሩ።

All rights reserved

# حصن المسلم

## من أذكار الكتاب والسنة

# ሒስኑል - ሙስሊም
# (የሙስሊሞች ምሽግ)

## አዝካር ከቁርአንና ሐዲስ


<u>ጥንቅር</u>

ሰዒድ ኢብን ዓሊ ኢብን ወህፍ
አል-ቀሕጧኒ



<u>ተርጓሚና አሳታሚ</u>

ሒላል ሊሚትድ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

እንደገና የመረመረው :
ዐብደላህ ኸድር
ኢማም ዩኒቨርሲቲ (ፒ.ኤች.ዲ) ሪያድ

بسم الله الرحمن الرحيم

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ
መቅደም.......................................................15
መግቢያ.......................................................17
የዚክር ትሩፋቶች...........................................19
1. ከእንቅልፍ ሲነቁ የሚሏቸው ዚክሮች...28
2. ልብስዎን ሲለብሱ የሚሉት ዱዓ..........36
3. አዲስ ልብስ ሲለብሱ የሚሉት ዱዓ......37
4. አዲስ ልብስ ለለበሰ ሰው የሚሉትዱዓ..38
5. ልብስዎን ሲያወልቁ የሚሉት ዱዓ.......39
6. ወደ ሽንት ቤት ሲገቡ... .......................39
7. ከሽንት ቤት ሲወጡ የሚሉት................40
8. ከውዱእ በፊት የሚባሉ ዚክሮች...........40
9. ውዱእ ካጠናቀቁ በኋላ .........................40
10. ከቤት ሲወጡ .......................................42
11. ወደ ቤት ሲገቡ ....................................43
12. ወደ መስጊድ ሲጓዙ..............................43
13. ወደ መስጊድ ሲገቡ ..............................46
14. ከመስጊድ ሲወጡ..................................48
15. የአዛን ዚክሮች.......................................48
16. የሶላት መግቢያ ዱዓ..............................51
17. ሩኩዕ ላይ የሚደረግ ዱዓ......................62
18. ከሩኩዕ ሲነሱ........................................64
19. ሱጁድ ላይ የሚደረግ ዱዓ....................66

20. በሱጁድ መካከል የሚደረግ ዱ..............70
21. በሱጁድ ቲላዋህ ወቅት የሚደረግ ዱዓ..70
22. ተሸሁድ ......................................................72
23. ከተሸሁድ በኋላ ሶለዋት ማለት..............73
24. ከመጨረሻው ተሸሁድ በኋላ ሶላት
ከመጠናቀቁ በፊት የሚደረግ ዱዓ.........75
25. ሶላት ከተጠናቀቀ በኋላ የሚባል ዚክር..86
26. የ"ሶላተል ኢስቲኻራ"
(የምርጫ ሶላት ዱዓ)...............................95
27. የጧትና የማታ ዚክሮች..........................98
28. ከመኝታ በፊት የሚባሉ ዚክሮች.........118
29. ሌሊት ነቅተው የመኝታአቅጣጫዎን
ሲቀይሩ የሚሉት ዱዓ........................132
30. ሌሊት በድንገት(በድንጋጤ) ሲባንኑ ወይም
ብቸኝነት ሲሰማዎ የሚሉት ዱዓ.......133
31. ሕልምና ቅብዥር ሲመለከቱ፡ የሚሉት
ዱዓ ...................................................... 134
32. የዊትር ቁኑት ዱዓ .......................... 134
33. ዊትርን ካጠናቀቁ በኋላ የሚባል
ዚክር ................................................. 138
34. በትካዜና በሐዘን ወቅት የሚባል
ዱዓ ..................................................... 138
35. የጭንቅ ጊዜ ዱዓ ............................ 141
36. ከጠላት ወይም(ከጨካኝ) ባለሥልጣን
ጋር ሲገናኙ የሚሉት ዱዓ..................143
37. የባለሥልጣናትን ግፍ የፈራ ሰው

የሚያደርገው ዱዓ ...............................144
38. በጠላት ላይ ዱዓ ማድረግ...................147
39. ሰዎችን የፈራ ሰው የሚለው ዱዓ......148
40. እምነቱ ላይ ጥርጣሬ ያደረበት ሰው
የሚያደርገው ዱዓ...............................148
41. ዕዳ ያለበት ሰው የሚያደርገው ዱዓ...149
42. ሶላት ውስጥ ወይም ቁርአን ሲያነብ
የሸይጧን ጉትጎታ ያጋጠመው ሰው
ማለት ያለበት ዱዓ.............................150
43. አንዳች አስቸጋሪ ነገር የገጠመው
ሰው ........................................................151
44. ወንጀል የፈፀመ ሰው ማድረግ
ያለበት......................................................151
45. ሸይጧንን ለማባረርና ጉትጎታውን
ለመቋቋም የሚደረግ ዱዓ.....................152
46. የማይፈልጉት ወይም ከአቅምዎ በላይ
የሆነ ነገር ሲከሰት የሚሉት ዱዓ........152
47. ልጅ ለወለደ ሰው ብሥራትና ምላሹ...153
48. ለህፃናት የሚደረግ ዱዓ .....................154
49. በሽተኛን በሚጠይቁበት ወቅት የሚሉት
ዱዓ...................................................... 155
50. በሽተኛን የመጠየቅ ትሩፋት.................155
51. ለመዳን ተስፋ የሌለው በሽተኛ
የሚያደርገው ዱዓ ............................ 156
52. ጣእረሞት ላይ ያለን ሰው መምራት...158
53. ችግር የገጠመው ሰው የሚለው

ዱዓ ................................................ 158
54. የሞተን ሰው ዓይን ሲከድኑ የሚሉት
ዱዓ ................................................ 159
55. ሶላተል ጀናዛ ላይ ለሟች የሚደረግ
ዱዓ ................................................ 160
56. ለአቅመ አዳም ሳልደረሱ ህፃናት የሚደረግ
የሶላተል ጀናዛ ዱዓ.......................... 165
57. የሐዘን መግለጫ ዱዓ .................... 167
58. ሟችን ቀብር ውስጥ ሲያስገቡ የሚሉት
ዱዓ ................................................ 168
59. ሟች ከተቀበረ በኋላ የሚባል ዱዓ.... 169
60. በቀብር ጉብኝት ወቅት የሚባል ዱዓ..169
61. ነፋስ ሲነፍስ የሚደረግ ዱዓ............ 176
62. በጉርምርምታ ወቅት የሚደረግ ዱዓ...171
63. ዝናብ በሚጠፋበት ወቅት የሚባል
ዱዓ................................................. 172
64. ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት የሚደረግ
ዱዓ ................................................ 174
65. ዝናብ ከዘነበ በኋላ የሚባል ዚክር.......174
66. ዝናብ ሲበዛ የሚደረግ ዱዓ ...............174
67. ጨረቃን ሲያዩ የሚሉት ዱዓ............175
68. ጾመኛ ሲያፈጥር የሚለው ዱዓ..........176
69. ከምግብ በፊት የሚባል ዱዓ................177
70. ምግብ ሲያጠናቅቁ የሚባል ዱዓ.........178
71. እንግዳ ለጋበዙ የሚያደርገው ዱዓ.....179

72. ውሃ ላጠጣም ሰው ወይም ውሃ ሲከጅሉ የሚያሰሙት ዱዓ..............................180
73. ጾመኛ ከሌላ ሰው ቤት ሲያፈጥር የሚያሰማው ዱዓ ..............................180
74. ጾመኛ ምግብ ቀርቦለት ካላፈጠረ የሚያደርገው ዱዓ ..............................181
75. አንድ ጾመኛ በሚሰደብበት ወቅት ማለት ያለበት ..............................................181
76. የፍራፍሬ እሸት በሚመለከቱበት ወቅት የሚያሰሙት ዱዓ..............................182
77. ያነጠሰ ሰው የሚለው ዱዓ..................182
78. አንድ ካፊር አላህን ካመሰገነ የሚሰጠው ምላሽ ...............................................183
79. ላገባ ሰው የሚደረግ ዱዓ ..................184
80. ያገባ ወይም እንስሳት የገዛ ሰው የሚያደርገው ዱዓ ..............................184
81. ከወሲባዊ ተራክቦ በፊት የሚደረግ ዱዓ.........................................................185
82. በቁጣ ወቅት የሚደረግ ዱዓ................186
83. የተሞከረ(ወንጀል ላይ የወደቀ) ሰው በሚያዩበት ወቅት የሚሉትዱዓ ........186
84. ስብሰባ(መጅሊስ) ላይ የሚባል ዱዓ....187
85. ከስብሰባ ሲነሱ የሚሉት ዚክር.......... 187
86. "አላህ ምህረቱን ይለግስህ" ላልዎት ሰው የሚሰጡት ምላሽ.............................. 188
87. መልካም ውለታ ለዋለልዎት የሚሉት

ዱዓ ........................................................ 188
88. አላህ ከደጃል የሚጠብቅባቸው ዚክሮች ........................................ 189
89. "ለአላህ ብዬ እወድሀለሁ" ላልዎት የሚያደርጉት ዱዓ ........................... 189
90. ገንዘብ ለለገስዎ ሰው የሚያደርጉት ዱዓ........................................ 190
91. የተበደረ ሰው ገንዘብ ሲመልስ አበዳሪው የሚያደርግለት ዱዓ.......... 190
92. ሽርክ ሲያስጋዎ የሚሉት ዱዓ.......... 191
93. "አላህ ረድዔቱን ይለግስህ" ላልዎ ሰው የሚያደርጉት ዱዓ.............................. 191
94. በገድ ያለማመንን ለማመልከት የሚባል ዚክር ........................................ 192
95. መጓጓዣ ላይ ሲወጡ የሚሉት ዱዓ. 192
96. ለጉዞ ሲወጡ የሚያደርጉት ዱዓ....... 194
97. ወደ አንድ ሰፈር ወይም ከተማ ሲገቡ የሚይደርጉት ዱዓ ............................196
98. ወደ አንድ የገበያ ቦታ ሲገበ የሚሉት ዱዓ ........................................ 198
99. መጓጓዣዎ ሲደክም የሚያደርጉት ዱዓ........................................ 199
100. መንገደኛ ለቤተሰቦቹ ወይም ለሚኖርበት አገር ሰዎች የሚያደርገው ዱዓ ............. 199
101. መንገደኛ ያልሆነ(ሙቂም) ለመንገደኛ (ሙሳፊር) የሚያደርገው ዱዓ.............200

102.በጉዞ ላይ"ተስቢህ" እና "ተክቢር"
ማድረግ ..............................................201
103.አንድ ሰው ጧት ለጉዞ ሲወጣ የሚለው
ዱዓ ......................................................201
104.በጉዞ መካከል ለእረፍት ቆይታ
በሚያደርጉበት ቦታ የሚሉት..............202
105.ከጉዞ ሲመለሱ የሚሉት .....................202
106.የሚያስደስተው ወይም የሚጠላው ነገር
የገጠመው ሰው የሚለው ዱዓ...........204
107.በነቢዩ(ሲ.ዐ.ወ) ላይ ሰላምታ የማውረድ
ትሩፋት ...............................................205
108.ሰላምታን ማብዛት ..............................206
109.ካፊር ሰላምታ በሚያቀርብበት ወቅት
የሚሰጡት ምላሽ.................................207
110.አውራ ዶሮ ሲጮህና አህይ ሲያናፋ
የሚያደርጉት ዱዓዎች .......................207
111.ውሾች በሌሊት በሚጮሁበት ወቅት
የሚደረግ ዱዓ ...................................207
112.ለሰደቡት ሰው የሚያደርጉት ዱዓ.......208
113.ሙስሊሞች ሙስሊምን በሚያወድሱበት
ወቅት የሚሉት ..................................208
114.አንድ ሙስሊም ሲወደስ ማለት
ያለበት ................................................ 209
115.ከሐጅ ወይም ዑምራህ ሥርዓት ውስጥ
ያለ ሰው የሚያሰማው ዚክር
/ተልቢያህ/ ......................................... 210

116. "ሩክነል አስወድ" ሲደርሱ የሚሉት ዚክር ............................................. 210
117.በ"ሩክነል የማኒ" እና በ"ሐጀረል አስወድ" መካከል የሚባል.............................. 211
118.ሶፋና መርዋህ ላይ ሲቆሙ የሚያደርጉት ዱዓ........................................................ 211
119.በዐረፋ ቀን የሚደረግ ዱዓ................ 213
120.የ"መሽዐረል ሐራም" ዕለት የሚባል ዚክር................................................ 214
121.በጭንጫ ውርወራ ሥርዓት ወቅት "ተክቢራ" ማድረግ ............................ 214
122.አንድ የሚያስደንቅ ወይም የሚያስደስት ነገር ሲገጥምዎ የሚሉት.................. 215
123.አስደሳች ዜና የሰማ ሰው የሚለው.... 216
124.ከአካሉ ላይ ህመም የተሰማው ሰው የሚለው ዱዓ........................................216
125.በዓይኑ ጉዳት እንዳይደርስ የሰጋ ሰው የሚለው ዱዓ........................................ 217
126.በድንጋጤ ወቅት የሚባል ዚክር..........217
127.እንስሳትን በሚያርዱበት ወቅት ማለት ያለብዎ.................................................. 218
128.የሸይጧንን ተንኮል ለመመከት የሚደረግ ዱዓ ........................................................ 218
129.አላህን ምህረት መማፀን(እስቲግፋር) እና በፀፀት ወደርሱ መመለስ (ተውባህ) ... 220
130.የ"ተስቢሀ"፣ "ተሕሚድ"፣ እና "ተክቢር"

ትሩፋቶች .............................................. 222
131.የነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) የተስቢህ አደራረግ
ስልት .................................................228
132.አጠቃላይ የሆነ ሥርዓት. ....................229

በአላህ ስም፣ እጅግ በጣም ሩህሩህ
በጣም አዛኝ በሆነው።

## መቅድም

የሰው ልጅ ቀልቡ ይቆሽሻል፤ ይዝ ጋል፤ አለመረጋጋት ይገጥመዋል፤ ስክነት ይጐድለዋል አላህ(ሱ.ወ) ከእንዲህ ዓይነቱ በሽታ የምንፈወስበትን ስልት መርቶናል። «ዚክር»/አላህን ማውሳትና ማወደስ/ መረ ጋጋት ለመጐናፀፍና ቀልብን ከቆሻሻ ለማጽዳት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ነግሮናል። እናም«ዚክር» የቀልብ ዝገትን ያስወግዳል፣ ስሜትን ያድሳል፣ ስክነትን ይለግሳል። ለሙስሊሞች እጅግ ጠቃሚ መሣሪያ ነው። «ዚክር» ካለው ጠቀሜታ አንፃር የሐገራችን ሙስሊም ህብረተሰብ በሚገባው ቋንቋ የተዘጋጀ የ«ዚክር» መጽሐፍ እንደሚያስፈልገው አመንበት። እናም «ሒስኑል ሙስሊም» በሚል ርዕስ በ «ሰዒድ ኢብን ዓሊ ኢብን ወሀፍ አል-

ቀህጧኒ» ከቁርዓንና ከሐዲስ ተውጣጥቶ የተዘጋጀውን የ«ዚክር» መጽሐፍ ወደ አመርኛ መልሰናል:: ትርጉምን በተመ ለከተ የተጠቀምነው የአተረጓጐም ስልተ የቃልበቃል ትርጉም ቢሆንም አንዳንድ የአተረጓጐም ስልት መልዕክታቸውን በትክክል አይገልፁም ካልናቸው ስፍራ ዎች ላይ ደግሞ የነፃ ትርጉምን ሥርዓት ተከትለናል:: ኢስላምንና ሙስሊምን ለማገልገል ካለን ቅን ፍላጐት አንፃር ይህን ከባድ ሃላፊነት ወስደናል:: ሥራችን ከግድፈት የፀዳ ነው የሚል እምነት የለንም ስህተቶች ፈፅመን ሊሆን ይችላ ል:: እናም ስህተታችንን ይጠቁሙን ዘንድ በአላህ ስም አንባብያንን እንማፀናለን:: ወደፊት የምናቀርባቸውን ሥራዎች በተሻለ ጥራት ለመሥራት ይረዳናልና::

አላህ ምስጋና ይገባው ለዓለማት ጌታ:: በነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ)፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው፣ እንዲሁም ፈለጋቸውን በተከተሉ ሁሉ ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈን::

ሒሳዐ ሲሚትድ

## መግቢያ

ምስጋና የሚገባው ለአላህ ነው:: እናመሰግነዋለን:: እርዳታውን እንጠይ ቃለን:: ምህረቱን እንማፀናለን:: ነፍሳችን ከምታመጣብን ተንኮልና ከምግባረ ብልሹነት በርሱ እንጠበቃለን:: አላህ ያቀናውን የሚያጠመው እርሱ ያጠመ መውን ደግሞ የሚያቀናው የለም:: ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክ ራለሁ:: አንድ ነው:: አጋር የለውም:: ሙሐመድ ባሪያውና መልዕክተኛው መሆ ናቸውንም እናዘዛለሁ:: በርሳቸውና በቤተ ሰቦቻቸው+ እንዲሁም በባልደረቦቻቸው እና እስከ ዕለተ ቂያማ ድረስ ፈለጋቸውን በተከተሉ ሁሉ ላይ የአላህ እዝ ነት፣በረከትና ሰላም ይስፈን::

ይህችን አነስተኛ መፅሐፍ ያዘጋ ጀኋት «አዝዚከሩ ወዱዓእ ወል ዒላጀ ቢሩቃ ሚነል ኪታቢ ወሱና» ከተሰኘው መፅሐፍ ውስጥ የ«ዚክር» (መወደስ) ክፍሉን ብቻ በመውሰድ ነው:: መንገ ደኞች በቀላሉ ይዘውት መጓዝ እንዲችሉ ያመች ዘንድ እጥር ምጥን ብላ ተዘጋ ጅታለች::

ያስፈርኳቸውን ሐዲሶች ፍሬ ሐሳቦችና አንድ ወይም ሁለት ዘጋቢዎቻቸውን ብቻ በመግለፅ ተወስኛለሁ:: የሐዲሶቹን የመልዕክት ሰንሰለት ወይም ተጨማሪ ዘገባዎችን ማዎቅ የሚሹ ኦሪጅናል መፅሐፉን እንዲመለከቱ ይጋበዛሉ:: ሥራዬን ከርሱ ዘንድ ተቀባይነት ያለው፣ በህይወት እያለሁም ሆነ ከሞት በኋላ ጠቃሚዬ፣ እንባብያንን፣ ያሳተሙና ያተሙ ከፍሎችንም የሚጠቅም ያደርግልኝ ዘንድ አላህን በመልካም ስሞቹና ባህሪያቶቹ እማፀነዋለሁ:: ይህን ማድረግ የማይሳነው አምላክ ነውና:: በነቢዩ መሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው፣ እንዲሁም እስከ ዕለተ ቂያማ ድረስ ፈለጋቸውን በተከተሉ ሁሉ ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈን::

ደራሲው

ወርሃ-ሶፈር 1409 ሒጅሪያ

## የዚክር ትሩፋቶች

ከቁርአን:- ﴿ فَٱذْكُرُونِىٓ أَذْكُرْكُمْ وَٱشْكُرُوا۟ لِى وَلَا تَكْفُرُونِ ﴾

«አስታውሱኝ፣ አስታውሳችኋለሁና:: ለኔም አመስግኑ:: አትካዱኝም::» (አል-በቀራህ ፥152)

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱذْكُرُوا۟ ٱللَّهَ ذِكْرًا كَثِيرًا ﴾

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ብዙ ማውሳትን አውሱት::» (አል-አሕዛብ ፥41)

﴿ وَٱلذَّٰكِرِينَ ٱللَّهَ كَثِيرًا وَٱلذَّٰكِرَٰتِ أَعَدَّ ٱللَّهُ لَهُم مَّغْفِرَةً وَأَجْرًا عَظِيمًا ﴾

«አላህን በብዙ አውሺዎች ወንዶችና አውሺዎች ሴቶችም አላህ ለነርሱ ምህረትንና ታላቅ ምንዳን አዘጋጅቶላቸዋል::» (አል-አሕዛብ ፥35)

﴿ وَٱذْكُر رَّبَّكَ فِى نَفْسِكَ تَضَرُّعًا وَخِيفَةً وَدُونَ ٱلْجَهْرِ مِنَ ٱلْقَوْلِ بِٱلْغُدُوِّ وَٱلْءَاصَالِ وَلَا تَكُن مِّنَ ٱلْغَٰفِلِينَ ﴾

«ጌታህንም በምስጢር ተዋድቀህና ፈርተህ ከጩኸት በታችም በኾነ ቃል ፥ በጧትም በማታም አውሳው:: ከዘንጊ ዎቹም አትሁን::» (አል-አዕራፍ ፥205)

ከሐዲስ:-

وَقَالَ ﷺ : «مَثَلُ الَّذِي يذْكُرُ رَبَّهُ وَالَّذِي لَا يَذْكُرُ رَبَّهُ مَثَلُ الْحَيِّ وَالْمَيِّتِ»

«አላህን የሚያወሳ በህያው፥ የማያወሳ ደግሞ በሙት ይመሰላሉ::» (ቡኻሪ ሙስሊም)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) :-

«أَلاَ أُنَبِّئُكُمْ بِخَيْرِ أَعْمَالِكُمْ، وَأَزْكَاهَا عِنْدَ مَلِيكِكُمْ، وَأَرْفَعِهَا فِي دَرَجَاتِكُمْ، وَخَيْرٍ لَكُمْ مِنْ إِنْفَاقِ الذَّهَبِ وَالْوَرِقِ، وَخَيْرٍ لَكُمْ مِنْ أَنْ تَلْقَوْا عَدُوَّكُمْ فَتَضْرِبُوا أَعْنَاقَهُمْ وَيَضْرِبُوا أَعْنَاقَكُمْ؟»

قَالُوا بَلَىٰ. قَالَ: «ذِكْرُ اللهِ تَعَالَىٰ»

«ከሥራችሁ ሁሉ በላጭ የሆነ፣ ወርቅና ብር ከምትለግሱ የተሻለ ምንዳ የሚያስገኝላችሁና ከጠላት ጋር ተገናኝታችሁ አንገታችሁን ከመሞሻለቅ የበለጠ ሥራ ልጠቁማችሁን?» በማለት ጠየቁ:: «አዎ» አሏቸው::

«አላህን ማውሳት» በማለት መለሱ:: (ቲርሙዝይና ኢብን ማጀህ)

وَقَالَ ﷺ : «يَقُولُ اللهُ تَعَالَىٰ : أَنَا عِنْدَ ظَنِّ عَبْدِي بِي ، وَأَنَا مَعَهُ إِذَا ذَكَرَنِي ، فَإِنْ ذَكَرَنِي فِي نَفْسِهِ ذَكَرْتُهُ فِي نَفْسِي ، وَإِنْ ذَكَرَنِي فِي مَلأٍ ذَكَرْتُهُ فِي مَلأٍ خَيْرٍ مِنْهُمْ ، وَإِنْ تَقَرَّبَ إِلَيَّ شِبْراً تَقَرَّبْتُ إِلَيْهِ ذِرَاعاً ، وَإِنْ تَقَرَّبَ إِلَيَّ ذِرَاعاً تَقَرَّبْتُ إِلَيْهِ بَاعاً ، وَإِنْ أَتَانِي يَمْشِي أَتَيْتُهُ هَرْوَلَةً»

«አላህ እንዲህ ብሏል:- እኔ ባሪያዬ በጠበቀኝ ሁኔታ እገኛለሁ:: ሲያስታውሰኝ ከርሱ ጋር ነኝ:: ብቻውን ሆኖ ካወሳኝ ብቻዬን ሆኜ አወሳዋለሁ:: ከሌሎች ጋር ሆኖ ካወሳኝ ደግሞ እኔም ከሌሎች ጋር ሆኜ አወሳዋለሁ! አንድ ስንዝር ወደኔ ሲቀርብ አንድ ክንድ ወደርሱ እቀርባለሁ:: አንድ ክንድ ወደኔ ሲቀርብ አንድ እርምጃ

ወደርሱ እቀርባለሁ:: ወደኔ በዝግታ ከተራመደ እኔም ወደ ርሱ በፍጥነት እገሰግሳለሁ::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

አብደላህ ኢብን ቡስር እንዳስተላለፉት አንድ ሰው ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) :-

: يَارَسُولَ اللهِ إِنَّ شَرَائِعَ الإِسْلَامِ قَدْ كَثُرَتْ عَلَيَّ فَأَخْبِرْنِي بِشَيْءٍ أَتَشَبَّثُ بِهِ قَالَ: «لَا يَزَالُ لِسَانُكَ رَطْباً مِنْ ذِكْرِ اللهِ»

«የኢስላማዊው ሸሪዓ ድንጋጌዎች በርከተውብኛል:: ሁልዬም አዘውትሬ የምይዛቸውን ነገሮች ያስትምሩኝ» አሳቸው:: «ምላስህ አሳህን ከማውሳት አይበዝን» አሉት:: (ቲርሙ ዝይና ኢብን ማጀህ)

ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

وَقَالَ ﷺ : «مَنْ قَرَأَ حَرْفاً مِنْ

كتَابِ اللهِ فَلَهُ بِهِ حَسَنَةٌ، وَالْحَسَنَةُ بِعَشْرِ أَمْثَالِهَا، لَا أَقُولُ: ﴿الٓمٓ﴾ حَرْفٌ؛ وَلَـٰكِنْ: أَلِفٌ حَرْفٌ، وَلَامٌ حَرْفٌ، وَمِيمٌ حَرْفٌ»

«ከአላህ ኪታብ አንድ ፊደል (ሆሄ) ያነበብ አንድ የመልካም ሥራ ምንዳ (ሐሰና) ያገኛል:: አንዱ «ሃሰና» በአሥር ሊባዛለትም ይችላል:: «አሊፍ ላም ሚም» አንድ ሆሄ ነው፥ አልልም:: «አሊፍ» አንድ ሆሄ ነው:: «ላም» አንድ ሆሄ ነው:: «ሚም» አንድ ሆሄ ነው::»(ቲርሙዝይ)

ዑቅበት ኢብን ዓሚር እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

ሱፍፋህ ውስጥ ነበርን:: የአላህ መልዕክተኛ እኛ ወዳለንበት በመምጣት:-

خَرَجَ رَسُولُ اللهِ ﷺ :

وَنَحْنُ فِي الصُّفَّةِ «أَيُّكُمْ يُحِبُّ أَنْ

يَغْدُوَ كُلَّ يَوْمٍ إِلَىٰ بُطْحَانَ أَوْ إِلَىٰ الْعَقِيقِ فَيَأْتِيَ مِنْهُ بِنَاقَتَيْنِ كَوْمَاوَيْنِ فِي غَيْرِ إِثْمٍ وَلاَ قَطِيعَةِ رَحِمٍ؟ » فَقُلْنَا : يَارَسُولَ اللهِ نُحِبُّ ذٰلِكَ . قَالَ : «أَفَلاَ يَغْدُو أَحَدُكُمْ إِلَىٰ الْمَسْجِدِ فَيَعْلَمَ، أَوْ يَقْرَأَ آيَتَيْنِ مِنْ كِتَابِ اللهِ عَزَّ وَجَلَّ خَيْرٌ لَهُ مِنْ نَاقَتَيْنِ، وَثَلاَثٌ خَيْرٌ لَهُ مِنْ ثَلاَثٍ، وَأَرْبَعٌ خَيْرٌ لَهُ مِنْ أَرْبَعٍ، وَمِنْ أَعْدَادِهِنَّ مِنَ الْإِبِلِ »

«ሁልዩም ጧት፣ ጧት ወደ ቡጥሐን ወይም ዐቂቅ በመሄድ ወንጀል ሳይፈፅምና ከዘመድ ጋር ሳይቆራረጥ ሁለት ሁለት ሴት ግመሎችን ማምጣት የሚሻ ከመካከላችሁ ማን ነው?» በማለት ጠየቁ። «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሁላችንም ይህንን እንወዳለን።» አልናቸው። «እንግዲያውስ ከናንተ አንዳችሁ ወደ

መስጊድ ይሂድና እውቀት ይገብይ ወይም ከቁርአን ሁለት አናቅፅ ያን ብብ፡፡ ይህ ለርሱ ከሁለት ሴት ግመሎች የተሻለ ዋጋ አለው፡፡ ሦስት አንቀጾችን ካነበብ ከሦስት ሴት ግመሎች ይሻለዋል፡፡ አራት አናቅፅ ካነበብ ከአራት ግመሎች ይሻለዋል፡፡ ከወንድ ግመሎችም ቢሆን ይበልጣል፡፡» አሉ፡፡ (ሙስሊም)

መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

وَقَالَ ﷺ: «مَنْ قَعَدَ مَقْعَداً لَمْ يَذْكُرِ اللهَ فِيهِ كَانَتْ عَلَيْهِ مِنَ اللهِ تِرَةٌ، وَمَنِ اضْطَجَعَ مَضْجَعاً لَمْ يَذْكُرِ اللهَ فِيهِ كَانَتْ عَلَيْهِ مِنَ اللهِ تِرَةٌ».

«አንድ ሰው በሚቀመጥበት ወይም በሚጋደምበት ወቅት አላህን ካላወሳ ከአላህ ርቋል፡፡» (አቡዳውድ)

وَقَالَ ﷺ: «مَا جَلَسَ قَوْمٌ مَجْلِساً

لَمْ يَذْكُرُوا اللهَ فِيهِ، وَلَمْ يُصَلُّوا عَلَىٰ نَبِيِّهِمْ إِلَّا كَانَ عَلَيْهِمْ تِرَةً، فَإِنْ شَاءَ عَذَّبَهُمْ وَإِنْ شَاءَ غَفَرَ لَهُمْ» .

«ሰዎች በሚሰበሰቡበት ወቅት አላህንካላወሱና በነቢያቸው (ሶ.ዐ.ወ) ላይም ሰለዋት ካላወረዱ ለክስረት ተደርገዋል:: (አላህ) ከፈለገ ይቀጣቸዋል:: ከፈለገም ይምራቸዋል::» (ቲርሙዝይ)

وَقَالَ ﷺ: «مَا مِنْ قَوْمٍ يَقُومُونَ مِنْ مَجْلِسٍ لَا يَذْكُرُونَ اللهَ فِيهِ إِلَّا قَامُوا عَنْ مِثْلِ جِيفَةِ حِمَارٍ وَكَانَ لَهُمْ حَسْرَةً» .

«ሰዎች ከተቀመጡበት(ስብሰባ) ሲነሱ አላህን ካላወሱ ጥንብ ተመግበ እንደሄደ አህያ ናቸው:: ክስረት ገጥሟቸዋል::» (አቡ-ዳወድ)

## 1. ከእንቅልፍ ሲነቁ የሚባቸው ዚክሮች

١ -« الْحَمْدُ لِلَّـهِ الَّذِي أَحْيَانَا بَعْدَ مَا أَمَاتَنَا وَإِلَيْهِ النُّشُورُ» .

1. «አልሐምዱ ሊላሂለለዚ አሕያና በዕደ ማአማተና ወኢለይሒ ንኑሹር::»
«ከሞትን (ከእንቅልፍ) በኋላ ህይወትን ለለገሰን አላህ ምስጋናይገባው::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

2. የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

٢ -« لَا إِلَـهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ، وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ. سُبْحَانَ اللهِ، وَالْحَمْدُ للهِ، وَلَا إِلَـهَ إِلَّا اللهُ، وَاللهُ أَكْبَرُ، وَلَا حَوْلَ وَلَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللهِ الْعَلِيِّ الْعَظِيمِ،

رَبِّ اغْفِرْ لِي».

*«ላኢላሃ ኢልለላሁ ወሕደሁ ላሸሪከለሁ፣ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁዋ ዓላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር፤ ሱብሐነልላሁ፣ ወልሐምዱ ሊላሁ፣ ወላኢላሀ ኢልለላሁ፣ ወልላሁ አክበር፣ ወላሐውላ ወላ ቁውተ ኢልላ ቢልላሂል ዓሊዩል ዓዚም፣ ረብቢ ኢግፊር ሊ::»*

ከእንቅልፉ ባኖ የተነሳ በነቃበት ቅፅበት:- «ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አንድ ነው:: ተጋሪ የለውም:: ንግስና ለርሱ ብቻ ነው:: ምስጋናም ለርሱ ብቻ ነው:: እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው:: ለአላህ ጥራት ይገባው:: ምስጋና ለአላህ ይገባው:: ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አላህ ታላቅ ነው:: ብልሃትም +ኃይልም+! ታላቅና ልዑል በሆነው አላህ ቢሆን እንጂ የለም::» ያለና:- «አላህ ሆይ! ምህረትህን ለግሰኝ::» በማለት አላህን የተማፀነ ወንጀሉ ይማር ለታል::»

ወሊድ እንዳስተላለፈው ደግሞ:-

«ዱዓ ካደረገ ዱዓው ተቀባይነትን ያገኛል:: ከመኝታው በመነሳት ውዱእ

አድርጉ ከሰገደ ሶላቱ ተቀባ ይነትን ታገኛለች» ብለዋል:: (ቡኻሪና ሌሎችም)

«الْحَمْدُ لِلّٰهِ الَّذِي عَافَانِي فِي جَسَدِي، وَرَدَّ عَلَيَّ رُوحِي، وَأَذِنَ لِي بِذِكْرِهِ»

*3. «አልሐምዱ ሊልላሂልለዚ ዓፋኒ ፊ ጀሰዲ! ወረድደ ዓለይየ ሩሒ! ወአዚነ ሊ ቢዚክሪሒ::»*

«ለአካሌ ጤንነት ለለገሰኝ ፣ ነፍሴን ለመለሰልኝ፣ እንዳወሳውም ለፈ ቀደልኝ አላህ ምስጋና ይገባው::» (ቲርሙዝይ)

٤ - ﴿ إِنَّ فِي خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱخْتِلَٰفِ ٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ لَءَايَٰتٍ لِّأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ۞ ٱلَّذِينَ يَذْكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمْ وَيَتَفَكَّرُونَ فِى خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَٰذَا بَٰطِلًا سُبْحَٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ۞ رَبَّنَآ

إِنَّكَ مَن تُدْخِلِ ٱلنَّارَ فَقَدْ أَخْزَيْتَهُۥ وَمَا
لِلظَّٰلِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ * رَّبَّنَآ إِنَّنَا سَمِعْنَا
مُنَادِيًا يُنَادِى لِلْإِيمَٰنِ أَنْ ءَامِنُوا بِرَبِّكُمْ
فَـَٔامَنَّا ۚ رَبَّنَا فَٱغْفِرْ لَنَا ذُنُوبَنَا وَكَفِّرْ عَنَّا
سَيِّـَٔاتِنَا وَتَوَفَّنَا مَعَ ٱلْأَبْرَارِ * رَبَّنَا وَءَاتِنَا
مَا وَعَدتَّنَا عَلَىٰ رُسُلِكَ وَلَا تُخْزِنَا يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ ۗ
إِنَّكَ لَا تُخْلِفُ ٱلْمِيعَادَ * فَٱسْتَجَابَ لَهُمْ
رَبُّهُمْ أَنِّى لَآ أُضِيعُ عَمَلَ عَٰمِلٍ مِّنكُم مِّن
ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ ۖ بَعْضُكُم مِّنۢ بَعْضٍ ۖ فَٱلَّذِينَ
هَاجَرُوا وَأُخْرِجُوا مِن دِيَٰرِهِمْ وَأُوذُوا فِى
سَبِيلِى وَقَٰتَلُوا وَقُتِلُوا لَأُكَفِّرَنَّ عَنْهُمْ
سَيِّـَٔاتِهِمْ وَلَأُدْخِلَنَّهُمْ جَنَّٰتٍ تَجْرِى مِن

تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَـٰرُ ثَوَابًا مِّنْ عِندِ ٱللَّهِ ۗ وَٱللَّهُ
عِندَهُۥ حُسْنُ ٱلثَّوَابِ * لَا يَغُرَّنَّكَ تَقَلُّبُ
ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ فِى ٱلْبِلَـٰدِ * مَتَـٰعٌ قَلِيلٌ ثُمَّ
مَأْوَىٰهُمْ جَهَنَّمُ ۚ وَبِئْسَ ٱلْمِهَادُ * لَـٰكِنِ
ٱلَّذِينَ ٱتَّقَوْا۟ رَبَّهُمْ لَهُمْ جَنَّـٰتٌ تَجْرِى مِن
تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَـٰرُ خَـٰلِدِينَ فِيهَا نُزُلًا مِّنْ
عِندِ ٱللَّهِ ۗ وَمَا عِندَ ٱللَّهِ خَيْرٌ لِّلْأَبْرَارِ * وَإِنَّ
مِنْ أَهْلِ ٱلْكِتَـٰبِ لَمَن يُؤْمِنُ بِٱللَّهِ وَمَآ
أُنزِلَ إِلَيْكُمْ وَمَآ أُنزِلَ إِلَيْهِمْ خَـٰشِعِينَ لِلَّهِ
لَا يَشْتَرُونَ بِـَٔايَـٰتِ ٱللَّهِ ثَمَنًا قَلِيلًا ۗ
أُو۟لَـٰٓئِكَ لَهُمْ أَجْرُهُمْ عِندَ رَبِّهِمْ ۗ
إِنَّ ٱللَّهَ سَرِيعُ ٱلْحِسَابِ * يَـٰٓأَيُّهَا

ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱصْبِرُواْ وَصَابِرُواْ وَرَابِطُواْ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ ۝

4. «ኢንነ ፊ ኸልቂስሰማዋቲ ወል አርድ፣ ወኸቲላፊልለይሊ ወንነሓር፣ ለአያቲን ሊኡሊል አልባብ። አልለዚነ የዝኩሩነልላሃ ቂያመን ወቁዑደን ወዓላ ጁኑቢሂም፣ ወየተፈክከሩነ ፊ ኸልቂስሰማዋቲ ወል አርዲ ረብበና ማኸለቅተ ሓዛ ባጢለን ሱብሓነከ ፈቂና ዐዛበንናር። ረብበና ኢንነከ መን ቱድኺሊንናረ ፈቀድ አኽዘይተሁ፣ ወማ ሊዝዟሊሚነ ሚን አንሷር። ረብበና ኢንነናሰሚዕና ሙናዲየን ዩናዲ ሊል ኢማን፣ አን አሚኑ ቢረብቢኩም ፈአመንና፣ ረብበና ፈግፊርለና ዙኑበና፣ ወከፍፊር ዓንና ሰይአቲና፣ ወተወፍፈና መዓል አብራር። ረብበና ወአቲና ማ ዋዐድተና ዓላ ሩሱሊከ ወላ ቱኽዚና የውመል ቂያማ፣ ኢንነከ ላቱኽሊፉል ሚዓድ። ፈስተጃበ ለሁም ረብቡሁም አንኒ ላኡዲዑ ዓመለ ዓሚሊን ሚንኩም ሚን ዘከሪን አው ኡንሣ በዕዱኩም ሚን በዕድ፣ ፈልለዚነ ሓጀሩ፣ ወኡኽሪጁ ሚን ዲያሪሂም፣ ወኡዙ ፊሰቢሊ፣ ወቃተሉ ወቁቲሉ ለኡከፍፊረንነ ዐንሁም ሰይአቲሂም፣ ወለ ኡድኺለንነሁም ጀንናቲን ተጅሪ ሚን ተሕቲሓል አንሓር ሠዋበን ሚን ዒንዲልላህ፣ ወሏሁ ዒንደሁ ሑስኑል መኣብ። ላየጉርረንነከ

ተቀልሉበል ለዚነ ከፈሩ ፊል ቢላድ፣ መታዑን ቀሊል፤ ሡምመ መእዋሁም ጀሃንነም ወቢእሰል ሚሃድ፣ ላኪኒልለዚነትተቀው ረብበሁም ለሁም ጀንናቱን ተጅሪ ሚን ተሕቲሐል አንሐር፤ ኻሊዲነ ፊይሃ ኑዙለን ሚን ዒንዲልላህ፤ ወማ ዒንደልላሂ ኽይሩን ሊል አብራር፣ ወኢንና ሚን አህሊል ኪታቢ ለመን ዩእሚኑ ቢልላሂ፤ ወማ ኡንዚለ ኢለይኩም፤ ወማ ኡንዚለ ኢለይሂም ኻሺዒይነ ሊልላሂ ላየሽተሩነ ቢአያቲልላሂ ሠመነን ቀሊላ፤ ኡውላኢከ ለሁም አጅሩሁም ዒንደረብቢሂም፤ ኢንነላሃ ሰሪዑል ሒሳብ፣ ያአዩሀልለዚነ አመኑው ኢስቢሩው፤ ወሷቢሩው፤ ወራቢጡው፤ ወተተቁልላህ ለዐልለኩም ቱ፡ፍ፡ሊሁውን።»

«ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር፣ ሌሊትና ቀንንም በማተካካት ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ ምልክቶች አሉ። (እነርሱም) እነዚያ ቆመው ተቀምጠውም በጐኖቻቸው ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ፣ በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ፡- ጌታችን ሆይ! ይህን በከንቱ አልፈጠርከውም፣ ጥራት ይገባህ፣ ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን፣ የሚሉ ናቸው ።ጌታችን ሆይ! አንተ እሳት የምታገባውን

ሰው በእረግጥ አዋረድከው ለበደለኞችም ምንም ረዳቶች የሉዋቸውም::ጌታችን ሆይ! እኛ በጌታችሁ እመኑ በማለት ወደ እምነት የሚጠራን ጠሪ ሰማን፤ አመን ንም! ጌታችን ሆይ! ኃጢአቶቻችንንም ለኛ ማር፤ ክፉ ሥራዎቻችንንም ከኛ አብስ፤ ከንጹሖቹም ሰዎች ጋር ግደለን! ጌታችን ሆይ! በመልዕክተኞችም ላይ ተስፋ ቃል ያደረግክልንን ሰጠን በትንሣኤ ቀንም አታዋርደን፤ አንተ ቀጠሮን አታፈርስምና፤ (የሚሉ ናቸው):: ጌታቸ ውም እኔ ከናንተ ከወንድ ወይም ከሴት የሠሪን ሥራ አላጠፋም ከፊላችሁ ከከፊሉ ነው:: በማ ለት ለነርሱ ልመናቸውን ተቀበለ እነዚያም የተሰደዱ ከአገሮ ቻቸውም የተባረሩ በመንገዴም የተጠቁ፥ የተጋደሉም የተገደሉም፥ ክፉ ሥራዎቻ ቸውን ከነርሱ በእርግጥ አብሳለሁ፤ በሥሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሉባቸውን ገነቶች በእርግጥ አገባቸዋለሁ፤ ከአላህ ዘንድ የኾነን ምንዳ (ይመነዳሉ) አላህም እርሱ ዘንድ መልካም ምንዳ አለለ:: የነዚያ የካዱት ሰዎች በአገሮች መንፈ ላሰስ አያታልህ:: እንሰተኛ ጥቅም ነው፤

ከዚያም መኖሪያቸው ገሀነም ናት፤ ምን ትከፉም ምንጣፍ! ግን እነዚያ ጌታቸውን የፈሩ ለነሱ ከስሮ ቻቸው ወንዞች የሚፈ ሱባቸው ገነቶች፥ በውስጧ ዘውታሪዎች ሲኾኑ ከአላህ ዘንድ (የተሰጡ) መስተ ንግዶች አሏቸው፤ አላህም ዘንድ ያለው (ምንዳ) ለበጎ ሠሪዎች በላጭ ነው:: ከመጽሐፉም ባለቤቶች ለአላህ ፈሪዎች፥ በአላህ አንቀጾችም ጥቂትን ዋጋ የማይለ ውጡ ሲኾኑ፥ በአላህና በዚያ ወደ እናንተ በተወረደው በዚያም ወደነርሱ በተወረደው የሚያምኑ ሰዎች አልሉ፤ እነዚያ ለነርሱ በጌታቸው ዘንደ ምንዳቸው አላቸው፤ አላህ ምርመራው ፈጣን ነው:: እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ታገሱ፤ ተበራቱም (በጠ ር ኬላ ላይ) ተሰለፉም ትድኑም ዘንድ አላህን ፍሩ::» (አሊ ዒምራን፥ 190-200)

## 2. ልብስዎን ሲለብሱ የሚሉት ዱዓ

٥ -«الْحَمْـدُ لِلَّـهِ الَّـذِي كَسَـانِي هَـذَا (الثَّوبَ) وَرَزَقَنِيهِ مِنْ غَيْرِ حَوْلٍ مِنِّي

وَلاَ قُوَّةٍ . .

*5. «አልሐምዱ ሊልላሂልለዚ ከሣኒ ሐዛ(ስሰውበ) ወረዘቀኒሂ፣ ሚን ገይሪ ሐውሊን ሚንኒ ወላ ቁወህ።»*

«ያለእኔ ብልሃት፣ ኃይልና ጉልበት ይህንን (ልብስ) ላለበሰኝና ለለ ገሠኝ አላህ ምስጋና ይገባው...»

(አህለ ሱነን- ከነሳእይ ውጭ)

## 3. አዲስ ልብስ ሲለብሱ

٦ - « اللَّهُمَّ لَكَ الْحَمْدُ أَنْتَ كَسَوْتَنِيهِ، أَسْأَلُكَ مِنْ خَيْرِهِ وَخَيْرِ مَا صُنِعَ لَهُ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّهِ وَشَرِّ مَا صُنِعَ لَهُ»

6. *«አልሏሁምመ ለከል ሐምዱ አንተ ከሰውተኒሂ፣ አስአሉከ ሚን ኸይሪሂ ወኸይሪ ማሱኒዐ ለሁ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪሂ ወሸርሪ ማሱኒዐ ለሁ።»*

«አላህ ሆይ! ለአንተ ምስጋና የተገባ ነው። ያለበስከኝ አንተ ነህ። የዚህን (ልብስ) በጐ ገፅታና የተሠራበትን መልካም ዓላማ እንድትለግሰኝ እጠይ

ቃለሁ:: ከዚህ (ልብስ) መጥፎ ገፅታና ከተሠራበት መጥፎ ዓላማ በአንተ እጠበ ቃለሁ::»

(አቡ ዳውድ፣ ቲርሙዝይና በገውይ)

## 4. አዲስ ልብስ ለለበሰ ሰው የሚደረግ ዱዓ

٧ - «تُبْلِي وَيُخْلِفُ اللهُ تَعَالَى» .

*7. «ቱብሊ ወዩኽሊፉልሏሁ ተዓላ::»*

«(በሰላም) ይለቅ:: አላህ ምትኩን ይለግስህ::»

٨ - «اِلْبِسْ جَدِيداً، وَعِشْ حَمِيداً، وَمُتْ شَهِيداً»

*8. «ኢልበስ ጀዲደን፣ ወዒሽ ሐሚደን፣ ወሙት ሸሂደን::»*

«ሁልዩም አዳዲስ ልብሶችን ልበስ:: በሀይወት እስካለህ ድረስ አላህን አመስጋኝ

ሁን፤ ስትሞት ደግሞ ሸሂድ ሆነህ ሙት።»

## 5. ልብስዎን ሲያወልቁ

9. «ቢስሚልላህ» «بِسْمِ اللهِ» ٩
«በአላህ ስም።» (ቲርሙዝይ)

## 6. ወደ ሽንት ቤት ሲገቡ

١٠. «[بِسْمِ اللهِ] اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ الْخُبُثِ وَالْخَبَائِثِ»

10. «ቢስሚልላህ፤ አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ኹቡሲ ወል ኸባኢስ»
«(በአላህ ስም) አላህ ሆይ! ከሴትና ከወንድ ሰይጣናት ተንኮል በአንተ እጠበቃለሁ።» (ቡኻሪ)

## 7. ከሽንት ቤት ሲወጡ

*11. «ጉፍራነከ»* «غُفْرَانَكَ» - ١١
«ምህረትህን (ለግስኝ)፡፡» (አስሐበ ሱነን-ከነሳእይ ውጭ)

## 8. ከውዱእ በፊት የሚባሉ ዚክሮች

*12. «ቢስሚልላህ፡፡»* «بِسْمِ اللهِ» - ١٢
«በአላህ ስም»
(አቡዳውድና ኢብን ማጀህ)

## 9. ውዱእ ካጠናቀቁ በኋላ

١٣ - «أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ وَأَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّداً عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ..»

*13. «አሽሐዱ አን ላኢላሀ ኢልለ ላሁ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ! ወአሽሃዱ አንነ ሙሐመደን ዓብዱሁ ወረሱሉሁ፡»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም በማለት እመሰክራለሁ። አንድነው። ተጋሪ የለውም። ሙሐመድ ባሪያውና መልዕክተኛው መሆናቸውንም እመሰክ ራለሁ።» (ሙስሊም)

١٤ - «اللَّهُمَّ اجْعَلْنِي مِنَ التَّوَّابِينَ وَاجْعَلْنِي مِنَ الْمُتَطَهِّرِينَ»

*14. «አልላሁም መ ኢጅዐልኒ ሚነትተዋቢነ፣ ወጅዐልኒ ሚነል ሙተጦሂሪይን።»*

«አላህ ሆይ! ከፀፀተኞች አድርገኝ። ከንፁሃን (ባሮችህ) ጉራም ፈርጀኝ።» (ቲርሙዝይ)

١٥ - «سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ وَبِحَمْدِكَ، أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ، أَسْتَغْفِرُكَ وَأَتُوبُ إِلَيْكَ»

*15. «ሱብሐነከልሏሁም መ ወቢ ሐምዲከ፣ አሽሐዱ አንላኢላሀ ኢልላ አንተ፣ አስተግፊሩከ ወአቱቡ ኢለይከ።»*

«አላህ ሆይ! ጥራት ይገባህ። ምስጋ ናም። ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ እንደሌለ

እመሰክራለሁ:: ምህረትህን እለምንሃለሁ:: ወደ አንተም በፀፀት እመለሳለሁ::» (ንሳእይ)

## 10. ከቤት ሲወጡ

١٦ - «بِسْمِ اللهِ، تَوَكَّلْتُ عَلَى اللهِ، وَلَا حَوْلَ وَلَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللهِ»

*16. «ቢስሚላሂ፣ ተወክክልቱ ዓለላሂ፣ ወላ ሃውለ ወላ ቁውወተ ኢልላ ቢልላሂ::»*

«በአላህ ስም፤ በአላህ እመካለሁ:: ከአላህ ውጭ ብልሃትም + ኃይልም የለም::» (አቡዳውድና ቲርሙዝይ)

١٧ - «اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ أَنْ أَضِلَّ، أَوْ أُضَلَّ، أَوْ أَزِلَّ، أَوْ أُزَلَّ، أَوْ أَظْلِمَ، أَوْ أُظْلَمَ، أَوْ أَجْهَلَ، أَوْ يُجْهَلَ عَلَيَّ»

*17. «አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ አን አዲልለ አው ኡደልለ፣ አው አዚልለ አው ኡዘልለ፣ አው አዝሊመ አው ኡዝለመ፣ አው አጅሐለ አው ዩጅሐለ ዓለይየ::»*

«አላህ ሆይ! እኔ እንዳልጠም፥ ሌሎች ንም እንዳላጠም፤ ሌሎችን እንዳላሳስት፥ እኔንም ሌሎች እንዳያሳስቱኝ፤ እንዳልበ ድል፤ እንዳል በደልም በአንተ እጠበ ቃለሁ:: (አህለሉነን)

## 11. ወደ ቤት ሲገቡ

١٨ ـ «بِسْمِ اللهِ وَلَجْنَا، وَبِسْمِ اللهِ خَرَجْنَا، وَعَلَىٰ رَبِّنَا تَوَكَّلْنَا، ثُمَّ لِيُسَلِّمْ عَلَىٰ أَهْلِهِ»

*18. «ቢስሚል ላሂ ወለጅና፣ ወቢስሚ ልላሂ ኸረጅና፣ ወዓላ ረብቢና ተወክልና»*

«በአላህ ስም ተመለስን ፤ በአላህ ስም መጣን:: በጌታችን ተመካንም::» (አቡዳውድ)

## 12. ወደ መስጊድ ሲጓዙ

١٩ - اللَّهُمَّ اجْعَلْ فِي قَلْبِي نُوراً، وَفِي لِسَانِي نُوراً، وَفِي سَمْعِي نُوراً، وَفِي بصَري نُوراً، وَمِنْ فَوْقِي نُوراً، وَمِنْ تحْتِي نُوراً، وَعَنْ يَمِينِي نُوراً، وَعَنْ شِمَالِي نُوراً، وَمِنْ أَمَامِي نُوراً، وَمِنْ خلْفِي نُوراً، وَاجْعَلْ فِي نَفْسِي نُوراً، وأَعْظِمْ لِي نُوراً، وَعَظِّمْ لِي نُوراً، واجْعَلْ لِي نُوراً، وَاجْعَلْنِي نُوراً، اللَّهُمَّ أَعْطِنِي نُوراً، وَاجْعَلْ فِي عَصَبِي نُوراً، وفِي لَحْمِي نُوراً، وَفِي دَمِي نُوراً، وفِي شَعْرِي نُوراً، وَفِي بَشَرِي نُوراً»

«[اللَّهُمَّ اجْعَلْ لِي نُوراً فِي قَبْرِي . . وَنُوراً فِي عِظَامِي]» [«وَزِدْنِي نُوراً، وَزِدْنِي نُوراً، وَزِدْنِي نُوراً»] [«وَهَبْ لِي نُوراً عَلَىٰ نُورٍ»]

*19: «አልላሁምመ ኢጅዐል ፊቀልቢ ኑረን፣ ወፊ በሰሪ ኑረን፣ ወሚን ፊውቂ ኑረን፣ ወሚን ተህቲ ኑረን፣ ወዓን የሚይኒ ኑረን፣ ወዓን ሺማሊ ኑረን፣ ወሚን አማሚ ኑረን፣ ወሚን ኸልፊ ኑረን፣ ወጅዐል ፊነፍሲ ኑረን፣ ወአዕዚምሊ ኑረን፣ ወዓዝዚም ሊ ኑረን፣ ወጅዐል ሊ ኑረን፣ ወጅዐልኒ ኑረን፣ ወጅዐል ፊ ዐሰቢ ኑረን፣ ወፊ ለሕሚ ኑረን፣ ወፊ ደሚ ኑረን፣ ወፊ ሸዕሪ ኑረን፣ ወፊ በሸሪ ኑረን፤ አልላሁምመ ኢጅዐልሊ ኑረን ፊቀብሪ፣ ወኑረን ፊዒዟሚ፤ ወዚድኒ ኑረን፤ ወሐብሊ ኑረን ዓላ ኑረን፤»*

«አላህ ሆይ! ቀልቤ ውስጥ (የእምነት) ብርሃን አድርግልኝ:: ምላሴ ላይ ብርሃን አድርግልኝ:: ጆሮዬ ውስጥ ብርሃን

አድርግልኝ:: ዓይኔም ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ:: ከበላዬ ብርሃን አድርግልኝ:: ከበታቼም ብርሃን አድርግልኝ:: ከበስተቀኜም፣ ከበስተግራዬም ብርሃን አድርግልኝ:: ከፊትለፊቴ ብርሃን አድርግልኝ:: ከበስተ ኋላዬም ብርሃን አድርግልኝ:: ነፍሴ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ:: እጅግ የላቀ ብርሃን ለግሰኝ:: የገዘፈ ብርሃንን ለግሰኝ:: ብርሃንን አድርግልኝ:: ብርሃን አድርገኝ:: አላህ ሆይ! ብርሃንን ለግሰኝ:: ጅማቴ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ:: ስጋዬ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ:: ደሜ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ:: ፀጉሬ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ:: ቆዳዬ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ:: » (ቡኻሪና ሙስሊም) «አላህ ሆይ! በቀብሬ ውስጥ ብርሃን አድርግልኝ፣ በአጥንቴ ውስጥም»(ቲርሙዚ) «ብርሃን ጨምርልኝ፣ ብርሃን ጨምርልኝ፣ ብርሃን ጨምርልኝ»(ቡኻሪ) «በብርሃን ላይ ብርሃን ስጠኝ» (ኢብንሃጀር)

## 13. ወደ መስጊድ ሲገቡ

٢٠ - «أَعُوذُ بِاللهِ الْعَظِيمِ، وَبِوَجْهِهِ الْكَرِيمِ،

وَسُلْطَانِهِ الْقَدِيمِ، مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ

*20. «አዑዙ ቢልላሂል ዐዚም፣ ወቢ ወጅሂሂል ከሪም፣ ወሱልጧኒሂል ቀዲም ሚነ ሸይጧኒርረጂይ ም::»*

«በተላቀው አላህ፣ ክቡር በሆነው ፊቱ፣ ቀደምት በሆነው ስልጣኑ ከሸይጧን እጠበቃለሁ::» (አቡዳውድ)

[بِسْمِ اللهِ، وَالصَّلَاةُ] [وَالسَّلَامُ عَلَى رَسُولِ اللهِ]

*«ቢስሚላህ ወስሰላቱ ወስሰላሙ ዐላ ረሱሊላህ»*

«በአላህ ስም፣ በአላህ መልዕክተኛ ላይ ሶላትና ሰላም ይስፈን::» (አቡዳውድ)

«اللَّهُمَّ افْتَحْ لِي أَبْوابَ رَحْمَتِكَ»

*«አልላሁምመፍታህሊ አብዋበ ራህመቲክ»*

«አላህ ሆይ! የእዝነትህን በር ክፈትልኝ::» (ሙስሊም)

## 14. ከመስጊድ ሲወጡ

٢١ - «بِسْمِ اللهِ وَالصَّلَاةُ وَالسَّلَامُ عَلَىٰ رَسُولِ اللهِ، اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ مِنْ فَضْلِكَ، اللَّهُمَّ اعْصِمْنِي مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ»

*21. «ቢስሚልላሂ ወስሶላቱ ወስሰላሙ ዓላ ረሱሊልላህ፣ አልላሁምመ ኢንኒ አስአሉክ ሚን ፈድሊክ፣ አልላሁምመ አዕሲምኒ ሚነ ሸይጧኒርረጂም፤»*

«በአላህ ስም፡፡ በአላህ መልዕክ ተኛ ላይ የአላህ ሶላትና ሰላም ይስፈን፡፡ አላህ ሆይ! ከትሩፋትህ እለም ንሃ ለሁ፡፡ አላህ ሆይ! ከሸይጧን ጠብ ቀኝ፡፡»

## 15. የአዛን ዚክሮች

*22.* ሙአዚኑ (አዛን የሚያሰማው ሰው) የሚለውን እንዳለ መድገም፡፡

*«ሐየዓለል፤ ሶላህ፣ ሐየዓለል ፈላህ»*

የሚሉት ቃላት ሲቀሩ፡፡በነርሱ ምትክ፦

*«(ላሃውለ ወላቁወተ ኢላ ቢላህ)*

(ብልሃትም ኃይልም የለም- በአላህ ቢሆን እንጅ)» ይበል፡፡

٢٣ - «وَأَنَا أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَـهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ وَأَنَّ مُحَمَّداً عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ، رَضِيتُ بِاللهِ رَبّاً، وَبِمُحَمَّدٍ رَسُولًا، وَبِالْإِسْلَامِ دِيناً»

*23 «ወአነ አሽሃዱ አን ላኢላሀ ኢልለላሀ ወሀደሁ ላሸሪከ ለሁ ወአንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ፣ ረዲይቱ ቢልላሂ ረብበን፣ ወቢ ሙሐመዲን ረሱለን፣ ወቢል ኢስላሚ ዲነን»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ አንድ ነው፡፡ ተጋሪ የለውም፡፡ ሙሐመድ ባሪያውና መልዕክተኛውናቸው፡፡ በአላህ የበላይ ገዥነት፣ በሙሐመድ መልዕክተኛ ነት፣ በኢስላም ሃይማኖት ረክቻለሁ፡፡» (ሙስሊም)

«ሙአዚኑ የመጨረሻዎቹን የአዛን ቃላት ካሰማ በኋላ ይህን ይበል::» (ኢብን ኹዘይመህ)

24. «የሙአዚኑን አዛን ደግሞ ካሰማ በኋላ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሰለዋት ያውርድ::» (ሙስሊም)

25. እንዲህ ይበልም:-

٢٥ - «اللَّهُمَّ رَبَّ هٰذِهِ الدَّعْوَةِ التَّامَّةِ، وَالصَّلَاةِ الْقَائِمَةِ، آتِ مُحَمَّداً الْوَسِيلَةَ وَالْفَضِيلَةَ، وَابْعَثْهُ مَقَاماً مَحْمُوداً الَّذِي وَعَدْتَهُ، [إِنَّكَ لَا تُخْلِفُ الْمِيعَادَ]»

*«አልሏሁምመ ረብበ ሃዚሂ-ድዳዕወቲት ታመ! ወስሶላተል ቃኢመህ አቲ ሙሐመደን አልወሲለተ ወል ፈዲለህ! ወብዐስሁ መቃመን መህሙደን አልለዚ ወዐድተሁ! ኢንነከ ላቱኽሊፉል ሚይዐድ::»*

«አላህ ሆይ! የዚህች ምሉዕ ጥሪና የዚህች ለመሰገድ የቀረበች ሶላት አምላክ ነህ:: ለሙሐመድ «ወሲላ» እና «ፈዲላ» የተባሉ ገጸ ችን ለግሳቸው:: ቃል

የገባህላቸውን የተመሰገነ ደረጃም አጐናፅፈህ (ከሞት) ቀስቅሳቸው:: አንተ ቃልህን የምታጥፍ አይደለህምና::» (ቡኻሪ)

26. ማስታወሻ:- ከአዛንና ከኢቃማ መካከል የሚደረግ ዱዓ ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሆ ኑን ቲርሙዝይ፣ አቡዳወድና አህመድ ያስፈሩት የሐዲስ ዘገባ ይጠቁማል:-

«በአዛንና በኢቃም መካከል ለራሱ ዱዓ ያድርግ:: በዚያ ወቅት የሚደረግ ዱዓ ተቀባይነት አለው::» (አቡዳወድ፣ ቲርሙዝይና አህመድ)

## 16. የሰላት መግቢያ ዱዓ

٢٧ ـ « اللَّهُمَّ بَاعِدْ بَيْنِي وَبَيْنَ خَطَايَايَ كَمَا بَاعَدْتَ بَيْنَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ، اللَّهُمَّ نَقِّنِي مِنْ خَطَايَايَ، كَمَا يُنَقَّى الثَّوْبُ الأَبْيَضُ مِنَ الدَّنَس، اللَّهُمَّ اغْسِلْنِي مِنْ

خَطَايَايَ، بِالثَّلْجِ وَالْمَاءِ وَالْبَرَدِ»

*27. «አልሏሁምመ ባዒድ በይኒ ወበይነ ኸጧያየ ከማ በዐድተ በይነል መሽሪቅ ወል መግሪብ፣ አልሏሁምመ ነቂኒ ሚን ኸጧያየ ከማ ዩነቂ ሰሰውቡል አብየዱ ሚነደነሰ፣ አልላሁምመ ኢግሲልኒ ሚን ኸጧያየ ቢስሰልጅ ወል ማኢ ወል በረድ::»*

«አላህ ሆይ! ምሥራቅን ከምዕራብ እንዳራቅክ እኔንም ከወንጀሌ አርቀኝ:: አላህ ሆይ! ነጭ ልብስ ከእድፍ እንደሚ ፀዳው እኔንም ከሐጢአት አፅዳኝ:: አላህ ሆይ! ሐጢአቴን በወርጭ፣ በውሃና በበረዶ እጠብልኝ::» (ቡኻሪ)

٢٨ . - «سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ وَبِحَمْدِكَ، وَتَبَارَكَ اسْمُكَ، وَتَعَالَىٰ جَدُّكَ، وَلَا إِلَٰهَ غَيْرُكَ»

*28. «ሱብሐነከልሏሁመ ወቢሐምዲከ፣ ወተባረከስሙከ፣ ወተአላ ጀድዱከ፣ ወላኢላሀ ገይሩከ»*

«አላህ ሆይ! (ከጉድለት) የጠራህ ነህ:: ምስጋና ይገባሃል:: ስምህ የተቀደሰ ሆነ::

ልቅናህ ከፍ አለ። ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም።» (አራቱ የአሰሐበ ሱነን አባላት ዘግበውታል)

٢٩ – «وَجَّهْتُ وَجْهِيَ لِلَّذِي فَطَرَ السَّمٰوَاتِ وَالْأَرْضَ حَنِيفاً وَمَا أَنَا مِنَ الْمُشْرِكِينَ، إِنَّ صَلَاتِي، وَنُسُكِي، ومَحْيَايَ، وَمَمَاتِي لِلّٰهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ، لا شَرِيكَ لَهُ وَبِذٰلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَا مِن الْمُسْلِمِينَ. اللَّهُمَّ أَنْتَ الْمَلِكُ لَا إِلٰهَ إِلَّا أَنْتَ. أَنْتَ رَبِّى وَأَنَا عَبْدُكَ، ظَلَمْتُ نَفْسِي وَاعْتَرَفْتُ بِذَنْبِي فَاغْفِرْ لي ذُنُوبِي جَمِيعاً إِنَّهُ لَا يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلَّا أَنْتَ.

وَاهْـدِنِي لِأَحْسَنِ الأَخْـلَاقِ لَا يَهْـدِي
لِأَحْسَنِهَا إِلَّا أَنْتَ، وَاصْرِفْ عَنِّي سَيِّئَهَا،
لَا يَصْرِفُ عَنِّي سَيِّئَهَا إِلَّا أَنْتَ، لَبَّيْكَ
وَسَعْدَيْكَ، وَالْخَيْرُ كُلُّهُ بِيَدَيْكَ، وَالشَّرُّ
لَيْسَ إِلَيْكَ، أَنَا بِكَ وَإِلَيْكَ، تَبَارَكْتَ
وَتَعَالَيْتَ، أَسْتَغْفِرُكَ وَأَتُوبُ إِلَيْكَ»

29. «ወጀኻህቱ ወጅሒ ሊልለዚ ፈጠረስሰማዋቲ ወል አርደ ሐኒፈን ወማ አነ ሚነል ሙሽሪኪን፣ ኢንነ ሶላቲ ወኑሱኪ ወመሕያየ ወመማቲ ሊልላሂ ረብቢል ዓለሚን፣ ላሸሪከ ለሁ፣ ወቢዛሊከ ኡሚርቱ ወአነ ሚነል ሙስሊሚን፣ አልሏሁምመ አንተል መሊኩ ላኢላሃ ኢልላ አንተ፣ አንተ ረብቢ ወአነ ዐብዱከ፣ ዘለምቱ ነፍሲ፣ ወዕተረፍቱ ቢዘንቢ፣ ፈግፊርሊ ዙኑቢ ጀሚዐን፣ ኢንነሁ ላየግፊሩዝዙኑበ ኢልላ አንተ ወህዲኒ ሊአሕሰኒል አኽላቂ ላየህዲ ሊአሕሰኒሀ ኢልላ አንተ፣ ለብበይከ ወሰዕደይከ፣ ወል

*ኸይሩ ኩልሉሁ ቢየዲክ፣ ወሸሸሩ ለይሰ ኢለይክ፣ አነ ቢከ ወኢለይክ፣ ተባረክተ ወተዓለይት፣ አስተግፊሩክ ወአቱቡ ኢለይክ»*

«ወደዚያ ሰማያትንና ምድርን ወደ ፈጠረው አምላክ ፊቴን አዞርኩ:: ቀጥ በማለት:: እኔ ከአጋ ሪዎች አይደ ለሁም:: ስግደቴም፥ መስዋዕቴም፥ ህይወ ቴም፥ ሞቴም ለአላህ ነው:: ለአለማት ጌታ:: አጋር የለ ውም:: ይህን እንድፈፅም ታዝዣለሁ:: እኔ ከሙስሊሞች ነኝ:: አላህ ሆይ! ንጉሡ አንተ ነህ:: ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አንተ ጌታዬ ነህ:: እኔ ደግሞ ባሪያህ ነኝ:: ራሴን በድያለሁ:: ሐጢአት መሥራቴን አውቂያለሁ:: ሁሉ ንም ሐጢአቶቼን ማርልኝ:: ከአንተ ውጭ ሐጢአቴን የሚምር (ኃይል) የለም:: መልካም ሥነ-ምግባርን ለመጐ ናፀፍ አብቃኝ:: ለመልካም ሥነ- ምግባር የምታበቃው አንተ ብቻ ነህና:: መጥፎ ባህሪን አስወግድልኝ:: መጥፎ ባህሪን የሚያስወግደው አንተ ብቻ ነህና:: አቤቱ ጌታዬ! መልካም ነገሮች ሁሉ በእጅህ ናቸው:: ክፉ ነገሮች ከአንተ የሚመነጩ አይደሉም:: እኔ (የተገኘሁት)። በአንተ

ነው:: ወደ አንተም እመለሳለሁ:: የተቀ ደሰክ፣ ልዑልም ነህ:: ምህረትህን እለምናለሁ:: ወደ አንተ በፀሎት እመ ለሳለሁ::» (ሙስሊም)

٣٠ - «اللَّهُمَّ رَبَّ جِبْرَائِيلَ، وَمِيكَائِيلَ، وَإِسْرَافِيلَ فَاطِرَ السَّمٰوَاتِ وَالأَرْضِ، عَالِمَ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ، أَنْتَ تَحْكُمُ بَيْنَ عِبَادِكَ فِيمَا كَانُوا فِيهِ يَخْتَلِفُونَ. اهْدِنِي لِمَا اخْتُلِفَ فِيهِ مِنَ الْحَقِّ بِإِذْنِكَ إِنَّكَ تَهْدِي مَنْ تَشَاءُ إِلَىٰ صِرَاطٍ مُسْتَقِيمٍ»

30. *«አልላሁምመ ረብበ ጂብረል ወሚካኤል ወኢስራፊል፣ ፋጢረስሰማዋቲ ወል አርድ፣ ዓሊመል ገይቢ ወሽሽሃደህ፣ አንተ ተሕኩሙ በይነ ዒባዲከ ፊይማ ካኑ ፊሂ የኽተሊፉን ኢህዲኒ ሊመኽቱሊፈ ፊሂ ሚነል ሐቅ ቢኢዝኒከ ኢንነከ ተሕዲ መን ተሻኡ ኢላ ሲራጢን ሙስተቂም»*

«የጂብሪል፣ የሚካኤልና የኢሥራፊል አምላክ ሆይ! የሰማያትና የምድር ፈጣሪ+ ሚስጥርንም ግልፅንም አዋቂ የሆንክ አምላክ ሆይ! አንተ ባሮችህ ይወዛገቡበት በነበረው ነገር ላይ የመጨረሻ ብይን ትሰጣለህ። ከተወዛገቡበት ነገር ትክክለ ኛውን አስጨብጠኝ-በፈቃድህ። አንተ ወደ ቀጥተኛው ጉዳና ትመራለህ።» (ሙስሊም)

٣١ – «اللهُ أَكْبَرُ كَبِيراً، اللهُ أَكْبَرُ كَبِيراً، اللهُ أَكْبَرُ كَبِيراً، وَالْحَمْدُ لِلَّٰهِ كَثِيراً، وَالْحَمْدُ لِلَّٰهِ كَثِيراً، وَالْحَمْدُ لِلَّٰهِ كَثِيراً، وَسُبْحَانَ اللهِ بُكْرَةً وَأَصِيلاً»

*31. «አልሏሁ አክበር ከቢራ፣ አልሏሁ አክበር ከቢራ፣ አልሏሁ አክበር ከቢራ፣*

*ወልሐምዱ ሊልላሂል ከሢራ፣ ወልሐምዱ ሊልላሂል ከሢራ፣ ወልሐምዱ ሊልላሂል ከሢራ፣ ወሱብሐነልላሂ ቡክረተን ወአሲላ፤ »*

«አላህ ታላቅ ነው፡፡ አላህ ታላቅ ነው፡፡ አላህ ታላቅ ነው፡፡ በርካታ ምስጋና ለአላህ፡፡ በርካታ ምስጋና ለአላህ፡፡ በርካታ ምስጋና ለአላህ፡፡በጧትም በማታም ለአላህ ጥራት ይገባው፡፡» (ሦስት ጊዜ)

በመቀጠልም፡-

«أَعُـوذُ بِاللهِ مِنَ الشَّيْطَانِ : مِنْ نَفْخِهِ ، وَنَفْثِهِ ، وَهَمْزِهِ»

«አዑዙ ቢልላሂ ሚነሸይጧኒ፡ ሚንነፍኺሂ ወነፍሢሂ ወሐምዚሂ »

«ከሰይጣን ተንኮልና ጥቃት በአላህ እጠበቃለሁ፡፡» (ሙስሊም፣ ኢብን ማጀህና አህመድ)

٣٢ - «اللَّهُمَّ لَكَ الْحَمْدُ أَنْتَ نُورُ

السَّمٰواتِ وَالأَرْضِ وَمَنْ فِيهِنَّ، وَلَكَ الْحَمْدُ أَنْتَ قَيِّمُ السَّمٰواتِ وَالأَرْضِ وَمَنْ فِيهِنَّ، [وَلَكَ الْحَمْدُ أَنْتَ رَبُّ السَّمٰواتِ وَالأَرْضِ وَمَنْ فِيهِنَّ] [وَلَكَ الْحَمْدُ لَكَ مُلْكُ السَّمٰواتِ وَالأَرْضِ وَمَنْ فِيهِنَّ] [وَلَك الْحَمْدُ أَنْتَ مَلِكُ السَّمٰواتِ وَالأَرْضِ] [وَلَكَ الْحَمْدُ] [أَنْتَ الْحَقُّ، وَوَعْدُكَ الْحَقُّ، وَقَوْلُكَ الْحَقُّ، وَلِقَاؤُكَ الْحَقُّ، وَالْجَنَّةُ حَقٌّ، والنَّارُ حَقٌّ، وَالنَّبِيُّونَ حَقٌّ، وَمُحَمَّدٌ ﷺ حَقٌّ، وَالسَّاعَةُ حَقٌّ] [اللَّهُمَّ لَكَ

أَسْلَمْتُ، وَعَلَيْكَ تَوَكَّلْتُ، وَبِكَ آمَنْتُ، وَإِلَيْكَ أَنَبْتُ، وَبِكَ خَاصَمْتُ، وَإِلَيْكَ حَاكَمْتُ. فَاغْفِرْ لِي مَا قَدَّمْتُ، وَمَا أَخَّرْتُ، وَمَا أَسْرَرْتُ، وَمَا أَعْلَنْتُ] [أَنْتَ الْمُقَدِّمُ، وَأَنْتَ الْمُؤَخِّرُ لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ] [أَنْتَ إِلَهِي لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ]»

32. «አልሏሁምመ ለከል ሐምድ፤ አንተ ኑሩስሰማዋቲ ወል አርዲ ወመን ፊሂንነ፤ ወለከል ሐምዱ አንተ ቀይሙስሰማዋቲ ወል አርዲ ወመን ፊሂንነ፤ ወለከል ሐምዱ አንተ ረብቡስሰማዋቲ ወል አርዲ ወመን ፊሒንነ ወለከል ሐምዱ ለከሙልኩስሰማዋቲ ወል አርዲ ወለከል ሐምዱ አንተል ሐቅቁ፤ ወወዕዱከል ሐቅቁ፤ ወቀውሉከል ሐቅቁ፤ ወሊቃኡከል ሐቅቁ፤ ወልጀንነቱ ሐቅቁን፤ ወንናሩ ሐቅቁን፤ ወንነቢዩን ሐቅቁን፤ ወሙሐመዱን ሐቅቁን፤ ወስሳዐቱ ሐቅቁን፤ አልሏሁምመ ለከ አስለምቱ፤ ወዐለ

*ይከ ተወከከልቱ፣ ወቢከ አመንቱ ወኢለይከ አነብቱ፣ ወቢከ ኻሰምቱ፣ ወኢለይከ ሐከምቱ፣ ፈግፈር ሊማ ቀደምቱ፣ ወማ አኽኽርቱ፣ ወማ አስረርቱ፣ ወማ አዕለንቱ አንተል ሙቀዲሙ፣ ወአንተል ሙአኺሩ፣ ላኢላሃ ኢልላ አንተ፣ አንተ ኢላሂ ላኢላሃ ኢልላ አንተ፤»*

«አላህ ሆይ! ለአንተ ምስጋና ተገቢነው:: የሰማያትና የምድር፣ በውስጣቸው ያሉ ነገሮችም ብርሃን አንተ ነህ:: ምስጋና ተገቢ የሚሆነው ለአንተ ነው:: ሰማያት ንና ምድርን፣ በውስጣቸው ያሉ ፍጡራን ንም ያቆምክ አንተ ነህ:: ምስጋና ለአንተ ነው:: የሰማያትና የምድር፣ እንዲሁም በመካከላቸው ያሉ ነገሮች አምላክ ነህ:: ምስጋና ተገቢነቱ ለአንተ ነው:: የሰማያ ትና የምድር በውስጣቸው ያሉ ነገሮችም ንግሥና የአንተ ብቻ ነው:: ምስጋና ተገቢነቱ ለአንተ ብቻ ነው:: የሰማያትና የምድር ንግስና የአንተ ነው:: ምስጋና ተገቢነቱ ለአንተ ብቻ ነው:: አንተ እውነት ነህ:: ቃል ኪዳንህም እውነት ነው:: ንግግርህ እውነት ነው:: አንተን የመገናኘት ነገር እውነት ነው:: ጀንነት እውነት ነው:: እሳትም እውነት ነው::

ነቢያት እውነት ናቸው። ሙሐመድ እውነት ነው። ምፅአት እውነት ነው። አላህ ሆይ! እኔነቴን ለአንተ አስረከብኩ። በአንተ ተመካሁ። በአንተ አመንኩ። ወደ አንተም ተመለስኩ። በአንተ ተከራከርኩ። ወዳንተ ተፋረድኩ። ከአሁን በፊት ያስቀደምኩትን፣ ወደፊትም የምፈፅመውን፣ በስውረም በግልፅም የፈፀምኩትን ወንጀል ሁሉ ማርልኝ። የምታስቀድምም የምታዘገይም አንተ ነህ። ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። አንተ አምላኬ ነህ።ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም።» (ቡኻሪ)

## 17. ሩኩዕ ላይ የሚደረግ ዱዓ

٣٣ - "سُبْحَانَ رَبِّيَ الْعَظِيمِ"

*33. «ሱብሓነ ረቢየል ዐዚም»*
«ታላቅ የሆነው ጌታ (ከጉድለቶች) ሁሉ የጠራ ነው።» ሦስት ጊዜ። (አህለሱነንና አህመድ)

٣٤ - "سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ رَبَّنَا وَبِحَمْدِكَ اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي"

34. «ሱብሐነከልላሁምመ ረብበና ወቢሐምዲክ፣ አልላሁምመ ኢግፊርሊ።»
«ጌታችን አላህ ሆይ! ጥራት ይገባሀ። ምስጋና ለአንተ ተገቢ ነው። አላህ ሆይ! ምህረትህን ለግሠኝ።» (ቡኻሪ)

٢٥ - "سُبُّوحٌ، قُدُّوسٌ، رَبُّ الْمَلَائِكَةِ وَالرُّوحِ"

35. «ሱብቡሑን ቁዱሱን፣ ረብቡል መላኢከቲ ወርሩሁ»
«ብፁእና ቅዱስ (አምላክ)። የመላእክታንና የመንፈሱ ጌታ።» (ሙስሊም)

٣٦ - "اللَّهُمَّ لَكَ رَكَعْتُ، وَبِكَ آمَنْتُ، وَلَكَ أَسْلَمْتُ خَشَعَ لَكَ سَمْعِي، وَبَصَرِي، وَمُخِّي، وَعَظْمِي، وَعَصَبِي، وَمَا اسْتَقَلَّ بِهِ قَدَمِي"

36. «አልላሁምመ ለከ ረከዕቱ፣ ወቢከ አመንቱ፣ ወለከ አስለምቱ፣ ኸሸዐ ለከ ሰምዒ፣

*ወበሰሪ፣ ወሙኽኺ፣ ወአዝሚ፣ ወዐሰቢ፣ ወመስተቀልለ ቢሂ ቀደሚ »*
«አላህ ሆይ! ለአንተ ሩኩዕ አደረግኩ:: በአንተ አመንኩ:: ለአንተ እኔነቴን አስረ ከብኩ:: ጆሮዬም፣ ዓይኔም፣ ቅልጥሜም፣ አጥንቴም፣ ጅማቴም፣ እግሮቼ የተሸ ከሙት ሁሉም ለአንተ አጉበደዱ::»
(ሙስሊም)

٣٧ - «سُبْحَانَ ذِي الْجَبَرُوتِ، وَالْمَلَكُوتِ، وَالْكِبْرِيَاءِ، وَالْعَظَمَةِ»

*37. «ሱብሐነ ዚል ጀበሩት፣ ወል መለኩት፣ ወል ኪብሪያእ፣ ወል ዐዘመህ::»*
«ጥራት ይገባህ::የክብርና የንግሥና፣ የኩራትና የልቅና ባለቤት ነህ::»
(አቡዳውድ፣ ነሳእይና አህመድ)

## 18. ከሩኩዕ ሲነሱ

٣٨ - «سَمِعَ اللهُ لِمَنْ حَمِدَهُ»

*38. «ሰሚዐልሏሁ ሊመን ሐሚደሁ»*

«አላህ የሚያመሰግነውን ይሰማል።» (ቡኻሪ)

٣٩ - «رَبَّنَا وَلَكَ الْحَمْدُ، حَمْداً كَثِيراً طَيِّباً مُبَارَكاً فِيهِ»

*39 «ረብበና ወለከል ሐምዱ፣ ሐምደን ከሢረን ጠይበን ሙባረከን ፊይሂ»*

«ጌታችን ሆይ! ምስጋና ይገባሀ። ብዙ፣ መልካምና የተባረከ ምስጋና።» (ቡኻሪ)

٤٠ - «مِلْءَ السَّمٰوَاتِ وَمِلْءَ الأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا، وَمِلْءَ مَا شِئْتَ مِنْ شَيْءٍ بَعْدُ. أَهْلَ الثَّنَاءِ وَالْمَجْدِ، أَحَقُّ مَا قَالَ الْعَبْدُ، وَكُلُّنَا لَكَ عَبْدٌ. اللَّهُمَّ لَا مَانِعَ لِمَا أَعْطَيْتَ، وَلَا مُعْطِيَ لِمَا مَنَعْتَ، وَلَا يَنْفَعُ ذَا الْجَدِّ مِنْكَ الْجَدُّ»

*40. «ሚልዐሰሰማዋቲ ወሚልአል አርዲ ወማበይነሁማ፣ ወሚልአ ማሺእተ ሚን ሸይኢን በዕዱ፣ አህለ ሰናኢ ወል መጅዲ፣ አሐቁ ማቃለል ዐብዱ፣ ወኩሉና ለከ ዐብዱን፣ አልላሁምመ ላማኒዐ ሊማ አዕጠይተ፣ ወላ ሙዕጢ ሊማ መነዕተ፣ ወላ የንፈዑ ዙል ጀድዲ ሚንከል ጀዱ።»*

« (አላህ ሆይ!) ሰማያትንና ምድርን፥ እንዲሁም በመካከላቸው ያለውን፥ ከነገሮች የፈለግከውንም የሚሞላ (ምስጋና ይገባህ)። የውዳሴና ክብር ባለቤት የሆንከው (አምላክ) ሆይ! ባሪያህ - ሁላችንም የአንተ ባሪያ ነን- ካለህ ሁሉ በላጩ ተከታዩ ነው፡- አላህ ሆይ! አንተ የሰጠህውን የሚነፍገው! የነፈግከውን የሚሰጠው የለም። ከአንተ ዘንድ የክብር ባለቤት ክብሩ ቅንጣት አይፈይደውም።» (ሙስሊም)

## 19. ሱጁድ ላይ የሚደረግ ዱዓ

٤١ – «سُبْحَانَ رَبِّيَ الأَعْلَى»

*41. «ሱብሓነ ረብቢየል አዕላ»*

«ልዑል የሆነው አላህ ጥራት ይገባው::»- ሦስት ጊዜ:: (አህለሱነንና አህመድ)

٤٢ - «سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ رَبَّنَا وَبِحَمْدِكَ

اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي»

*42. «ሱብሐነከልኋሁምመ ረብበና ወቢ ሐምዲከ አልኋሁምመ ኢግፊርሊ»*

«ጌታችን አላህ ሆይ! ጥራት ይገባህ:: ምስጋናም:: አላህ ሆይ! ምህረትን ለግሰኝ::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

*43. «ሱብቡሑን ቁድዱስ! ረብቡል መላኢከቲ ወርሩሀ::»*

«ብፁእና ቅዱስ አምላክ:: የመላእክታንና የመንፈሱ ጌታ::» (ሙስሊም)

٤٤ - «اللَّهُمَّ لَكَ سَجَدْتُ وَبِكَ آمَنْتُ ،

وَلَكَ أَسْلَمْتُ ، سَجَدَ وَجْهِيَ لِلَّذِي خَلَقَهُ ،

وَصَوَّرَهُ ، وَشَقَّ سَمْعَهُ وَبَصَرَهُ ، تَبَارَكَ

اللهُ أَحْسَنُ الْخَالِقِينَ»

*44. «አልሏሁምመ ለከ ሰጀድቱ ወቢከ አመንቱ፣ ወለከ አስለምቱ፣ ሰጀደ ወጅሂ ሊልለዚ ኸለቀሁ፣ ወሰውወረሁ፣ ወሸቅቀ ሰምዐሁ ወበሰረሁ ተባረከልሏሁምመ አህሰኑል ኸሊቂን»*

«አላህ ሆይ! ለአንተ ሱጁድ አደረግኩ፡፡በአንተ አመንኩ፡፡ እኔነቴን ለአንተ አስረከብኩ፡፡ ፊቴ ለዚያ ለፈጠረውና ለቀረው ፣ መስሚያ ጆሮና መመልከቻ ዓይን ላበጀለት አምላክ ሰገደ፡፡ አላህ የተቀደሰ ነው፡፡ ወደር የለሽ ፈጣሪም ነው፡፡ » (ሙስሊም)

*45. «ሱብሓነ ዚል ጀበሩውት፣ ወል መለኩውት፣ ወልኪብሪያእ፣ ወል ዐዘመህ፡፡»*

«ጥራት ይገባህ! የክብርና የንግሥና! የኩራትና የልቅና ባለቤት ነህ፡፡» (አቡዳውድ፣ አህመድና ነሳእይ)

٤٦ – «اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي ذَنْبِي كُلَّهُ، دِقَّهُ وجِلَّهُ، وَأَوَّلَهُ وَآخِرَهُ وَعَلَانِيَتَهُ وَسِرَّهُ»

*46. «አልሏሁምመ ኢግፊር ሊዘንቢ ኩልለሁ፣ ዲቅቀሁ ወጂልለሁ፣ ወአውወለሁ፣*

*ወአኺረሁ፣ ወዐላ ንየተሁ ወሲርረሁ»*

«አላህ ሆይ! ወንጀሌን ሁሉ ማርልኝ፤ ትንሹንም ትልቁንም፤ የመጀመሪያውንም የመጨረሻውንም፤ በግል ፅም+ በስውርም የተፈፀመውንም።» (ሙስሊም)

٤٧ - اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِرِضَاكَ مِنْ سَخَطِكَ، وَبِمُعَافَاتِكَ مِنْ عُقُوبَتِكَ وَأَعُوذُ بِكَ مِنْكَ، لَا أُحْصِي ثَنَاءً عَلَيْكَ أَنْتَ كَمَا أَثْنَيْتَ عَلَى نَفْسِكَ »

*47. «አልላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢሪዷከ ሚን ሰኽጢከ፣ ወቢ ሙዓፋቲከ ሚን ዑቁባቲከ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚንከ፣ ላኡህሲ ሠናአን ዐለይከ አንተ ከማ አሥነይተ ዐላ ነፍሲከ።»*

«አላህ ሆይ! በውዴታህ ከቁጣህ+ በይቅር ባይነትህ ከቅጣትህ እጠበቃለሁ። ካንተ በአንተ እጠበቃለሁ። አንተ ራስህን ያወደስከውን ያክል ላወድስህ አይሆንልኝም።» (ሙስሊም)

## 20. በሱጁዶች መካከል የሚደረግ ዱዓ

«رَبِّ اغْفِرْ لِي رَبِّ اغْفِرْ لِي» - ٤٨

*48. «ረብቢ ኢግፊር ሊ፣ ረብቢ ኢግፊር ሊ»*
«አላህ ሆይ! ምህረትህን ለግሠኝ:: አላህ ሆይ! ምህረትህን ለግሠኝ::» (አቡዳውድ)

«اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي، وَارْحَمْنِي، وَاهْدِنِي، وَاجْبُرْنِي، وَعَافِنِي، وَارْزُقْنِي، وَارْفَعْنِي»

*49. «አልላሁምመ ኢግፊርሊ፣ ወርሐምኒ፣ ወህዲኒ፣ ወጅቡርኒ፣ ወዐፊኒ፣ ወርዙቅኒ፣ ወርፈዕኒ»*
«አላህ ሆይ! ምህረትህን ለግሠኝ:: እዘንልኝ፤ ምራኝ፤ ጠግነኝ፤ ጤንነትን ለግሠኝ፤ ሲሳይን ለግሠኝ! ከፍ አድርገኝም::» (አስሐበሱነን- ከነሳኢይ ውጭ)

## 21. በሱጁድ ቲላዋህ ወቅት (ሱጁድ የሚያስፈልገው የቁርአን አንቀፅ ሲነበብ) የሚደረግ ዱዓ

٥٠ - «سَجَدَ وَجْهِيَ لِلَّذِي خَلَقَهُ، وَشَقَّ سَمْعَهُ وَبصَرَهُ بِحَوْلِهِ وَقُوَّتِهِ، ﴿فَتَبَارَكَ ٱللَّهُ أَحْسَنُ ٱلْخَٰلِقِينَ﴾

50. «ሰጀደ ወጅሂየ ሊልለዚ ኸለቀሁ፣ ወሸቅቀ ሰምዐሁ ወበሰረሁ ቢሐውሊሂ ወቁውወቲሂ፣ ፈተባረከልላሁ አሕሰኑል ኻሊቂን»

«ፊቴ ለዚያ በኃይሉና በብልሃቱ ለፈጠረው፣ ጆሮውንና ዓይኑን ላበጀለትም (አምላክ) ሰገደ:: አፈጣጠሩን ያሳመረ የሆነው አላህ ረድኤተ ብዙ ነው::» (ቲርሙዚይ)

٥١ - «اللَّهُمَّ اكْتُبْ لِي بِهَا عِنْدَكَ أَجْراً، وَضَعْ عَنِّي بِهَا وِزْراً، وَاجْعَلْهَا لِي عِنْدَكَ ذُخْراً، وَتَقَبَّلْهَا مِنِّي كَمَا تَقَبَّلْتَهَا مِنْ عَبْدِكَ دَاوُدَ»

*51. «አልላሁምመ ኢክቱብ ሊ ቢሀ ዒንደክ አጅራ! ወደዕ ዐኒ ቢሃ ዊዝራ! ወጅዐልሃ ሊ ዒንደክ ዙኽራ! ወተቀበልሃ ሚኒ ከማ ተቀበልተሃ ሚን ዐብዲከ ዳውድ::»*

«አላህ ሆይ! በርሷ ከአንተ ዘንድ ምንዳን ጻፍልኝ:: ወንጀሌን በርሷ (ሰበብ) አራግፍልኝ:: ከአንተ ዘንድ ድልብ አድርገልኝም:: ከባሪያህ ከዳውድ እንደተ ቀበልካት ከኔም ተቀ በለኝ::» (ቲርሙዚይ)

## 22. ተሸሁድ

٥٢ «التَّحِيَّاتُ لِلَّهِ، والصَّلَوَاتُ، وَالطَّيِّبَاتُ، السَّلَامُ عَلَيْكَ أَيُّهَا النَّبِيُّ وَرَحْمَةُ اللهِ وَبَرَكَاتُهُ، السَّلَامُ عَلَيْنَا وَعَلَىٰ عِبَادِ اللهِ الصَّالِحِينَ. أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللهُ وَأَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّداً عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ».

*52. «አትተሂያቱ ሊልላሂ፣ ወስሰለዋቱ፣ ወጥጠይባቱ፣ አስሰላሙ ዐለይከ አይዩሃንነቢዩ ወራህመቱልላሂ ወበረካቱሁ፣ አስሰላሙ ዐለይና ወዐላ ዒባዲልላሂ ስስሷሊሂን፣ አሽሃዱ አን ላ ኢላሃ ኢልለላሁ ወአሽሃዱ አንነ ሙሃመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ»*

«ክብር ሁሉ ለአላህ ነው:: ሶላቶችና መልካም ተግባራትም ለአላህ ናቸው:: አንተ ነብይ ሆይ! ሰላም በአንተ ላይ ይውረድ:: የአላህ እዝነትና ውዴታም ይስፈንብህ:: በእኛና በአላህ ቅን ባሪያዎ ችም ላይ ሰላም ይስፈን:: ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ:: ሙሐመድ ባሪያውና መልዕክተኛው መሆናቸውን እናዘዛለሁ::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

## 23. ከተሸሁድ በኋላ በነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) ላይ ሶለዋት ማውረድ

٥٣ - «اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِ مُحَمَّدٍ، كَمَا صَلَّيْتَ عَلَىٰ إِبْرَاهِيمَ

وَعَلَىٰ آلِ إِبْرَاهِيمَ، إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ، اللَّهُمَّ بَارِكْ عَلَىٰ مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِ مُحَمَّدٍ كَمَا بَارَكْتَ عَلَىٰ إِبْرَاهِيمَ وَعَلَىٰ آلِ إِبْرَاهِيمَ، إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ»

*«አልሏሁምመ ሶሊ ዓላ ሙሐመዲን ወዓላ ዓሊ ሙሐመዲን፣ ከማ ሶለይታ ዓላ ኢብራሂም ወዓላ አሊ ኢብራሂም፣ ኢንነከ ሀሚዱምመጂድ፣ አልሏሁምመ ባሪክ ዓላ ሙሐመዲን ወዓላ አሊ ሙሐመዲን፣ ከማ ባረክታ ዓላ ኢብራሂም ወዓላ አሊ ኢብራሂም ኢንነከ ሃሚዱምመጂድ»*

«አላህ ሆይ! በሙሐመድና በቤተሰቦቻቸው ላይ እዝነትህን አስፍን፤ በኢብራሂምና በቤተሰቦቻቸው ላይ እዝነትህን እንዳሰፈንክ ሁሉ:: አንተ ምስጉንና የተላቅክ ነህ:: አላህ ሆይ! በሙሐመድና በቤተሰቦቻቸው ላይ ረድኤትህን አስፍን! በኢብራሂምና በቤተሰቦቻቸው ላይ ረድኤትህን እንዳሰፈንክ ሁሉ:: አንተ ምስጉንና የተላቅክ ነህ::» (ቡኻሪ)

٥٤ - «اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ أَزْوَاجِهِ وَذُرِّيَّتِهِ، كَمَا صَلَّيْتَ عَلَىٰ آلِ

إِبْرَاهِيمَ. وَبَارِكَ عَلَىٰ مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ أَزْوَاجِهِ وَذُرِّيَّتِهِ، كَمَا بَارَكْتَ عَلَىٰ آلِ إِبْرَاهِيمَ. إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ»

*54 «አልላሁምመ ሰልሊ ዓላ ሙሐመዲን ወዓላ አዝዋጂሂ ወዙርሪየቲሂ፣ ከማ ሰልለይተ ዓላ ኣሊ ኢብራሂመ ወባሪክ ዓላ ሙሐምመዲን ወዓላ አዝዋጂሂ ወዘርሪየቲሂ ከማ ባረከተ ዓላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢንነከ ሃሚዱን መጂድ»*

«አላህ ሆይ! በሙሐመድ፣ በባልተቤቶቻቸውና በልጆቻቸው ላይ እዝነትህን አስፍን፤ በኢብራሂም ላይ እንዳሰፈንከ ሁሉ:: በሙሐመድ፣ በባልተቤቶቻቸውና በልጆቻቸው ላይ ረድኤትህን አስፍን! በኢብራሂም ላይ ረድኤትህን እንዳሰፈንከ ሁሉ:: አንተ ምስጉንና የተላቅክ ነህ::»

## 24. ከመጨረሻው ተሸሁድ በኋላ ሶላት ከመጠናቀቁ በፊት የሚደረግ ዱዓ

٥٥ - «اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ، وَمِنْ عَذَابِ جَهَنَّمَ، وَمِنْ فِتْنَةِ الْمَحْيَا وَالْمَمَاتِ، وَمِنْ شَرِّ فِتْنَةِ الْمَسِيحِ الدَّجَّالِ»

*55. «አልሏሁምመ ኢንኒ አኡዙቢከ ሚን አዛቢልቀብር ወሚን አዛቢ ጀሀንነመ ወሚን ፊትነቲል መህያ ወልመማት ወሚን ሸርሪ ፊትነቲል መሲሀ አል አድደጃል::»*

«አላህ ሆይ! ከቀብር ቅጣትም፥ በህይወትም ሆነ ከሞት በኋላ ከሚከሰት ፈተናም፥ እንዲሁም ከአታላዩ መሲሐደጃል ፈተና በአንተ እጠበቃለሁ::» (ቡኻሪ)

٥٦ - «اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ فِتْنَةِ الْمَسِيحِ الدَّجَّالِ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ فِتْنَةِ الْمَحْيَا وَالْمَمَاتِ. اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ

الْمَأْثَمِ وَالْمَغْرَمِ»

*56. «አልሏሁምመ ኢንኒ አኡዙ ቢከ ሚን አዛቢልቀብሪ ወአኡዙቢከ ሚን ፊትነቲል መሲህ አድደጃል ወአኡዙ ቢከ ሚን ፊትነቲል መህያ ወልመማት አልሏሁምመ ኢንኒ አኡዙ ቢከ ሚነል መእሰሚ ወልመግረም»*

«አላህ ሆይ ! ከቀብር ቅጣት፥ ከገሃነም ቅጣትም፥ በህይወትም ሆነ ከሞት በኋላ ከሚከሰት ፈተና፥ እንዲሁም ከአታላዩ መሲሐደጀል በአንተ እጠበቃለሁ። አላህ ሆይ! ከወንጀልና በመጭው ዓለም ዕዳ ከፋይ ከመሆን በአንተ እጠበቃለሁ።» (ቡኻሪ)

٥٧ - «اللَّهُمَّ إِنِّي ظَلَمْتُ نَفْسِي ظُلْماً كَثِيراً، وَلَا يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلَّا أَنْتَ، فَاغْفِرْ لِي مَغْفِرَةً مِنَ عِنْدِكَ وَارْحَمْنِي

إِنَّكَ أَنْتَ الْغَفُورُ الرَّحِيمُ»

*57. «አልኋሁምመ ኢንኒ ዘለምቱ ነፍሲ ዙልመን ከሲራ፣ ወላ የግፊሩዝዙኑበ ኢልላ አንተ፣ ፈግፊር ሊ መግፊረተን ሚን ኢንዲከ ወርሃምኒ ኢንነከ አንተል ገፉሩ አርረሂም»*

«አላህ ሆይ! እኔ ነፍሴን በርካታ በደል በድያለሁ:: ሐጢአትን ከአንተ ውጭ የሚምር የለም:: ከአንተ የሆነን ምህረት ለግሰኝ::እዘንልኝ::አንተመሐሪና አዛኝ ነህና::»
(ቡኻሪና ሙስሊም)

٥٨ ـ «اللَّهُمَّ اغْفِرَ لِي مَا قَدَّمْتُ، وَمَا أَخَّرْتُ، وَمَا أَسْرَرْتُ، وَمَا أَعْلَنْتُ، وَمَا أَسْرَفْتُ، وَمَا أَنْتَ أَعْلَمُ بِهِ مِنِّي. أَنْتَ الْمُقَدِّمُ، وَأَنْتَ الْمُؤَخِّرُ لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ»

*58. «አልኋሁምመ ኢግፊርሊ ማቀድደምቱ ወማ አኽከርቱ ወማ አስረርቱ ወማ አእለንቱ ወማ አስረፍቱ ወማ አንተ አእለሙ ቢሂ ሚንኒ አንተል ሙቀድዲሙ ወአንተል ሙአኽኺሩ ላኢላሀ ኢልላ አንተ»*

«አላህ ሆይ! ከአሁን በፊት የፈፀምኩትን፣ ወደፊትም የምፈፅመውን፣ በግልፅ የፈፀምኩትን፣ በሥውርም የፈፀምኩትን (ወንጀል ሁሉ) ማርልኝ:: ስህተቴንም፣ አንተ የምታውቀውን ጥፋቴንም ይቅር በለኝ:: የምታስቀድመውም የምታዘገይም አንተ ነህ:: ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም::» (ሙስሊም)

٥٩ - «اللَّهُمَّ أَعِنِّي عَلَىٰ ذِكْرِكَ، وَشُكْرِكَ، وَحُسْنِ عِبَادَتِكَ»

*59. «አልላሁምመ አኢንኒ አላ ዚክሪከ ወሹክሪከ ወሁስኒ ኢባደቲከ::»*

«አላህ ሆይ! አንተን ለማስታወስ፣ ለማመስገንና አምልኮህን ለማሳመር እርዳኝ::» (አቡዳውድ ናሳኢይ)

٦٠ - «اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ الْبُخْلِ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنَ الْجُبْنِ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ أَنْ أُرَدَّ إِلَىٰ أَرْذَلِ الْعُمُرِ، وَأَعُوذُ

بِكَ مِنْ فِتْنَةِ الدُّنْيَا وَعَذَابِ الْقَبْرِ »

*60. «አልሏሁም መ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ቡኽሊ ወአዑዙቢከ ሚን አን ኡረድደ ኢላ አርዘሊል ዑሙሪ ወአዑዙቢከ ሚን ፊትነቲድዱንያ ወዐዛቢል ቀብር»*

«አላህ ሆይ! ከስስት በአንተ እጠበቃለሁ:: ከፍርሃት በአንተ እጠበቃለሁ:: በዕድሜ በጣም ገፍቶ ከመጃጃት በአንተ እጠበቃ ለሁ:: ከዚህች ዓለም ፈተናና ከቀብር ውስጥ ቅጣት በአንተ እጠበቃለሁ::»

(ቡኻሪ)

٦١ - «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْجَنَّةَ وَأَعُوذُ بِكَ مِنَ النَّارِ »

*61. «አልሏሁም መ ኢንኒ አስአሉከል ጀንነተ ወአዑዙቢከ ሚን አንናር»*

«አላህ ሆይ! ጀንነትን እጠይቅሃለሁ:: ከእሳትም በአንተ እጠበቃለሁ::»(አቡዳውድ)

٦٢ - « اللَّهُمَّ بِعِلْمِكَ الْغَيْبَ وَقُدْرَتِكَ عَلَى الْخَلْقِ أَحْيِنِي مَا عَلِمْتَ الْحَيَاةَ

خيراً لِي وَتَوَفَّنِي إذا عَلِمْتَ الْوَفَاةَ خَيْراً لِي، اللَّهُمَّ إنِّي أَسْأَلُكَ خَشْيَتَكَ فِي الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ، وَأَسْأَلُكَ كَلِمَةَ الْحَقِّ فِي الرِّضَا وَالْغَضَبِ، وَأَسْأَلُكَ الْقَصْدَ فِي الْغِنَى وَالْفَقْرِ، وَأَسْأَلُكَ نَعِيماً لا يَنْفَدُ، وَأَسْأَلُكَ قُرَّةَ عَيْنٍ لَا تَنْقَطِعُ، وَأَسْأَلُكَ الرِّضَا بَعْدَ الْقَضَاءِ، وَأَسْأَلُكَ بَرْدَ الْعَيْشِ بَعْدَ الْمَوْتِ، وَأَسْأَلُكَ لَذَّةَ النَّظَرِ إلَىٰ وَجْهِكَ وَالشَّوْقَ إلَىٰ لِقَائِكَ فِي غَيْرِ ضَرَّاءَ مُضِرَّةٍ وَلَا فِتْنَةٍ مُضِلَّةٍ، اللَّهُمَّ زَيِّنَّا بِزِينَةِ الْإِيمَانِ وَاجْعَلْنَا هُدَاةً مُهْتَدِينَ»

*62. «አልላሁምመ ቢዒልሚከል ገይብ ወቁድረቲከ አለል ኸልቂ አህይኒ ማዐሊምተል ሃያተ ኸይረን ሊ ወተወፍፋኒ ኢዛ ዐሊምተል ወፋተ ኸይረን ሊ አልላሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ኸሽየተከ ፊል ገይቢ ወሸሸሃደቲ ወአስአሉከ ከሊመተል ሐቅ ፊ አርረዷ ወልገደቢ ወአስአሉከ አልቀስደ ፊል ጊና ወልፈቅር ወአስአሉከ ነዒመን ላ የንፈድ ወአስአሉከ ቁርረተ አይኒን ላ ተንቀጢእ ወአስአሉከ አርሪዷ ባእደል ቀዷእ ወአስአሉከ በርደል ዐይሺ በዕደል መውቲ ወአስአሉከ ለዝዘተን ነዘሪ ኢላ ወጅሂከ ወሸሸውቀ ኢላ ሊቃኢከ ፊ ገይሪ ደርራእ ሙዲርረቲን ወላ ፊትነቲን ሙዲልለቲን፣ አልላሁምመ ዘይንና ቢዚነቲል ኢማን ወጀአልና ሁዳተን ሙህተዲን»*

«አላህ ሆይ! በሩቅ ሚስጥር እውቀትህና በፍጡራን ላይ ባለህ ችሎት እማፀንሃለሁ:: ህይወት ለኔ መልካም መሆኑን ካወቅክ በህይወት አቆየኝ:: ሞት ለኔ መልካም እንደሆነ ካወቅክ ደግሞ ለህልፈት አብቃኝ:: አላህ ሆይ! በግልፅም በሥውርም አንተን እንድፈራ ታስችለኝ ዘንድ እለምንሃለሁ:: በእርካታም ሆነ በቁጣ ሰዓት እውነትን መናገርን እንድ ታስችለኝ እጠይቅሃለሁ:: ሐብት ኖሮኝም ሆነ ድሃ

በምሆንበት ወቅት ገንዘብን በሥርዓት የመጠቀም ችሎታን ትለግሰኝ ዘንድ እማፀንሃለሁ:: የማይነጥፍ ፀጋን እጠይቅሃለሁ:: የማይቋረጥ የዓይን ማረፊያን እለምንሃለሁ:: አንዳች ነገር ከደረሰብኝ በኋላ በፀጋ መቀበልን እማፀን ሃለሁ:: ከሞት በኋላ የተመቻቸ ኑሮን እለምንሃለሁ:: ፊትህን በማየት የሚገኘን እርካታ፣ ከባድ ጉዳት ወይም ለጥመት የሚያበቃ ፈተና ሳይደርስብኝ አንተን ለመገናኘት መጓጓትን እጠይቅሃለሁ:: አላህ ሆይ! በኢማን ጌጥ አስውበን:: የተቀኑና ሌሎችም መቀናት ምክንያት የሚሆኑ ሰዎች አድርገን::» (ነሳእይ እና አህመድ)

٦٣ - «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ يَا أَللهُ بِأَنَّكَ الْوَاحِدُ الأَحَدُ الصَّمَدُ الَّذِي لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ وَلَمْ يَكُنْ لَهُ كُفُواً أَحَدٌ، أَنْ تَغْفِرَ لِي ذُنُوبِي إِنَّكَ أَنْتَ الْغَفُورُ الرَّحِيمُ»

*63. «አልላሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ያ አልላህ ቢአንነከል ዋሂዱል አሀዱ አስሰመዱ አልለዚ*

*ለም የሊድ ወለም ዩለድ ወለም የኩን ለሁ ኩፍወን አሐዱን አንተግፊርሊ ዙኑቢ ኢንነከ አንተል ገፉሩ አልረሂም»*

«አላህ ሆይ! አንተ አንድና ብቸኛ (አምላክ) ነህ። ለሌሎች መመኪያና መጠጊያ ነህ። ያልወለድክ ያልተወለድክም አምላክ ነህ። ብጤ የለህም። ሐጢአቴን ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ። አንተ መሐሪ አዛኝ ነህና።» (ነሳአይና አህመድ)

٦٤ – «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ بِأَنَّ لَكَ الْحَمْدَ لَا إِلَـٰهَ إِلَّا أَنْتَ وَحْدَكَ لَا شَرِيكَ لَكَ، الْمَنَّانُ، يَا بَدِيعَ السَّمٰوَاتِ وَالْأَرْضِ يَا ذَا الْجَلَالِ وَالْإِكْرَامِ، يَا حَيُّ يَا قَيُّومُ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْجَنَّةَ وَأَعُوذُ بِكَ مِنَ النَّارِ»

*64. «አልኋሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ቢአንነ ለከል ሐምዱ ላኢላሀ ኢልላ አንተ ወሕደከ ላሸሪከ ለከ፣ አል መንናኑ፣ ያበዲዐስሰማዋቲ ወል አርዲ ያዘል ጀላሊ ወል ኢክራም፣*

*ያሐይዩያቀይዩም ኢንኒ አስአሉከል ጀንነተ ወአዑዙ ቢከ ሚነንናር»*

«አላህ ሆይ! ምስጋና ለአንተ ተገቢ ነው:: ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አንድ ነህ:: አጋር የለህም:: ለጋስ ነህ:: የሰማያትና የምድር ፈጣሪ የሆንከው አምላክ ሆይ! የልቅናና የልግስና ባለቤት የሆንከው አምላክ ሆይ! ህያውና በራስህ የተብቃቃህ የሆንከው አምላክ ሆይ! ጀንነትን እጠይቅሃለሁ:: ከእሳት በአንተ እጠበቃለሁ::» (አህለ ሱነን)

٦٥ - «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ بِأَنِّي أَشْهَدُ أَنَّكَ أَنْتَ اللهُ لَا إِلٰهَ إِلَّا أَنْتَ الأَحَدُ الصَّمَدُ الَّذِي لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ وَلَمْ يَكُنْ لَهُ كُفُواً أَحَدٌ»

*65. «አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ቢአንኒ አሽሐዱ አንነከ አንተልሏሁ ላኢላሀ ኢልላ አንተ አል-አሐዱ ለስሰመዱ አልለዚ ለም የሊድ ወለም ዩውለድ ወለም የኩን ለሁ ኩፉወን አሀድ»*

«አላህ ሆይ! መልካምን ሁሉ እማፀን ሃለሁ:: ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ እንደ ሌለ እመሰክራለሁ:: አንድ ነህ:: መመኪያና መጠጊያ ነህ:: አልወለድክም:: አልተወለድክም:: ብጤም የለህም::» (አቡዳውድ፣ ቲርሚዝይ፣ ኢብን ማጀህና አህመድ)

## 25. ሶላት ከተጠናቀቀ በኋላ የሚደረግ ዚክር

٦٦ - «أَسْتَغْفِرُ اللهَ (ثَلَاثًا) اللَّهُمَّ أَنْتَ السَّلَامُ، وَمِنْكَ السَّلَامُ، تَبَارَكْتَ يَا ذَا الْجَلَالِ وَالْإِكْرَامِ»

*66. «አስተግፊሩልላህ አልኋሁምመ አንተስሰላም፣ ወሚንከስሰላም፣ ተባረክተ ያዘልጃላሊ ወል ኢክራም»*

«አላህን ምህረትን እጠይቀዋለሁ::»- ሦስት ጊዜ::

«አላህ ሆይ! አንተ ሰላም ነህ:: ሰላም የሚመነጨው ከአንተ ነው::

የልዕልናና የልግስና ባለቤት የሆንከው አምላክ ሆይ! ረድኤተ ብዙ ነህ::»
(ሙስሊም)

٦٧ – «لَا إِلٰهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ، اللَّهُمَّ لَا مَانِعَ لِمَا أَعْطَيْتَ، وَلَا مُعْطِيَ لِمَا مَنَعْتَ، وَلَا يَنْفَعُ ذَا الْجَدِّ مِنْكَ الْجَدُّ»

*67. «ላኢላሃ ኢልለሏሁ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ፣ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር፣ አልሏሁምመ ላማኒዐ ሊማ አዕጦይተ፣ ወላ ሙዕጢ ሊማ መናዕተ፣ ወላ የንፈዑ ዘል ጀድዲ ሚንከል ጀድዲ»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አንድ ነው:: አጋር የለውም:: ንግሥና ለርሱ ብቻ ነው:: ምስጋናም ተገቢነቱ ለርሱ ነው:: እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው:: አላህ ሆይ! አንተ የለገስከውን ሰው

ከልካይ የለውም:: የነፈግከውን ደግሞ ሊሰጠው የሚችል የለም:: የክብር ባለቤት ከአንተ ዘንድ ክብሩ ቅንጣት አይፈይደ ውም::» (ቡኻሪ)

٦٨ – «لَا إِلٰهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ، وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ. لَا حَوْلَ وَلَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللهِ، لَا إِلٰهَ إِلَّا اللهُ، وَلَا نَعْبُدُ إِلَّا إِيَّاهُ، لَهُ النِّعْمَةُ وَلَهُ الْفَضْلُ وَلَهُ الثَّنَاءُ الْحَسَنُ، لَا إِلٰهَ إِلَّا اللهُ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ وَلَوْ كَرِهَ الْكَافِرُونَ»

*68. «ላኢላሃ ኢልለሏሀ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ፣ ለሁልሙልኩ ወለሁል ሐምዱ፣ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲይር፤ ላሐውላ ወላቁወተ ኢልላ ቢልላሀ፣ ላኢላሀ ኢልለሏሀ፣ ወላ ነዕቡዱ ኢልላ ኢይያሁ፣ ለሁንኒዕመቱ ወለሁል ፈድሉወለሁሰናኡል ሁስን፣ ላኢላሃ*

*ኢልለኋህ ሙኽሊሲይነ ለሁድዲይነ ወለው ከሪሃል ካፊሩውን»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አንድ ነው:: አጋር የለውም:: ንግሥና ለርሱ ብቻ ነው:: ምስጋናም ተገቢነቱ ለርሱ ብቻ ነው:: እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው:: ብልሃትም ኃይልም የለም- በአላህ ቢሆን እንጅ:: ከርሱ ውጭ ሌላን (ኃይል) አናመልክም:: ፀጋዎች ሁሉ የርሱ ናቸው:: መልካም ውዳሴ የሚገባውም እርሱ ነው:: ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: ለርሱ ሃይማኖት ፍፁም ቅኖችና ታማኞች ሆን:: ካህድያን ባይወዱም እንኳ::» (ሙስሊም)

٦٩ – «سُبْحَانَ اللهِ، وَالْحَمْدُ لِلَّهِ، وَاللهُ أَكْبَرُ (ثَلَاثاً وَثَلَاثِينَ) لَا إِلٰهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ»

*69. «ሱብሐነልኋህ፣ ወልሐምዱ ሊልኋህ፣ ወልኋሁ አክበር፣ ላኢላሃ ኢልለኋህ ወህደሁ*

*ላሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲይር»*
«ለአላህ ጥራት ይገባው:: ምስጋና ለአላህ ነው:: አላህ ከሁሉም የላቀ ነው፡ ሠላሣ ሶስት ጊዜ::

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አንድ ነው:: አጋር የለውም:: ንግሥና ለርሱ ነው:: ምስጋናም ተገቢነቱ ለርሱ ብቻ ነው:: እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው::» (ሙስሊም)

٧٠ - بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ﴿ قُلْ هُوَ ٱللَّهُ أَحَدٌ ۞ ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ ۞ لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ ۞ وَلَمْ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدٌۢ ﴾

*70. «ቁል ሁወልሏሁ አሐድ! አልሏሁስሰመድ! ለምየሊድ ወለም ዩውለድ! ወለም የኩን ለሁ ኩፉወን አሐድ::»*
«በል:-አላህ አንድ ነው:: አላህ የሁሉ መጠጊያ ነው:: አልወለደም አልተወለደምም:: ለርሱ አንድም ብጤ የለውም::»
(አል- ኢኽላስ 1-4)

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ﴿ قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلْفَلَقِ ۞ مِن

شَرِّ مَا خَلَقَ * وَمِن شَرِّ غَاسِقٍ إِذَا وَقَبَ

* وَمِن شَرِّ ٱلنَّفَّٰثَٰتِ فِى ٱلْعُقَدِ *

وَمِن شَرِّ حَاسِدٍ إِذَا حَسَدَ ﴾

«ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ፣ ሚን ሸርሪ ማኸለቅ፣ ወሚንሸርሪ ጋሲቂን ኢዛ ወቀብ፣ ወሚን ሸርሪንነፋሳቲ ፊል ዑቀድ፣ ወሚን ሸርሪ ሐሲዲን ኢዛ ሐሰድ።»

«በል፡- በተፍለቅላቂው ጎህ ጌታ እጠበቃለሁ። ከፈጠረው ፍጡር ሁሉ ክፋት፤ ከሌሊትም ክፋት፤ በጨለመ ጊዜ፤ በተቋጠሩ (ክሮች) ላይ ተፊዎች ከሆኑ (ደጋሚ) ሴቶችም ክፋት፤ ከምቀኛም ክፋት- በተመቀኘ ጊዜ(እጠበቃለሁ በል።)» (አል-ፈለቅ 1-5)

﴿ قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلنَّاسِ * مَلِكِ ٱلنَّاسِ

* إِلَٰهِ ٱلنَّاسِ * مِن شَرِّ ٱلْوَسْوَاسِ

ٱلْخَنَّاسِ * ٱلَّذِى يُوَسْوِسُ فِى صُدُورِ

ٱلنَّاسِ * مِنَ ٱلْجِنَّةِ وَٱلنَّاسِ ﴾

*«ቁል አዑዙ ቢረብቢንናስ፣ መሊኪንናስ፣ ኢላሂንናስ፣ ሚንሸርሪል ወስዋሲል ኸንናስ፣ አልለዚ ዩወስዊሱ ፊ ሱዱሪንናስ፣ ሚነልጂንነቲ ወንናስ»*

«በል:- በሰዎች ፈጣሪ እጠበቃለሁ:: የሰዎች ሁሉ ንጉሥ በሆነው:: ብቅ እልም ባይ ከሆነው ጉትጓች (ሰይጣን) ከፋት፣ ከዚያ በሰዎች ልቦች ውስጥ የሚጉተጉት ከሆነው፣ ከጋኔኖችም፣ ከሰዎችም (ሰይጣናት እጠበቃለሁ::)» (አል-ናስ፥ 1-6)

ከየሰላቶች በኋላ እነኝህን ሁሉ ማለት:: (አቡ ዳውድና ነሳእይ)

٧١ – ﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡحَيُّ ٱلۡقَيُّومُۚ
لَا تَأۡخُذُهُۥ سِنَةٞ وَلَا نَوۡمٞۚ لَّهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ
وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۗ مَن ذَا ٱلَّذِي يَشۡفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا
بِإِذۡنِهِۦۚ يَعۡلَمُ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَمَا خَلۡفَهُمۡۖ وَلَا
يُحِيطُونَ بِشَيۡءٖ مِّنۡ عِلۡمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَۚ وَسِعَ

كُرْسِيُّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَلَا يَـُٔودُهُۥ حِفْظُهُمَا ۚ وَهُوَ ٱلْعَلِىُّ ٱلْعَظِيمُ ﴿

*71. «አልሏሁ ላኢላሀ ኢልላ ሁወል ሐይዩል ቀይዩም፣ ላተእኹዙሁ ሲነቱን ወላ ነውም፣ ለሁ ማፊስሰማዋቲ ወማ ፊል አርድ፡ መንዘልለዚ የሽፉዑ ዒንደሁ ኢልላ ቢኢዝኒሂ ያዕለሙ ማበይነ አይዲይሂም ወማ ሀኸልፈሁም ወላ ዩሒጡና ቢሸይኢን ሚን ዒልሚሂ ኢልላ ቢማሻአ፣ ወሲዐ ኩርስዩሁስሰማዋቲ ወል አርድ ወላ የኡዱሁ ሒፍዙሁማ ወሁወል ዐልዩል ዐዚይም»*

«አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም:: ሕያውና ራሱን ቻይ ነው:: ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም:: በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው:: ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጅ የሚያማልድ ማን ነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላ ቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል:: በሻውም ነገር እንጅ ከእውቀቱ በምንም ነገር እያካ ብቡም:: (አያውቁም):: መንበሩ ሰማያት ንና ምድርን ሰፋ:: ጥበቃቸውውም:: እርሱም ከሁሉ በላይ ታላቅ ነው::» (አል-በቀራሀ ፥ 255)

ሶላቶችን ካጠናቀቁ በኋላ ወዲያ
ውኑ ይህንን ማለት:: (ነሳእይ)

٧٢ - «لَا إِلٰهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ يُحْيِي وَيُمِيتُ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ»

*72. «ላኢላሀ ኢልለኋሀ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ፣ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ዩሕዪ ወዩሚይቱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲይር»*
«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አንድ ነው:: አጋር የለውም:: ንግስና የርሱ ብቻ ነው:: ምስጋና ተገቢነቱ ለርሱ ብቻ ነው:: ህያው ያደርጋል:: ይገድላልም:: እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው::»- ከመግሪብና ከሱብሒ ሶላቶች በኋላ አስር አስር ጊዜ:: (ቲርሙዝይና አህመድ)

٧٣ - «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ عِلْماً نَافِعاً، ورِزْقاً طَيِّباً، وَعَمَلاً مُتَقَبَّلاً»

73. «አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ዒልመን ናፊዐ፣ ወሪዝቀን ጠይበን፣ ወዐመለን ሙተቀብቢላ»

«አላህ ሆይ! ጠቃሚ እውቀትን፥ መል ካም የሆነ ሲሳይን፥ ተቀባይነት ያለው ንም ተግባር እጠይቅሃለሁ::» የፈጅርን ሶላት ካጠናቀቁ በኋላ:: (ኢብን ማጀህና ሌሎችም)

## 26. የ«ሶላተል ኢስቲኻራ» (የምርጫ ሶላት ዱዓ)

ጃቢር ኢብን ዓብደላህ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የቁር አን ምዕራፎችን እንደሚያስተም ሩን ሁሉ በሁሉም ነገር በጉውን ለመምረጥ ፀሎት (ኢስቲኻራ) እናደርግ ዘንድ ያስተምሩን ነበር:: አንድ የሚያሳስበን ጉዳይ ሲገጥ መን ከፈርድ (ግዴታ) ሶላቶች ውጪ የሆኑ ሁለት ረከዓዎችን እንድንሰግድና ተከታዩን ዱዓ እንድናደርግ አሰተምረው ናል:-

٧٤ ــ « اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْتَخِيرُكَ بِعِلْمِكَ، وَأَسْتَقْدِرُكَ بِقُدْرَتِكَ، وَأَسْأَلُكَ مِنْ فَضْلِكَ الْعَظِيمِ، فَإِنَّكَ تَقْدِرُ وَلَا أَقْدِرُ، وَتَعْلَمُ، وَلَا أَعْلَمُ، وَأَنْتَ عَلَّامُ الْغُيُوبِ، اللَّهُمَّ إِنْ كُنْتَ تَعْلَمُ أَنَّ هَذَا الْأَمْرَ ـ وَيُسَمِّي حَاجَتَهُ ـ خَيْرٌ لِي فِي دِينِي وَمَعَاشِي وَعَاقِبَةِ أَمْرِي ـ أَوْ قَالَ: عَاجِلِهِ وَآجِلِهِ ـ فَاقْدُرْهُ لِي وَيَسِّرْهُ لِي ثُمَّ بَارِكْ لِي فِيهِ، وَإِنْ كُنْتَ تَعْلَمُ أَنَّ هَذَا الْأَمْرَ شَرٌّ لِي فِي دِينِي وَمَعَاشِي وَعَاقِبَةِ أَمْرِي ـ أَوْ قَالَ. عَاجِلِهِ وَآجِلِهِ ـ فَاصْرِفْهُ عَنِّي

وَاصْرِفْنِي عَنْهُ وَاقْدُرْ لِيَ الْخَيْرَ حَيْثُ كَانَ ثُمَّ أَرْضِنِي بِهِ»

*74. «አልሏሁምመ ኢንኒ አስተእኺሩከ ቢዒልሚከ፣ ወአስተቅዲሩከ ቢቁድረቲከ፣ ወአስአሉከ ሚንፈድሊከል ዐዚይም፣ ፈኢንነከ ተቅዲሩ ወላ አቅዲሩ! ወተዕለሙ ወላ አዕለሙ፣ ወአንተ ዐልላሙል ጉዩውብ፣ አልሏሀምመ ኢንኩንተ ተዕለሙ አንነ ሐዘል አምር ሀኸይሩን ሊ ፊ ዲይኒ ወማዐሺ ወዐቂበተ አምሪ ፈቀዲርሁ ሊ ወየስሲርሁ ሊ፣ ሱምመ ባሪክ ሊ ፊሂ፣ ወኢን ኩንተ ተዕለሙ አንነ ሐዘል አምር ሸርሩን ሊ ፊ ዲይኒ ወመዐሺይ ወዐቂበተ አምሪ ፈስሪፍሁ ዐንኒ ወስሪፍኒ ዐንሁ፣ ወቅዲር ሊየል ኸይረ ሐይሱ ካነ ሱምመ አረዲይኒ ቢሂ»*

«አላህ ሆይ! በእውቀትህ (በጉው ን ነገር) እንድትመርጥልኝ እጠይቅሀለሁ:: በችሎታህ እተማመናለሁ፣ (እናም በጉውን ነገር ምረጥልኝ::) ከታላቁ ትሩፋትህ እጠይቅሀለሁ:: አንተ እንጅ እኔ ወሳኝ አይደለሁም:: አንተ አዋቂ ነህ:: እኔ ግን መሀይም ነኝ:: አንተ ሩቅ ሚስጥርን አዋቂ ነህ:: አላህ ሆይ! ይህ ጉዳይ

(ጉዳዩን ይጥቀስ) ለሃይማኖቴ፣ ለህይወቴ ፥ እንዲሁም ለፍጻሜዬ መልካም ከሆነ ወስንልኝ:: አቅልልኝም:: ረድኤትህንም ሙላልኝ:: ለሃይማኖቴ፥ ለህይወቴ፥ ለፍ ጻሜዬም መልካም ካልሆነ ከኔ አስወ ግደው:: እኔንም ከርሱ አርቀኝ:: ምንም ይሁን ምን መልካምን ወስንልኝ:: በወሰ ንክልኝ የምረካ አድረግኝም::» (ቡኻሪ)

በእርግጥ አንድን ጉዳይ አላህ እንዲ መርጥለት ያደረገ፥ ሙእሚኖችን ያማከረ ከዚያም በውሳኔው የፀናና ያላወላወለ አይቆጭም:: አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿وَشَاوِرْهُمْ فِي الْأَمْرِ فَإِذَا عَزَمْتَ فَتَوَكَّلْ عَلَى اللَّهِ﴾

*«ወሻዊርሁም ፊልአምሪ ፊዒዛ ዓዘመተ ፈተወክል ዓለሏህ»*

«በነገሩ ሁሉ አማክራቸው:: ቁርጥ ሐሳብ ባደረግክም ጊዜ በአላህ ላይ ተመካ::» (አል-ዒምራን ፥ 159)

## 27. የጧትና የማታ ዚክሮች

الْحَمْدُ لِلَّهِ وحده، وَالصَّلَاةُ وَالسَّلَامُ

عَلَىٰ مَنْ لَا نَبِيَّ بَعْدَهُ

«አልሃምዱ ሊላሂ ዋህደሁ ወስሰላቱ ወስሰላሙ ዓላ መን ላ ነቢየ ባዕድ»

«ምስጋና ለአላህ ይገባው:: አንድ ነው :: የአላህ ሶላትና ሰላም በነብያት መቋጫ በሆኑት (ነብይ) ላይ ይውረድ::» (አቡዳውድ)

٧٥ - أَعُوذُ بِاللهِ مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ

﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلْحَيُّ ٱلْقَيُّومُ لَا تَأْخُذُهُۥ سِنَةٌ وَلَا نَوْمٌ لَّهُۥ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ مَن ذَا ٱلَّذِى يَشْفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذْنِهِۦ يَعْلَمُ مَا بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَمَا خَلْفَهُمْ وَلَا يُحِيطُونَ بِشَىْءٍ مِّنْ عِلْمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَ وَسِعَ كُرْسِيُّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَلَا يَـُٔودُهُۥ حِفْظُهُمَا وَهُوَ ٱلْعَلِىُّ ٱلْعَظِيمُ ﴾[1]

1. የአረብኛ አነባበን ገጽ 93 ላይ ይመልከቱ

75. «ከተረገመው ሰይጣን በአላህ እጠበቃለሁ:: አላህ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም:: ሕያው፣ ራሱን ቻይ ነው:: ማንገላጀትም እንቅልፍም አይዘውም:: በሰማያት ውስጥ ያለውና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው:: ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጂ የሚያማልድ ማን ነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና በኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል:: በሻውም ነገር እንጂ በእውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም፣ (አያውቁም):: መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ:: ጥበቃቸውም አያቅተውም:: እርሱም ከሁሉ በላይ ታላቅ ነው::» (አል-በቀራህ ፡ 255)

٧٦ - بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ﴿ قُلْ هُوَ ٱللَّهُ أَحَدٌ * ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ * لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ * وَلَمْ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدٌۢ ﴾[1]

76. «በል:- አላህ አንድ ነው:: አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው: አልወለደም፤ አልተወለደም:: ለርሱም አንድም ቢጤ የለውም::» (አል-ኢክላስ 1-4)

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ﴿ قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلْفَلَقِ * مِن

1. የአረብኛ አነባበብን ገጽ 90 ላይ ይመልከቱ

شَرِّ مَا خَلَقَ * وَمِن شَرِّ غَاسِقٍ إِذَا وَقَبَ
* وَمِن شَرِّ ٱلنَّفَّـٰثَـٰتِ فِى ٱلْعُقَدِ *
وَمِن شَرِّ حَاسِدٍ إِذَا حَسَدَ ﴾ [1]

«በል:- በተፍለቅላቂው ጌታ እጠበቃለሁ:: ከፈጠረው ፍጡር ሁሉ ከፋት:: ከሌሊትም ከፋት- በጨለመ ጊዜ! በተቋጠሩ (ክሮች) ላይ ተፊዎች ከሆኑት (ደጋሚ) ሴቶችም ከፋት! ከምቀኛም ከፋት፥ በተመቀኘ ጊዜ (እጠበቃለሁ) በል::» (አል-ፈለቅ፥1-5)

﴿ قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلنَّاسِ * مَلِكِ
ٱلنَّاسِ * إِلَـٰهِ ٱلنَّاسِ * مِن شَرِّ
ٱلْوَسْوَاسِ ٱلْخَنَّاسِ * ٱلَّذِى يُوَسْوِسُ
فِى صُدُورِ ٱلنَّاسِ * مِنَ ٱلْجِنَّةِ
وَٱلنَّاسِ ﴾ [2]

«በል:- በሰዎች ፈጣሪ እጠበቃለሁ:: የሰዎች ሁሉ ንጉሥ በሆነው:: የሰዎች

1. የአረብኛ አነባቡን ገጽ 91 ላይ ይመልከቱ
2. የአረብኛ አነባቡን ገጽ 92 ላይ ይመልከቱ

አምላክ በሆነው:: ብቅ እልም ባይ ከሆነው ጐትጓች (ሰይጣን) ከፋት:: ከዚያ በሰዎች ልቦች ውስጥ የሚጐተጉት ከሆነው:: ከጋኔኖችም ከሰዎችም (ሰይጣናት እጠበቃ ለሁ በል::)» (አል-ናስ ፥1-6) (አቡዳውድና ቲርሙዝይ)

٧٧- «أَصْبَحْنَا وَأَصْبَحَ الْمُلْكُ لِلَّهِ
وَالْحَمْدُ لِلَّهِ، لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا
شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ
عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ، رَبِّ أَسْأَلُكَ خَيْرَ
مَا فِي هَذَا الْيَومِ وَخَيْرَ مَا بَعْدَهُ وَأَعُوذُ
بِكَ مِنْ شَرِّ مَا فِي هَذَا الْيَوْمِ وَشَرِّ مَا
بَعْدَهُ، رَبِّ أَعُوذُ بِكَ مِنَ الْكَسَلِ، وَسُوءِ
الْكِبَرِ، رَبِّ أَعُوذُ بِكَ مِنْ عَذَابٍ فِي
النَّارِ وَعَذَابٍ فِي الْقَبْرِ»

*77. «አስባሕና ወአስበሐል ሙልኩ ሊልላሀ ወልሐምዱ ሊልላሀ ላኢላሀ ኢልለሏሀ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲይር፤ ረብቢ አስአሉከ ኸይረ ማፊ ሃዘል የውመ ወኸይረ ማ ባዕደሁ ወአዑዙ ቢከ ሚንሸርሪ ማፊ ሐዘል የውመ ወሸርሪ ማ በዕደሁ፣ ረብቢ አዑዙ ቢከ ሚነል ከሰሊ ወሱኢል ኪበር፣ ረብቢ አዑዙ ቢከ ሚን ዐዛቢን ፊንናር ወዐዛቢን ፊል ቀብር»*

«ማለዳ[1] ላይ ለመድረስ ነቅተናል:: በዚህ ሰዓት ሉዓላዊነት የዓለማት ጌታ የሆነው የአላህ ነው:: ምስጋና ለአላህ ነው:: ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አንድ ነው:: አጋር የለውም:: ሉዓላዊነት የርሱ ብቻ ነው:: ምስጋናም የርሱ ብቻ ነው:: እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው:: ጌታዬ ሆይ! የዚህን ቀንና የቀጣዩን (የሌሊቱን[2]) መልካም ነገር እጠይቅሃለሁ:: ከዚህ ቀንና ከቀጣዩ (ከሌሊቱ) ክፉ ነገር በአንተ እጠበቃለሁ:: አላህ ሆይ! ከስንፍናና

---

1.ሲመሽ:-«ምሽት ላይ...» ይበሉ::

2.ሲመሽ:-«የዚህን ለሌሊተና የቀጣዩን (የቀኑን).....» ይበሉ::

መጥፎ ከሆነ እርጅና (ከመጃጃት) በአንተ እጠበቃለሁ:: ጌታዬ ሆይ! ከእሳት ቅጣት ከቀብር ውስጥ ቅጣትም በአንተ እጠበቃለሁ::» (ሙስሊም)

٧٨- «اللَّهُمَّ بِكَ أَصْبَحْنَا، وَبِكَ أَمْسَيْنَا ، وَبِكَ نَحْيَا، وَبِكَ نَمُوتُ وَإِلَيْكَ النُّشُورُ»

*78. «አልሏሁምመ ቢክ አስበሕና ወቢክ አምሰይና፣ ወቢክ ነሕያ ወቢክ ነሙውት፣ ወኢለይንኑሹውር»*

«አላህ ሆይ! በአንተ ለዚህ ማለዳ በቅተናል:: በአንተም ለምሽት እንበቃለን[1]:: በአንተ ህያው ሆነናል:: በአንተም እንሞታለን:: መመለሻ ወደ አንተ ነው::» (ቲርሙዝይ)

٧٩- «اللَّهُمَّ أَنْتَ رَبِّي لَا إِلَٰهَ إِلَّا أَنْتَ، خَلَقْتَنِي وَأَنَا عَبْدُكَ، وَأَنَا عَلَىٰ عَهْدِكَ

1. ሲመሽ:- «በአንተ ለዚህ ምሽት በቅተናል:: በአንተም ለመማለድ እንበቃለን...» ይበሉ::

وَوَعْدِكَ مَا اسْتَطَعْتُ، أَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا صَنَعْتُ، أَبُوءُ لَكَ بِنِعْمَتِكَ عَلَيَّ، وَأَبُوءُ بِذَنْبِي فَاغْفِرْ لِي فَإِنَّهُ لَا يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلَّا أَنْتَ»

*79. «አልላሁምመ አንተ ረብቢ ላኢላሀ ኢልላ አንተ፣ኸለቅተኒ ወአነ ዐብዱከ ወአነ ዐላ ዐሕዲከ ወወዕዲከ መስተጠዕቱ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ማሰነዕቱ አቡኡ ለከ ቢኒዕመቲከ ዐለይየ ወአቡኡ ቢዘንቢ ፈግፊርሊ ፈኢንነሁ ላየግፊሩዝዙኑውበ ኢልላ አንተ»*

«አላህ ሆይ! አንተ አምላኬ ነህ:: ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: ፈጥረ ህኛል:: እኔ ባሪያህ ነኝ:: እኔ የቻልኩትን ያክል ያንተን ቃል ኪዳን ለመሙላት እሞክራለሁ:: ከሰራሁው ነገር ከከፉው በአንተ እጠበቃለሁ:: በኔ ላይ ለዋልከው ፀጋህ እውቅናን እሰጣለሁ:: ሐጢአቴንም እናዘዛለሁ:: ማረኝ:: ከአንተ ውጭ ሐጢአትን የሚምር የለም::» (ቡኻሪ)

٨٠- «اللَّهُمَّ إِنِّي أَصْبَحْتُ أُشْهِدُكَ

وأُشْـهِدُ حَمَـلَةَ عَرْشِكَ، وَمَلَائِكَتَكَ وجَمِيعَ خَلْقِـكَ، أَنَّكَ أَنْتَ اللهُ لَا إِلَـهَ إِلَّا أَنْتَ وَحْـدَكَ لَا شَرِيكَ لَكَ، وَأَنَّ مُحَمَّداً عَبْدُكَ وَرَسُولُكَ»

*80. «አልሏሁምመ ኢንኒ አስበሕቱ ኡሽሒዱከ ወኡሽሒዱ ሐመለተ ዐርሺከ፣ ወመላኢከተከ ወጀሚዓ ኸልቂከ፣ አንከ አንተልሏሁ ላኢላሃ ኢልላ አንተ ወሕደከ ላሸሪከ ለከ፣ ወአንነ ሙሐመደን ዐብዱከ ወረሱሉከ»*

«አንተንና ዙፋንህን የተሸከሙ (መላዕክትን) ሳስመሰክር አንግቻለሁ::[1] አንተ አላህ መሆንህንና ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ እንደሌለ+ አንድነትህን፣ አጋር እንደሌለህም፤ ሙሐመድም ባሪያህና መልዕክተኛህ መሆናቸውንም::»- አራት ጊዜ::(አቡዳውና ቡኻሪ)

---

1. በምሽት:- «አንግቻለሁ» በሚለው ምትክ «አምሽቻለሁ» የሚለውን ቃል ይጠቀሙ ::

٨١- «اللَّهُمَّ مَا أَصْبَحَ بِي مَنْ نِعْمَةٍ أَوْ بِأَحَدٍ مِنْ خَلْقِكَ فَمِنْكَ وَحْدَكَ لَا شَرِيكَ لَكَ، فَلَكَ الْحَمْدُ وَلَكَ الشُّكْرُ»

*81. «አልላሁምመ ማ አስበሃቢ ሚን ኒዕመቲን አው ቢ አሃዲን ሚን ኸልቂከ ፈሚንከ ወሕደከ ላሸሪከ ለክ፣ ፈለከል ሐምዱ ወለከሽሹክር»*

«አላህ ሆይ! በኔ ወይም ከፍጡራንህ በአንዱ ላይ ያነጋው[1] ፀጋ ከአንተና ከአንተ ብቻ የመነጨ ነው:: አጋር የለህም:: ምስጋናና ውዳሴ ይገባሃል::» (አቡዳውድና ነሳኢይ)

٨٢- «اللَّهُمَّ عَافِنِي فِي بَدَنِي، اللَّهُمَّ عَافِنِي فِي سَمْعِي، اللَّهُمَّ عَافِنِي فِي بَصَرِي، لَا إِلَـهَ إِلَّا أَنْتَ. اللَّهُـمَّ إِنِّي

1. በምሽት ወቅት :- «ያነጋው» የሚለውን «ያመሸው» በሚል ይተኩት::

أَعُوذُ بِكَ مِنَ الكُفْـرِ ، والْفَقْرِ ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ ، لَا إِلَـٰهَ إِلَّا أَنْتَ »

*82. «አልሏሁምመ ዓፊይኒ ፊ በደኒ፣ ለልሏሁምመ ዓፊይኒ ፊ ሰምዒ፣ አልሏሁምመ ዓፊይኒ ፊ በሰሪ፣ ላኢላሃ ኢልላ አንተ፣ አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ኩፍሪ ወልፈቅሪ ወአዑዙ ቢከ ሚን ዐዛቢል ቀብሪ ላኢላሀ ኢልላ አንተ»*

«አላህ ሆይ! አካሌን ጤናማ አድርግ ልኝ:: አላህ ሆይ! ጆሮዬን ጤናማ አድር ግልኝ:: አላህ ሆይ! ዓይኔን ጤናማ አድርግልኝ:: ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አላህ ሆይ! ከክህደትና ከድህነት በአንተ እጠበቃለሁ:: ከቀብር ቅጣትም በአንተ እጠበቃለሁ:: ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም::»- ሦስት ጊዜ::

(አቡዳውድ፣ አህመድና ነሳእይ)

٨٣- «حَسْبِيَ اللهُ لَا إِلَـٰهَ إِلَّا هُوَ عَلَيْهِ تَوَكَّلْتُ وَهُوَ رَبُّ الْعَرْشِ العَظِيمِ »

*83. «ሐስቢየልላሁ ላኢላሀ ኢልላሁዋ ዐለይሒ ተወክከልቱ ወሁዋ ረብቡል ዐርሺል ዐዚይም»*

«አላህ በቂዬ ነው:: ከርሱ ሌላ ሊመለክ የሚገባው ኃይል የለም:: በርሱ ተመካሁ:: እርሱ የታላቁ ዓርሽ ጌታ ነው::»- ሰባት ጊዜ:: (አቡዳውድ)

٨٤- «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْعَفْوَ وَالْعَافِيَةَ فِي الدُّنْيَا وَالْآخِرَةِ، اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْعَفْوَ وَالْعَافِيَةَ: فِي دِينِي وَدُنْيَايَ وَأَهْلِي، وَمَالِي، اللَّهُمَّ اسْتُرْ عَوْرَاتِي، وَآمِنْ رَوْعَاتِي، اللَّهُمَّ احْفَظْنِي مِنْ بَيْنِ يَدَيَّ، وَمِنْ خَلْفِي، وَعَنْ يَمِينِي، وَعَنْ شِمَالِي، وَمِنْ فَوْقِي، وَأَعُوذُ بِعَظَمَتِكَ أَنْ أُغْتَالَ مِنْ تَحْتِي»

*84. «አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከ አል-ዐፍወ፣ ወል ዐፊየተ ፊድዱንያ ወል አኺረህ፣ አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከል ዐፍወ ወል ዐፍየተ ፊዲኒ ወዱንያየ ወአህሊ ወማሊ አልሏሁምመ አስቱር ዐውረቲ ወአሚን ረውዐቲ፣ አልሏሁምመ ኢህፈዝኒ ሚን በይኒ የደይየ ወሚን ኸልፊ ወዐን የሚኒ ወዐን ሽማሊ ወሚንፈውቂ ወአዑዙ ቢዐዘመቲከ አን ኡግታለ ሚን ተሕቲ»*

«አላህ ሆይ! በዚህችም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ይቅርታንና ጤንነትን እጠይቅሃለሁ:: አላህ ሆይ! በሃይማኖቴ፣ በዚህች ዓለም ህይወቴም፣ በቤተሰቦቼም፣ በንብረቴም ደህንነትን እጠይቅሃለሁ:: አላህ ሆይ! ነውሬን ሸፍንልኝ:: አላህ ሆይ! ከፊት ለፊቴ፣ ከኋላዬም፣ ከቀኜም፣ ከግራዬም፣ ከበላዬም ጠብቀኝ:: ከበታቼም እንዳልጠቃ በአንተ እጠበቃለሁ::»

(አቡዳውድና ኢብን ማጃህ)

٨٥- « اللَّهُمَّ عَالِمَ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ فَاطِرَ السَّمٰوَاتِ وَالْأَرْضِ، رَبَّ كُلِّ شَيْءٍ وَمَلِيكَهُ، أَشْهَدُ أَنْ لَّا إِلَـٰهَ إِلَّا أَنْتَ، أَعُوذُ

بِكَ مِنْ شَرِّ نَفْسِي، وَمِنْ شَرِّ الشَّيْطَانِ وَشِرْكِهِ، وَأَنْ أَقْتَرِفَ عَلَىٰ نَفْسِي سُوءاً، أَوْ أَجُرَّهُ إِلَى مُسْلِمٍ»

*85. «አልሏሁምመ ዓሊመል ገይቢ ወሸሸሃደህ፣ ፋጢረሰሰማዋቲ ወል አርድ፣ ረብበ ኩልሊ ሸይኢን ወመሊኩህ፣ አሽሀዱ አንላኢላሃ ኢልላ አንተ፣ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ነፍሲ፣ ወሚን ሸርሪ ሸይጧኒ ወሽሪኪሂ፣ ወአን አቅተሪፍ ዐላ ነፍሲ ሱውአን አው አጁርረሁ ኢላ ሙስሊሚን»*

«ሩቅንም ቅርብንም የምታውቅ፣ የሰማያትና የምድር ፈጣሪ የሆንክ አላህ ሆይ! የሁሉም ነገር ጌታ ነህ:: የሁሉም ነገር የበላይ ተቆጣጣሪ ነህ:: ከአንተ ሌላ የሚመለክ ኃይል የለም:: ከነፍሴ ክፉ ነገር፣ ከሸይጣንና አጋሮቹ ተንኮል፣ በራሴ ወይም በአንድ ሙስሊም ላይ ክፉ ነገር እንዳልፈፅምም በአንተ እጠበቃለሁ::»

(ቲርሙዝይና አቡዳውድ)

٨٦- «بِسْمِ اللهِ الَّذِي لَا يَضُرُّ مَعَ اسْمِهِ شَيْءٌ فِي الْأَرْضِ وَلَا فِي السَّمَاءِ وَهُوَ

«السَّمِيعُ الْعَلِيمُ»

*86. «ቢስሚልላሂል ለዚ ላየዱርሩ መዐ ኢስሚሂ ሸይኡን ፊል አርዲ ወላ ፊስሰማኢ ወሁወስሰሚዑል ዓሊይም»*

«በአላህ ስም፤ እርሱ (አላህ) ከስሙ ጋር (በስሙ የተጠበቁትን) በሰማይም በምድርም ምንም ነገር አይጎዳቸውም:: እርሱ ሰሚም አዋቂም ነው::»- ሦስት ጊዜ: (አቡዳውድ፣ ቲርሙዝይ እና ኢብን ማጀህ:)

٨٧- «رَضِيتُ بِاللهِ رَبّاً، وَبِالْإِسْلَامِ دِيناً، وَبِمُحَمَّدٍ ﷺ نَبِيّاً»

*87. «ረዲይቱ ቢልላሂ ረብበን፣ ወቢል ኢስላሚ ዲነን፣ ወቢ ሙሐመዲን ኔቢየን»*

«በአላህ፣ አምላክነት - በኢስላም ሃይማኖትና በሙሐመድ ነብይነት ረክቻለሁ::»- ሦስት ጊዜ:: (አህመድ ፣ነሳእይ፣ኢብን ማጀህና ቲርሙዝይ)

٨٨- «يَا حَيُّ يَا قَيُّومُ بِرَحْمَتِكَ أَسْتَغِيثُ أَصْلِحْ لِي شَأْنِي كُلَّهُ وَلَا تَكِلْنِي إِلَىٰ نَفْسِي طَرْفَةَ عَيْنٍ»

*88. «ያሐይዩ ያቀይዩውም ቢረህመቲከ አስተጊይሱ፣ አስሊህ ሊ ሸእኒ ኩልሊሂ ወላ ተኪልኒ ኢላ ነፍሲ ጠርፈተ ዐይኒን»*

«አንተ ህያው የሆንክ አምላክ ሆይ! አንተ ራስክን የቻልክ አምላክ ሆይ! በእዝ ነትህ እታገዛለሁ:: ጉዳዩን ሁሉ የተስተ ካከለና መልካም አድርግልኝ:: ለቅፅ በት እንኳ እኔን ለራሴው ብቻ አትተዉኝ::»

(ሐኪም)

٨٩- «أَصْبَحْنَا وَأَصْبَحَ الْمُلْكُ لِلَّـهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ ، اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ خَيْرَ هَذَا الْيَوْمِ : فَتْحَهُ، وَنَصْرَهُ وَنُورَهُ، وَبَرَكَتَهُ، وَهُدَاهُ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا فِيهِ وَشَرِّ مَا بَعْدَهُ»

*89. «አስባሕና ወአስበሐል ሙልኩ ሊልላሂ ረብቢል ዐላሚን፣ አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ኸይረ ሐዘል የውም ፈትሐሁ፣ ወነስረሁ ወኑረሁ፣ ወበረከተሁ፣ ወሁዳሁ፣*

*ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ማፊሒ ወሸርሪ ማበዕደሁ»*

«ለመማለድ በቅተናል። በዚህ ሰዓት ልዕልና የዓለማት ጌታ ለሆነው አላህ ነው። አላህ ሆይ! የዚህን ቀን መልካም ነገር፣ ስኬቱን፣ ድሉንና ብርሃኑን፥ እንዲሁም ረድኤቱንና በዚህ ቀን ትክክለኛ ፍኖትን መጨበጥን እጠይቅሃለሁ። ከርሱና ከርሱ ቀጥሎ ከሚመጣው ጊዜ ከፉ ነገር በአንተ እጠበቃለሁ።»

(አቡዳውድ)

٩٠- «أَصْبَحْنَا عَلَىٰ فِطْرَةِ الإِسْلَامِ وعَلَىٰ كَلِمَةِ الإِخْلَاصِ، وَعَلَىٰ دِينِ نَبِيِّنَا مُحَمَّدٍ ﷺ، وَعَلَىٰ مِلَّةِ أَبِينَا إِبْرَاهِيمَ، حَنِيفاً مُسْلِماً وَمَا كَانَ مِنَ الْمُشْرِكِينَ»

*90. «አስባህና ዐላ ፊጥረቲል ኢስላም ወአላ ከሊመቲል ኢኽላስ ወዐላ ዲኒ ነቢይነ ሙሐምመዲን ሰልለላሁ አለይሂ ወሰለም ወዐላ ሚልለቲ አቢና ኢብራሂም፣ ሃኒፈን ሙስሊመን ወማ ካነ ሚነል ሙሽሪኪይን»*

«በኢስላማዊ ተፈጥሯችን፥ በመልካም ንግግር (ከሊመተል ኢኽላስ)፣ በነብያችን በሙሐመድ ሃይማኖት፣ ቀጥያለ ሙስሊም በነበረውና ከሙሽሪኮች ባልነበረው በአባታችን በኢብራሂም ጉዳና ላይ እንደ ፀናን አነጋን::» (አህመድ)

٩١- «سُبْحَانَ اللهِ وَبِحَمْدِهِ»

*91. «ሱብሃነ አልላሂ ወቢሐምዲሂ»*

«ለአላህ ጥራት ይገባው፤ ምስጋናም::»- መቶ ጊዜ:: (ሙስሊም)

٩٢- «لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ، وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ»

*92. «ላኢላሀ ኢልለ ሏሁ ወሀደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሃምዱ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር»*

ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አንድ ነው:: አጋር የለውም:: ንግሥና ለርሱ ብቻ ነው:: ምስጋናም ለርሱ ተገቢው

ነው:: እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው::»- አሥር ጊዜ ተካልተቻለ አንድ ጊዜ :: (አቡዳውድ፣ ኢብን ማጀህና አህመድ)

٩٣- «لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ، وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ»

*93. «ላኢላሃ ኢልለሏህ ወህደሁ ላሸሪክ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሃምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር»*

«ከአላህ ውጪ ሌላ አምላክ የለም:: አንድ ነው:: አጋር የለውም:: ንግሥና የርሱ ብቻ ነው:: ምስጋናም ተገቢው ነው:: እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው::»-ንጋት ላይ መቶ ጊዜ:: (ቡኻሪና ሙስሊም)

٩٤- «سُبْحَانَ اللهِ وَبِحَمْدِهِ : عَدَدَ خَلْقِهِ، وَرِضَا نَفْسِهِ، وَزِنَةَ عَرْشِهِ وَمِدَادَ كَلِمَاتِهِ»

*94. «ሱብሀነልላሂ ወቢሃምዲሂ አደደ ኸልቂሂ ወሪዳ ነፍሲሂ ወዚነተ አርሺሂ ወሚዳደ ከሊማቲሀ»*

«ለአላህ ጥራት ይገባው:: ምስጋናም:: በፍጡራኑ ቁጥር ልክ! ነፍሱ በወደደ ችው ልክ! በዙፋኑ ክብደት ልክ! በቃላቱ ብዛት ልክ::»- ሦስት ጊዜ+ ንጋት ላይ:: (ሙስሊም)

-٩٥ «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ عِلْماً نَافِعاً، وَرِزْقاً طَيِّباً، وَعَمَلاً مُتَقَبَّلاً»

*95. «አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ዒልመን ናፊዐን ወሪዝቀን ጠይበን ወዐመለን ሙተቀቢላ»*

«አላህ ሆይ! ጠቃሚ እውቀትን+ መልካ ም የሆነ ሲሳይን+ ተቀባይነት ያለውን ተግባርም እጠይቅሃለሁ::» - ንጋት ላይ:: (ኢብን ማጀህ)

-٩٦ «أَسْتَغْفِرُ اللهَ وَأَتُوبُ إِلَيْهِ»

*96. «አስተግፊሩልላሂ ወአቱቡ ኢለይሀ»*
«አላህን ምህረትን እማፀናለሁ:: ወደርሱ

በፀፀት እመለሳለሁ::» -ብቀን መቶ ጊዜ:: (ቡኻሪና ሙስሊም)

-٩٧ «أَعُوذُ بِكَلِمَاتِ اللهِ التَّامَّاتِ مِنْ شَرِّ مَا خَلَقَ»

*97. «አዑዙ ቢከሊማቲልላሂትታማቲ ሚንሸሪ ማኸለቅ»*

«ከፍጡራን ተንኮል ምሉዕ በሆኑት የአላህ ቃላት እጠበቃለሁ::» -ምሽት ላይ ሦስት ጊዜ:: (አህመድና ነሳኢይ)

-٩٨ «اللَّهُمَّ صَلِّ وَسَلِّمْ عَلَىٰ نَبِيِّنَا مُحَمَّدٍ»

*98. «አልሏሁምመ ሶልሊ ወሰሊም ዐላ ነቢይና ሙሃምመዲን»*

«አላህ ሆይ! በነብዩ ላይ ሰላምታ አውርድ:: ሰላም አስፍንም::»- አሥር ጊዜ (ጠበራኒ)

## 28. ከመኝታ በፊት የሚባሉ ዚክሮች

99\. ነብዩ(ሶ.ዐ.ወ) ዘወትር ከመተኛታቸው በፊት ሁለት መዳፎቻቸውን በማጋጠም ከላያቸው ላይ ትፍ ትፍ ይሉባቸዋል:: ከዚያም የሚከተሉትን ያነባሉ:-

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ﴿قُلۡ هُوَ ٱللَّهُ أَحَدٌ ۞ ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ ۞ لَمۡ يَلِدۡ وَلَمۡ يُولَدۡ ۞ وَلَمۡ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدُۢ﴾[1]

«በል:- እርሱ አላህ አንድ ነው:: አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው:: አልወለደም:: አልተወለደም:: ለርሱም አንድም ቢጤ የለውም::» (አል-አኽላስ 1-4)

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ﴿قُلۡ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلۡفَلَقِ ۞ مِن شَرِّ مَا خَلَقَ ۞ وَمِن شَرِّ غَاسِقٍ إِذَا وَقَبَ ۞ وَمِن شَرِّ ٱلنَّفَّٰثَٰتِ فِي ٱلۡعُقَدِ ۞ وَمِن شَرِّ حَاسِدٍ إِذَا حَسَدَ﴾[2]

---

1 የአረብኛ-[illegible] ገጽ [illegible] ላይ ይመልከቱ

2 የአረብኛ አነባቡን ገጽ 91 ላይ ይመልከቱ

«በል:- በተፍለቅላቂው ጎህ ጌታ እጠበቃለሁ:: ከፈጠረው ፍጡር ሁሉ ክፋት:: ከሌሊትም ክፋት- በጨለመ ጊዜ:: በተቋጠሩ (ክሮች) ላይ ተፊዎች ከሆኑት (ደጋሚ) ሴቶችም ክፋት:: ከምቀኛም ክፋት- በተመቀኘ ጊዜ (እጠበቃለሁ በል::)» (አል-ፈለቅ 1-5)

﴿ قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلنَّاسِ ۞ مَلِكِ ٱلنَّاسِ ۞ إِلَٰهِ ٱلنَّاسِ ۞ مِن شَرِّ ٱلْوَسْوَاسِ ٱلْخَنَّاسِ ۞ ٱلَّذِى يُوَسْوِسُ فِى صُدُورِ ٱلنَّاسِ ۞ مِنَ ٱلْجِنَّةِ وَٱلنَّاسِ ﴾[1]

«በል:- በሰዎች ፈጣሪ እጠበቃለሁ:: የሰዎች ሁሉ ንጉሥ በሆነው:: የሰዎች አምላክ በሆነው:: ብቅ እልም ባይ ከሆነው ጉትጓች (ሰይጣን) ክፋት:: ከዚያም በሰዎች ልቦች ውስጥ የሚጉተጉት ከሆነው:: ከጋኔኖችም ከሰዎችም(ሰይጣናት እጠበቃለሁ በል::)» (አል-ናስ 1-6)

---

1. [illegible]

በመቀጠልም በመዳፎቻቸው ከእነ ላቸው የቻሉትን ያክል ያብሱ ነበር:: ከራሳቸው በመጀመርያ ፊታቸውንና በፊታቸው በኩል ያሉ የአካል ክፍሎቻቸውን ይዳብሳሉ :: ከዚያም ሌሎችን የአካል ክፍሎቻቸውን:: ይህንኑ ሦስት ጊዜ በመደጋገም ይፈጽማሉ:: (ቡኻሪና ሙስሊም)

١٠٠- ﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡحَيُّ ٱلۡقَيُّومُۚ لَا تَأۡخُذُهُۥ سِنَةٞ وَلَا نَوۡمٞۚ لَّهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۗ مَن ذَا ٱلَّذِي يَشۡفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذۡنِهِۦۚ يَعۡلَمُ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَمَا خَلۡفَهُمۡۖ وَلَا يُحِيطُونَ بِشَيۡءٖ مِّنۡ عِلۡمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَۚ وَسِعَ كُرۡسِيُّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَۖ وَلَا يَـُٔودُهُۥ حِفۡظُهُمَاۚ وَهُوَ ٱلۡعَلِيُّ ٱلۡعَظِيمُ ﴾[1]

100. «አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም:: ሕያው ራሱን ቻይ ነው::

---

1. የአረብኛ አነባቡን ገጽ 93 ላይ ይመልከቱ

ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም::
በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው
ሁሉ የርሱ ብቻ ነው:: ያ እርሱ ዘንድ
በፈቃዱ ቢሆን እንጅ የሚያማልድ ማን
ነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና
ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል::
በሻውም ነገር እንጅ ከእውቀቱ በምንም
ነገር አያካብቡም+ (አያውቁም):: መንበሩ
ሰማያትንና ምድርን ሰፋ:: ጥበቃቸውም
አያቅተውም:: እርሱም የሁሉ የበላይ
ታላቅ ነው::» (አል-በቀራህ+ 255) (ቡኻሪ)

١٠١- ﴿ ءَامَنَ ٱلرَّسُولُ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيۡهِ
مِن رَّبِّهِۦ وَٱلۡمُؤۡمِنُونَۚ كُلٌّ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَمَلَـٰٓئِكَتِهِۦ
وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ لَا نُفَرِّقُ بَيۡنَ أَحَدٖ مِّن
رُّسُلِهِۦۚ وَقَالُواْ سَمِعۡنَا وَأَطَعۡنَاۖ غُفۡرَانَكَ
رَبَّنَا وَإِلَيۡكَ ٱلۡمَصِيرُ * لَا يُكَلِّفُ ٱللَّهُ
نَفۡسًا إِلَّا وُسۡعَهَاۚ لَهَا مَا كَسَبَتۡ وَعَلَيۡهَا مَا

ٱكْتَسَبَتْ ۗ رَبَّنَا لَا تُؤَاخِذْنَآ إِن نَّسِينَآ أَوْ
أَخْطَأْنَا ۚ رَبَّنَا وَلَا تَحْمِلْ عَلَيْنَآ إِصْرًا
كَمَا حَمَلْتَهُۥ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِنَا ۚ رَبَّنَا
وَلَا تُحَمِّلْنَا مَا لَا طَاقَةَ لَنَا بِهِۦ ۖ وَٱعْفُ عَنَّا
وَٱغْفِرْ لَنَا وَٱرْحَمْنَآ ۚ أَنتَ مَوْلَىٰنَا فَٱنصُرْنَا
عَلَى ٱلْقَوْمِ ٱلْكَٰفِرِينَ ۞

*101. «አመነርረሱሉ ቢማ ኡንዚለ ኢለይሂ ሚንረቢሂ ወልሙእሚኑን ኩሉን አመነ ቢልላሂ ወመላኢከቲሂ ወኩቱቢሂ ወሩሱሊሂ ላኑፈሪቁ በይነ አሐዲን ሚን ሩሱሊሀ ወቃሉ ሰሚእና ወአጠእና ጉፍራነከ ረብበና ወኢለይከል መሲር! ላዩከሊፉልላሁ ነፍሰን ኢልላ ውስአሃ ለሃ ማከሰበት ወዐለይሃ መክተሰበት ረብበና ላቱአኺዝና ኢንነሲና አው አኽጠእና ረብበና ወላ ተህሚል ዐለይና ኢስረን ከማ ሐመልተሁ አለልለዚይነ ሚን ቀብሊና ረብበና ወላ ቱሐምሚልና ማላጣቀተ ለና ቢሂ ወዕፉ አና ወግፊር ለና ወርሃምና አንተ መውላና ፈንሱርና አለል ቀውሚል ካፊሪን »*

«መልዕክተኛው ከጌታው ወደርሱ በተወረደው አመነ። ምእምኖችም (እንደ ዚሁ)፤ ሁሉም በአላህም፣ በመላዕክቱም፣ በመጽሐፍቱም፣በመልዕክተኞችም ከመልዕ ክተኞቹ በአንድም መካከል አንለይም (የሚሉ ሲሆኑ) አመኑ። ሰማን፤ ታዘዝ ንም። ጌታችን ሆይ! ምህረትህን (እንሻ ለን)። መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው። አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገ ድዳትም፤ ለርሷ የሰራችው አላት በርሷም ላይ ያፈራችው(ኃጢያት) አለባት። (በሉ):- ጌታችን ሆይ! ብንረሳ፣ ወይም ብንስት አተያዘን፤ (አትቅጣን)፤ ጌታችን ሆይ!! ከባድ ሸክምን ከኛ በፊት በነበሩት ላይ እንደጫንከው በእኛ ላይ አትጫንብን፤ ጌታችን ሆይ! ለእኛም በእርሱ ችሎታ የሌለንን ነገር አታሸከመን፤ ከኛም ይቅርታ አድርግ፤ ለኛም ምህረት አድር ግ፤ እዘንልንም፤ ዋቢያችን አንተ ነህና፤ በከሃዲዎች ህዝቦች ላይም እርዳን።» (አል-በቀራህ፣ 285-286) (ሙስሊም)

١٠٢- «بِاسْمِكَ رَبِّي وَضَعْتُ جَنْبِي،
وبِكَ أَرْفَعُهُ، فَإِنْ أَمْسَكْتَ نَفْسِي فَارْحَمْهَا،

وإنْ أَرْسَلْتَهَا فَاحْفَظْهَا، بِمَا تَحْفَظُ بِهِ عِبَادَكَ الصَّالِحِينَ»

*102. «ቢስሚከ ረቢ ወዳእቱ ጀንቢ ወቢከ አርፈዑሁ ኢን አምሰክተ ነፍሲ ፈርሐምሃ ወኢን አርሰልተሃ ፈህፈዝሃ ቢማ ተህፈዝ ቢሂ ኢባደከ አስሳሊሂን»*

«ጌታዬ ሆይ! በስምህ ጎኔን አሳርፈ ያለሁ:: በስምህም እነሳዋለሁ:: ነፍሴን በዚያው ካስቀራሀት እዘንላት:: ከላከካት ደግሞ መልካም ባሮችህን በምትጠ ብቅበት (ስልትህ) ጠብቃት::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

١٠٣- «اللَّهُمَّ إنَّكَ خَلَقْتَ نَفْسِي وَأَنْتَ تَوَفَّاهَا، لَكَ مَمَاتُهَا وَمَحْيَاهَا، إنْ أَحْيَيْتَهَا فَاحْفَظْهَا، وَإنْ أَمَتَّهَا فَاغْفِرْ لَهَا. اللَّهُمَّ إنِّي أَسْأَلُكَ الْعَافِيَةَ»

*103. «አልሏሁምመ ኢንነከ ኸለቅተ ነፍሲ ወአንተ ተወፋሃ ለከ መማቱሃ ወመህያሃ ኢን*

*አህየይተሃ ፈህፈዝሃ ወኢን አመትተሃ ፈግፈር ለሃ አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከል ዐፊያህ»*

«አላህ ሆይ! ነፍሴን ፈጥረሃታል። የምትገድላትም አንተው ነህ። ሞቷም ህይወቷም ላንተ ነው። ህያው ካደረግካት ጠብቃት። ከገደልካት ደግሞ ምህረትህን ለግሳት። አላህ ሆይ! ጤንነትን እጠይቅ ሃለሁ።» (ሙስሊምና አህመድ)

١٠٤- «اللَّهُمَّ قِنِي عَذَابَكَ يَوْمَ تَبْعَثُ عِبَادَكَ»

*104. «አልሏሁምመ ቂኒ አዛበከ የውመ ተብአሱ ዒባደከ»*

«አላህ ሆይ! ባሮችህን በምት ቀስቅስበት ወቅት ከቅጣትህ ጠብቀኝ።» (አቡዳውድ)

١٠٥- «بِاسْمِكَ اللَّهُمَّ أَمُوتُ وأَحْيَا»

*105. «ቢስሚከልሏሁምመ አሙቱ ወአህያ»*

«አላህ ሆይ! በስምህ እሞታለሁ! ነፍስም እዘራለሁ።» (ቡኻሪና ሙስሊም)

١٠٦- «سُبْحَانَ اللهِ (ثَلاثاً وثَلاثِينَ) وَالْحَمْدُ لِلهِ (ثَلاثاً وثَلاثِينَ) واللهُ أَكْبَرُ (اربَعاً وثَلاثِينَ)»

*106. «ሱብሐነልላሂ ወልሃምዱ ሊልላሂ ወልላሁ አክበር»*

«አላህ ሆይ! ጥራት ይገባህ» ሠላሣ ሶስት ጊዜ! «ለአላህ ምስጋና ይገባው» ሠላሣ ሶስት ጊዜ! «አላህ ከሁሉም የላቀ ነው» ሠላሣ ሶስት ጊዜ :: (ቡኻሪና ሙስሊም)

١٠٧- «اللَّهُمَّ رَبَّ السَّمٰواتِ السَّبْعِ ورَبَّ الْعَرْشِ الْعَظِيمِ، رَبَّنَا وَرَبَّ كُلِّ شَيْءٍ، فَالِقَ الْحَبِّ وَالنَّوَى، وَمُنْزِلَ التَّوْرَاةِ وَالْإِنْجِيلِ، وَالْفُرْقَانِ، أَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ كُلِّ شَيْءٍ أنتَ آخِذٌ بِنَاصِيَتِهِ.

اللَّهُمَّ أَنْتَ الْأَوَّلُ فَلَيْسَ قَبْلَكَ شَيْءٌ، وأَنْتَ الْآخِرُ فَلَيْسَ بَعْدَكَ شَيْءٌ، وَأَنْتَ

الظَّـاهِرُ فَلَيْسَ فَوْقَـكَ شَيْءٌ، وَأَنْتَ الْبَاطِنُ فَلَيْسَ دُونَكَ شَيْءٌ، اقْضِ عَنَّا الدَّيْنَ وَأَغْنِنَا مِنْ الْفَقْرِ»

*107. «አልሏሁምመ ረብበስሰማዋቲስ ሰብዒ ወረብበል ዐርሺል ዐዚም ረብበና ወረብበ ኩልለ ሸይኢን ፋሊቀል ሐቢ ወንነዋ ወሙንዚላት ተውራተ ወልኢንጂሊ ወልፉርቃኒ አዑዙቢከ ሚን ሸርሪ ኩልሊ ሸይኢን አንተ አኺዙን ቢናሲየቲሂ አልላሁምመ አንተል አወሉ ፈለይሰ ቀብለከ ሸይኡን ወአንተል አኺሩ ፈለይሰ ባዕደከ ሸይኡን ወአንተዝዛሂሩ ፈለይሰ ፈውቀከ ሸይኡን ወአንተል ባጢኑ ፈለይሰ ዱነከ ሸይኡን አቅዲ ዐንና ደይነ ወአግኒና ሚነልፈቅሪ»*

«የሰባቱ ሰማያት አምላክ፥ የታላቁ ዓርሽም አምላክ የሆንከው አላህ ሆይ! አምላካችን፣ የሁሉም ነገር አምላክ፣ ፍሬዎችን የምትፈለቅቅ፣ ተውራትንና ኢንጂልን፣ ፉርቃንንም ያወረድክ የሆንክ አላህ ሆይ! ከሁሉም ነገር ክፋት በአንተ እጠበቃለሁ:: ሁሉንም ነገር መቆጣጠር

ትችላለህ። አላህ ሆይ! አንተ የመጀመሪያው ነህ። ከአንተ በፊት ምንም ነገር የለም። የመጨረሻውም ነህ። ከአንተ በኋላ ምንም ነገር አይኖርም። አንተ ግልፅ ነህ። ከአንተ በላይ ምንም ነገር የለም። ድብቅ ነህ ። ከአንተውጭም ምንም ነገር የለም። እዳችንን አስወግድልን። ከድህነት ገላግለህ ከብረትን ለግሰን።» (ሙስሊም)

١٠٨- «الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي أَطْعَمَنَا وسَقَانَا، وَكَفَانَا، وَآوَانَا، فَكَمْ مِمَّنْ لا كَافِيَ لَهُ وَلَا مُؤْوِيَ»

*108. «አልሐምዱ ሊልላሂ አልለዚ አጥአመና ወሰቃና ወከፋና ወአዋና ፈከም ሚምመን ላ ካፊየ ለሁ ወላ ሙእዊየ»*

«ላበላንና ላጠጣን፣ ለተንከባከበንና ላስጠጋን አላህ ምስጋና ይገባው። ተንከባካቢና አስጠጊ የሌላቸው ስንት ሰዎች አሉ!» (ሙስሊም)

١٠٩- «اللَّهُمَّ عَالِمَ الْغَيْبِ والشَّهَادِةِ

فاطِرَ السَّمٰوَاتِ وَالأَرْضِ، رَبَّ كُلِّ شَيْءٍ
وَمَلِيكَهُ، أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَٰهَ إِلَّا أَنْتَ،
أَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ نَفْسِي، وَمِنْ شَرِّ
الشَّيْطَانِ وَشِرْكِهِ، وَأَنْ أَقْتَرِفَ عَلَىٰ
نَفْسِي سُوءاً، أَوْ أَجُرَّهُ إِلَىٰ مُسْلِمٍ»

*109. «አልሏሁምመ ዓሊመል ገይቢ ወሸሸሃደቲ ፋጢረሰሰማዋቲ ወልአረዲ ረብበ ኩልለ ሸይኢን ወመሊከሁ አሽሃዱ አንላኢላሀ ኢልላ አንተ አዑዙቢከ ሚን ሸርሪ ነፍሲ ወሚን ሸርሪ ሸሸይጣኒ ወሺርኪሂ ወአን አቅተሪፍ ዐላ ነፍሲ ሱአን አው አጁርረሁ ኢላ ሙስሊም»*

«ሩቅንም ቅርብንም አዋቂ፥ የሰማያትና የምድር ፈጣሪ፥ የሁሉም ነገር አምላክና ገዥ የሆንከው አላህ ሆይ! ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ:: ከነፍሴ ተንኮል፥ ከሸይጧንና ከአጋሮቹ ተንኮልም፥ በራሴ

ወይም በሙስሊሞች ላይ መጥፎ ከመፈፀ
ምም በአንተ እጠበቃለሁ።»
(አቡዳውድና ቲርሙዝይ)

*110.* «አል-ሰጅደህ» እና «አል-ሙልክ» ምዕራፎችን ያንብቡ። (ቲርሙዝይና ነሳእይ)

١١١- «اللَّهُمَّ أَسْلَمْتُ نَفْسِي إِلَيْكَ، وَفَوَّضْتُ أَمْرِي إِلَيْكَ، وَوَجَّهْتُ وَجْهِي إِلَيْكَ، وَأَلْجَأْتُ ظَهْرِي إِلَيْكَ، رَغْبَةً وَرَهْبَةً إِلَيْكَ، لَا مَلْجَأَ وَلَا مَنْجَا مِنْكَ إِلَّا إِلَيْكَ، آمَنْتُ بِكِتَابِكَ الَّذِي أَنْزَلْتَ وَبِنَبِيِّكَ الَّذِي أَرْسَلْتَ»

*111. «አልሏሁምመ አስለምቱ ነፍሲ ኢለይከ ወፈውወድቱ አምሪ ኢለይከ ወወጀጀህቱ ወጂሂ ኢለይከ ወአልጀእቱ ዟህሪ ኢለይከ ረግበተን ወረህበተን ኢለይከ ላመልጀአ ወላ መንጃ ሚንከ ኢልላ ኢለይከ አመንቱ*

*ቢኪታቢከልለዚ አንዘልተ ወቢ ነቢይከልለዚ አርሰልተ »*

«አላህ ሆይ! ነፍሴን ለአንተ አስረክቢያለሁ:: ጉዳዩን ሁሉ ወደ አንተ አስጠግቻለሁ:: ፊቴን ወደ አንተ አዙሪ ያለሁ:: ጀርባዬን ወደ አንተ መልሻለሁ:: (እርካታህን ለማግኘት) በመጓጓት! (ቁጣህን) በመፍራት:: መመለሻም! ከአንተ (ከቅጣትህ) ነፃ መውጫም ወደአንተ ከመመለስ ውጭ ሌላ መንገድ የለም :: ባወረድከው ኪታብ፣ በላከው ነብይም አምኛለሁ::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

## 29. ሌሊት ነቅተው የመኝታ አቅጣጫዎን ሲቀይሩ የሚሉት ዱዓ

١١٢- «لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ الْوَاحِدُ الْقَهَّارُ، رَبُّ السَّمٰوَاتِ وَالْأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا الْعَزِيزُ الْغَفَّارُ»

*112. «ላኢላሀ ኢ.ለልላሁል ዋሒዱል ቀሀሃሩ ረበቡስሰማዋቲ ወልአርዲ ወማ በይነሁመል ዐዚዙል ገፍፋር»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። አንድና ኃያል ነው። የሰማያትና የምድር፣ በመካከላቸው ያሉ ነገሮችም አምላክ። አሸናፊና መሀሪ።» (ሐኪምና ነሳእይ)

**30. ሲቢት በድንገት (በድንጋጤ) ሲባንኑ ወይም ብቸኝነት ሲሰማዎ የሚሉት ዱዓ**

١١٣ - «أَعُوذُ بِكَلِمَاتِ اللهِ التَّامَّاتِ مِنْ غَضَبِهِ وَعِقَـابِهِ، وَشَـرِّ عِبَـادِهِ، وَمِـنْ هَمَزَاتِ الشَّيَاطِينِ وَأَنْ يَحْضُرُونِ»

*113. «አዑዙ ቢከሊማቲልላሃትታማቲ ሚን ገደቢሂ ወኢቃቢሂ ወሸርሪ ኢባዲሂ ወሚን ሐመዛቲሽሽያጢይኒ ወአን የሀዱሩን»*

«ምሉዕ በሆኑት የአላህ ቃላት፦ ከቁጣው ከቅጣቱ፣ ከባሪያዎቹ ተንኮል

እንዲሁም ከሰይጣናት ጉትጐታና ቀረቤታ እጠብቃለሁ::» (አቡዳውድና ቲርሙዝይ)

## 31. ሕልምና ቅብዥር ሲመለከቱ የሚሉት ዱዓ

*114.* በግራም በኩል ይተንፍሱ- ሦስት ጊዜ:: (ሙስሊም)

«ከሸይጧንና ካዩት ነገር ክፋት በአላህ ይጠበቁ::»(*አዑዙ ቢልላሂ ሚነሽሸይጧኒር ረጂም*) - ሦስት ጊዜ:: (ሙስሊም)

«ያዩትን ለማንም አይናገሩ::» (ሙስሊም)

«የመኝታ አቅጣጫ ይቀይሩ::» (ሙስሊም)

*115.* «ከፈለጉ ተነስተው ይስገዱ::» (ሙስሊም)

## 32. የዊትር ቁኑት ዱዓ

١١٦- «اللَّهُمَّ اهْدِنِي فِيمَنْ هَدَيْتَ، وَعَافِنِي فِيمَنْ عَافَيْتَ، وَتَوَلَّنِي فِيمَنْ

تَوَلَّيْتَ، وَبَارِكْ لِي فِيمَا أَعْطَيْتَ، وَقِنِي شَرَّ مَا قَضَيْتَ، فَإِنَّكَ تَقْضِي وَلَا يُقْضَىٰ عَلَيْكَ، إِنَّهُ لَا يَذِلُّ مَنْ وَالَيْتَ، [وَلَا يَعِزُّ مَنْ عَادَيْتَ]، تَبَارَكْتَ رَبَّنَا وَتَعَالَيْتَ»

*116. «አልሏሁምመህዲኒ ፊይመን ሃደይተ ወአፊኒ ፊይመን ዓፈይተ ወተወለኒ ፊይመን ተወለይተ ወባሪክ ሊ ፊይማ አእጠይተ ወቂኒ ሸርረ ማቀደይተ ፊኢንነከ ተቅዲ ወላ ዩቅዳ አለይከ ኢንነሁ ላየዚልሉ መን ዋለይተ ወላ የኢዝዙ መን አደይተ ተባረክተ ረብበና ወተአለይተ»*

አላህ ሆይ! ሌሎችን እንዳቀናኸው እኔንም አቅናኝ:: ለሌሎች ጤና እንደሰጠኸው ለእኔም ስጠኝ:: ለሌሎች ዋቢ እንደሆንክ ለኔም ዋቢ ሁነኝ:: በሰጠኸኝ (ፀጋ) ረድኤትህን ጨምርልኝ:: ከወሰንከው ክፉ ነገር ጠብቀኝ:: አንተ ትወስናለህ:: በአንተ ላይ አይወሰንብህም:: አንተ የተወዳጀኸው አይዋረድም:: አንተ ጠላት የሆንከው ክብር አይጎናፀፍም:: የተቀደስክና ልዑል ነህ::(አስሐበ ሱነን አራቱም፣

አህመድ፣ ዳረሚይ፣ ሐኪምና በይሐቂይ)

١١٧- «اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِرِضَاكَ مِنْ سَخَطِكَ، وَبِمُعَافَاتِكَ مِنْ عُقُوبَتِكَ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْكَ، لَا أُحْصِي ثَنَاءً عَلَيْكَ، أَنْتَ كَمَا أَثْنَيْتَ عَلَىٰ نَفْسِكَ»

*117. «አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢሪዳከ ሚን ሰኸጢከ ወቢሙአፋቲከ ሚን ዑቁበቲከ ወአዑዙ ቢከ ሚንከ ላኡህሲ ሰናአን ዐለይከ አንተ ከማ አስነይተ ዐላ ነፍሲከ»*

«አላህ ሆይ! በእርካታህ ከቁጣህ፣ በይቅር ባይነትህ ከቅጣትህ እጠበቃለሁ:: በአንተ ከአንተ እጠበቃለሁ:: አንተ ራስክን ያወደስከውን ያክል ላወድስህ አይቻለኝም::» (አስሐበ ሱነን አራቱና አህመድ)

١١٨- «اللَّهُمَّ إِيَّاكَ نَعْبُدُ، وَلَكَ نُصَلِّي وَنَسْجُدُ، وَإِلَيْكَ نَسْعَىٰ وَنَحْفِدُ، نَرْجُو رَحْمَتَكَ، وَنَخْشَىٰ عَذَابَكَ، إِنَّ

عذَابَكَ بِالْكَافِرِينَ مُلْحَقٌ. اللَّهُمَّ إِنَّا نَسْتَعِينُكَ، وَنَسْتَغْفِرُكَ، وَنُثْنِي عَلَيْكَ الْخَيْرَ، وَلَا نَكْفُرُكَ، وَنُؤْمِنُ بِكَ، وَنَخْضَعُ لَكَ، وَنَخْلَعُ مَنْ يَكْفُرُكَ»

*118. «አልሏሁምመ ኢይያከ ነዕቡዱ ወለከ ኑሶልሊ ወነስጁዱ ወኢለይከ ነስአ ወነህፊዱ ነርጁ ራህመተከ ወነኽሻ አዛበከ ኢንነ አዛበከ ቢልካፊሪይነ ሙልሀቅን! አልላሁምመ ኢንና ነስተኢይኑከ ወነስተግፊሩከ ወኑስኒ ዐለይከል ኸይረ ወላ ነከፉሩከ ወኑእሚኑ ቢከ ወነኽደኡ ለከ ወነኽለኡ መን የከፉሩክ»*

«አላህ ሆይ! አንተን ብቻ እናመልካለን:: ላንተ እንሰግዳለን! እናጉበድዳለን:: ወደአንተ እንሮጣለን! እንገሰግሳለን:: እዝነትህን እንሻለን:: ቅጣትህን እንፈራለን:: ቅጣትህ ካሀድያንን ያገኛል:: አላህ ሆይ! እርዳታህን እንጥይቅሀለን:: ምህረትህን እንማፀንሃለን:: እናወድስሃለን:: አንክድህም:: ባንተ እናምናለን:: ላንተ እንንበረከካለን:: አንተን የካደህን አንተዋለን::» (በይሐቅይ)

## 33. ዊትርን ካጠናቀቁ በኋላ የሚባል ዚክር

١١٩ - «سُبْحَانَ الْمَلِكِ الْقُدُّوسِ»

*119. «ሱብሃነል መሊኪል ቁዱስ»* «ብፁእ የሆነው ጌታ ከጉደሎ ነገሮች የጠራ ነው፡፡» ሦስት ጊዜ፡፡ ሦስተኛውን ድምፅዎን ከፍ በማድረግና በመሳብ ይበሉ፡፡

[رَبِّ الْمَلَائِكَةِ وَالرُّوحِ]»

*«ረብቢል መላኢከቲ ወርሩሂ»*
«የመላእክታንና የመንፈሱ አምላክ» የሚለውን ሀረግም ያክሉ፡፡

(ነሳእይ)

## 34. በትካዜና በሐዘን ወቅት የሚባል ዱዓ-

١٢٠ - «اللَّهُمَّ إِنِّي عَبْدُكَ، ابْنُ عَبْدِكَ، ابْنُ أَمَتِكَ، نَاصِيَتِي بِيَدِكَ، مَاضٍ فِيَّ

حُكْمُكَ، عَدْلٌ فِيَّ قَضَاؤُكَ، أَسْأَلُكَ
بِكُلِّ اسْمٍ هُوَ لَكَ، سَمَّيْتَ بِهِ نَفْسَكَ،
أَوْ أَنْزَلْتَهُ فِي كِتَابِكَ، أَوْ عَلَّمْتَهُ أَحَداً
مِنْ خَلْقِكَ، أَوِ اسْتَأْثَرْتَ بِهِ فِي عِلْمِ
الْغَيْبِ عِنْدَكَ، أَنْ تَجْعَلَ الْقُرْآنَ رَبِيعَ
قَلْبِي، وَنُورَ صَدْرِي، وَجَلَاءَ حُزْنِي،
وَذَهَابَ هَمِّي»

*120. «አልሏሁምመ ኢንኒ ዐብዱከ ኢብኑ ዐብዲከ ኢብኑ አመቲከ ናሲየቲይ ቢየዲከ ማዲን ፊይየ ሑክሙከ አድሉን ፊይየ ቀዷኡከ አሰአሉከ ቢኩልሊ ኢሰሚን ሁወ ለከ ሳምመይተ ቢሂ ነፍሰከ አው አንዘልተሁ ፊኪታቢከ አው አልለምተሁ አሐደን ሚን ኸልቂከ አዊሰተእሰርተ ቢሂ ፊይ ኢልሚን ገይቢ ኢንደከ አንተጅአለል ቁርአን ረቢዐ ቀልቢ ወኑረ ሰድሪ ወጀላአ ሑዝኒ ወዘሃበ ሐምሚ»*

«አላህ ሆይ! እኔ ባሪያህ፣ የወንድ ባሪያህም፣ የሴት ባሪያህም ልጅ ነኝ:: ሁሉ ነገሬ በእጅህ ነው:: ውሳኔህ በኔ ላይ ተፈጻሚ ብይንህ ፍትሃዊ ነው:: ቁርአንን የቀልቤ መርጊያ፣ የልቦናዬ ብርሃን፣ የሐዘኔ መፅናኛና የጭንቁ ማስወገጃ ታደርግ ልኝ ዘንድ በስሞችህ ሁሉ እማፀንሃለሁ:: አንተ ራስህን በጠራህባቸው ወይም ኪታብህ ውስጥ ባሰፈርካቸው፥ ከፍጡራንህ ለአንዱ ባስተማርካቸው ወይም ለማንም ባልገለፅካቸው ስሞችህ::» (አህመድ)

١٢١- «اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ الْهَمِّ وَالْحَزَنِ، وَالْعَجْزِ وَالْكَسَلِ، وَالْبُخْلِ والْجُبْنِ، وَضَلَعِ الدَّيْنِ وَغَلَبَةِ الرِّجَالِ»

*121. «አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙቢከ ሚነል ሃምሚ ወል ሐዘኒ ወልአጅዚ ወልከሰሊ ወልቡኽሊ ወል ጁብኒ ወደላኢድደይኒ ወገለበቲርሪጃል»*

«አላህ ሆይ! ከሐዘንና ትካዜ፥ ከደካማነትና ስንፍና ከስስትና፣ ፍርሃት፥ ከእዳ

ጫናና ከሽንፈት በአንተ እጠበቃለሁ።»

## 35. የጭንቅ ጊዜ ዱዓ

١٢٢- «لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ الْعَظِيمُ الْحَلِيمُ، لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ رَبُّ الْعَرْشِ الْعَظِيمُ، لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ رَبُّ السَّمٰوَاتِ وَرَبُّ الْأَرْضِ وَرَبُّ الْعَرْشِ الْكَرِيمُ»

*122. «ላኢላሀ ኢ ለልላሁል አዚይሙል ሐሊይሙ ላኢላሀኢልለልላሁ ረብቡል ዐርሺል ዐዚይም ላኢላሀ ኢልለልላሁ ረብቡስሰማዋቲ ወረብቡል አርዲ ወረብቡል ዐርሺል ከሪይም»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። ታላቅና ፅኑ ነው። ከአላህ ውጪ ሌላ አምላክ የለም። የታላቁ ዐርሽ ጌታ ነው። ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። የሰማያትና የምድር፥ እንዲሁም የታላቁ ዓርሽ ጌታ ነው።» (ቡኻሪና ሙስሊም)

١٢٣- «اللَّهُمَّ رَحْمَتَكَ أَرْجُو فَلَا

تكِلْنِي إِلَىٰ نَفْسِي طَرْفَةَ عَيْنٍ، وَأَصْلِحْ لِي شَأْنِيَ كُلَّهُ، لَا إِلَـٰهَ إِلَّا أَنْتَ»

*123. «አልላሁምመ ረሀመተከ አረጁ ፈላ ተኪልኒ ኢላ ነፍሲይ ጠርፈተ ዐይኒን ወአስሊህ ሊይ ሸእኒይ ኩልለሁ ላኢላሀ ኢልላ አንተ»*

«አላህ ሆይ! እዝነትህን እሻለሁ:: ለቅፅበት ያክል እንኳ ለራሴ አትተወኝ:: ሁሉ ነገሬን ያማረ አድርግልኝ:: ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም::» (አቡዳውድና አህመድ)

١٢٤- «لَا إِلَـٰهَ إِلَّا أَنْتَ سُبْحَانَكَ إِنِّي كُنْتُ مِنَ الظَّالِمِينَ»

*124. «ላኢላሀ ኢልላ አንተ ሱብሃነከ ኢንኒ ኩንቱ ሚን አዝዛሊሚይን»*

«ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: ጥራት ይገባህ:: እኔ ከበደለኞች አንዱ ነኝ::» (ቲርሙዝይ)

١٢٥- «اللهُ اللهُ رَبِّي لَا أُشْرِكُ بِهِ شَيْئاً»

*125. «አልሏሁ አልሏሁ ረብቢይ ላኡሽሪኩ ቢሂ ሸይአ»*
«አምላኬ አላህ ነው:: በርሱ ላይ ምንንም ኃይል አላጋራም::» (አቡዳውድ)

## 36. ከጠላት ወይም (ጨካኝ) ባለሥልጣን ጋር ሲገናኙ የሚሉት ዱዓ

١٢٦- «اللَّهُمَّ إِنَّا نَجْعَلُكَ فِي نُحُورِهِمْ وَنَعُوذُ بِكَ مِنْ شُرُورِهِمْ»

*126. «አልሏሁምመ ኢንና ነጅዐሉከ ፊይኑሁሪሂም ወነዑዙ ቢከ ሚን ሹሩሪሂም»*
«አላህ ሆይ! እኛ (ከጠላቶቻችን) ግንባር አድርገንሃል:: ከተንኮላቸውም በአንተ እንጠበቃለን::» (አቡዳውድና ሐኪም)

١٢٧- «اللَّهُمَّ أَنْتَ عَضُدِي، وَأَنْتَ نَصِيرِي، بِكَ أَجُولُ، وَبِكَ أَصُولُ، وَبِكَ أُقَاتِلُ»

*127. «አልሏሁምመ አንተ አዱዲይ ወአንተ ነሲይሪይ ቢከ አጁሉ ወቢከ አሱሉ ወቢከ ኡቃቲሉ»*

«አላህ ሆይ! አንተ መከታዬ ነህ:: አንተ ረዳቴ ነህ:: በአንተ (ኃይል) እንቀሳቀሳለሁ:: በአንተ ሐይል እጠበቃለሁ:: በአንተ ረዳትነት እፋለማለሁ::»

(አቡዳውድና ቲርሙዝይ)

١٢٨ - «حَسْبُنَا اللهُ وَنِعْمَ الْوَكِيلُ»

*128. «ሀስቡነልሏሁ ወኒእመል ወኪል»*

«አላህ ጠባቂያችን ነው:: (አላህ) ያማረ መመኪያ ነው::» (ቡኻሪ)

## 37. የባለሥልጣናትን ግፍ የፈራ ሰው የሚያደርገው ዱዓ

١٢٩ - «اللَّهُمَّ رَبَّ السَّمٰوَاتِ السَّبْعِ، وَرَبَّ الْعَرْشِ الْعَظِيمِ، كُنْ لِي جَاراً مِنْ فُلَانِ بْنِ فُلَانٍ، وَأَحْزَابِهِ مِنْ خَلَائِقِكَ؛ أَنْ

يَفْرُطَ عَلَيَّ أَحَدٌ مِنْهُمْ أَوْ يَطْغَىٰ؛ عَزَّ
جَارُكَ، وَجَلَّ ثَنَاؤُكَ، وَلَا إِلَـٰهَ إِلَّا أَنْتَ»

*129. «አልኋሁምመ ረብበስሰማዋቲስሰብዒ ወረብበል ዐርሹል ዐዚይም ኩን ሊይ ጃረን ሚን ፉላኒ ኢብኒ ፉላን ወአህዛቢሂ ሚን ኸላኢቂከ አን የፍሩጠ ዐለይየ አሐዱን ሚንሁም አው የጥጋ አዝዘጃሩከ ወጀልላ ሰናኡከ ወላኢላሀ ኢልላ አንተ »*

«የሰባቱ ሰማያትና የታላቁ ዓርሽ ጌታ ሆይ! እገሌ የእገሌ ልጅ ከሆነውና ፍጡራኖችህ ከሆኑት ረዳቶቹ(ጥቃት) ጠባቂ ሁነኝ:: እንዳቸውም እንዳይበድሉኝ፣ ጥቃትም እንዳይፈፅሙብኝ:: ጥበቃህ ላቀ:: ልዕልናህ ከፍ አለ:: ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም::» (ቡኻሪ)

١٣٠- «اللهُ أَكْبَرُ، اللهُ أَعَزُّ مِنْ خَلْقِهِ
جَمِيعاً، اللهُ أَعَزُّ مِمَّا أَخَافُ وَأَحْذَرُ، أَعُوذُ
بِاللهِ الَّذِي لَا إِلَـٰهَ إِلَّا هُوَ، الْمُمْسِكِ
السَّمٰوَاتِ السَّبْعِ أَنْ يَقَعْنَ عَلَىٰ الْأَرْضِ

إِلَّا بِإِذْنِهِ، مِنْ شَرِّ عَبْدِكَ فُلَانٍ، وَجُنُودِهِ
وَأَتْبَاعِهِ وَأَشْيَاعِهِ، مِنَ الْجِنِّ وَالْإِنْسِ،
اللَّهُمَّ كُنْ لِي جَاراً مِنْ شَرِّهِمْ، جَلَّ
ثَنَاؤُكَ وَعَزَّ جَارُكَ، وَتَبَارَكَ اسْمُكَ،
وَلَا إِلَٰهَ غَيْرُكَ»

*130. «አልሏሁ አክበር አልሏሁ አአዙ ሚን ኸልቂሂ ጀሚዐ፣ አልሏሁ አዐዝዙ ሚ ማ አኻፉ ወአህዘሩ፣ አሁዙ ቢልላሂልለዚ ላኢላሃ ኢልላ ሁወ፣ አልሙምሲኪስሰማዋቲስ ሰብዒ አን የቀዕና ዐለል አርዲ ኢላ ቢኢዝኒሂ፣ ሚንሸርሪ ዐብዲከ ፉላን፣ ወጁኑዲሂ ወአትባኢሂ ወአሽያኢሂ፣ ሚነልጂንነ ወል ኢንስ፣ አልሏሁምመ ኩን ሊ ጃረን ሚን ሸርሪሂም፣ ጀለ ሰናኡከ ወአዝዘ ጃሩከ፣ ወተባረከስሙከ፣ ወላኢላሃ ገይሩከ»*

«አላህ ከሁሉም የላቀ ነው። አላህ ከፍጡራኑ ይበልጥ ኃያል ነው። አላህ ከምፈራውና ከምጠነቀቀው ይበልጥ ኃያል ነው። ከርሱ ውጭ ሌላ አምላክ በሌለው፣ ሰባቱን ሰማያት በፈቃዱ ምድር ላይ

እንደይወድቁ ተቆጣጣሪ በሆነው አላህ እገሌ ከተባለ ባሪያው፣ ከአጋንንትም፣ ከሰውም ከሆኑ ረዳቶቹና ተከታዮቹ (ጥቃት) እጠበቃለሁ። አላህ ሆይ! ከከፋታቸው ጠባቂዬ ሁን። ልዕልናህ ከፍ አለ። ጥበቃህ በረታ። ስምህ ተቀደሰ። ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም።»- ሦስት ጊዜ። (ቡኻሪ)

## 38.በጠላት ላይ ዱዓ ማድረግ

١٣١ - «اللَّهُمَّ مُنْزِلَ الْكِتَابِ، سَرِيعَ الْحِسَابِ، اهْزِمِ الأَحْزَابَ، اللَّهُمَّ اهْزِمْهُمْ وَزَلْزِلْهُمْ»

*131. «አልሏሁምመ ሙንዚለል ኪታብ፣ ሠሪዐል ሒሳብ፣ እህዚሚል አሕዛብ፣ አልሏሁምመ ኢህዚምሁም ወዙልዚል ሁም»*

«ኪታቡን ያወረድክ+ ምርመራህ ፈጣን የሆነ አላህ ሆይ! ህዝቦችን በትን። አላህ ሆይ! በትናቸው። አርገፍግፋቸው።»

(ሙስሊም)

## 39. ሰዎችን የፈራ ሰው የሚለው ዱዓ

«اللَّهُمَّ اكْفِنِيهِمْ بِمَا شِئْتَ» - ١٣٢

*132. «አልሏሁምመ ኢክፊኒ ሂም ቢማ ሺእተ»*

«አላህ ሆይ! አንተ በምትሻው መንገድ ከጥቃታቸው አድነኝ።»

(ሙስሊም)

## 40. እምነቱ ላይ ጥርጣሬ ያደረበት ሰው የሚለው ዱዓ

*133.* «የአላህን ጥበቃ ይማፀን።»

(ቡኻሪና ሙስሊም)

«ካጠራጠረው ነገር ይገላገል።»

(ቡኻሪና ሙስሊም)

«آمَنْتُ بِاللهِ وَرُسُلِهِ» -١٣٤

*134. «አመንቱ ቢልላሂ ወረሱሊሂ»*

«በአላህና በመልዕክተኛው አመንኩ» ይበል።

(ሙስሊም)

135. ተከታዩን የአላህ ቃል ያንብብ:-

﴿هُوَ ٱلْأَوَّلُ وَٱلْآخِرُ وَٱلظَّـٰهِرُ وَٱلْبَاطِنُ وَهُوَ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمٌ﴾»

*«ሁወል አውወሉ ወል አኺሩ ወዝዟሂሩ ወል ባጢኑ ወሁወ ቢኩልሊ ሸይኢን ዐሊይም»*

«የመጀመሪያውም የመጨረሻውም፣ ገልፁም ስውሩም እርሱ ነው:: እርሱ የሁሉም ነገር አዋቂ ነው::»

(አል-ሐዲድ፣ 3) (አቡዳውድ)

## 41. እዳ ያስበት ሰው የሚያደርገው ዱዓ

١٣٦- «اللَّهُمَّ اكْفِنِي بِحَلَالِكَ عَنْ حَرَامِكَ وَأَغْنِنِي بِفَضْلِكَ عَمَّنْ سِوَاكَ»

*136. «አልላሁምመ ኢክፊኒ ቢሐላሊከ ዐን ሐራሚከ ወአግኒኒ ቢፈድሊከ ዐምመን ሲዋከ»*

«አላህ ሆይ! በሐላልህ ከሐራምህ

አብቃቃኝ::በትሩፋትህ ከአንተ ውጭ ያሉ አካላትን ከመጠየቅ አድነኝ::» (ቲርሙዝይ)

١٣٧- «اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ الْهَمِّ وَالْحَزَنِ، وَالْعَجْزِ وَالْكَسَلِ، وَالْبُخْلِ وَالْجُبْنِ، وَضَلَعِ الدَّيْنِ وَغَلَبَةِ الرِّجَالِ»

*137. «አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ሐምሚ ወልሐዘኒ፣ ወል ዐጅዚ ወልከሰሊ፣ ወል ቡኽሊ ወል ጁብኒ፣ ወደለዒድደይኒ ወገለበቲርሪጃል»*

«አላህ ሆይ! ከትካዜና ሐዘን፣ ከደካማ ነትና ስንፍና፣ ከስስትና ፍርሃት፣ ከእዳ ጫናና ከሸንፈት በአንተ እጠበቃለሁ::»

(ቡኻሪ)

**42. ሶላት ውስጥ ወይም ቁርአን በማንበብ ሳይ እያለ የሸይጧን ጉትጎታ ያጋጠመው ሰው ማለት ያለበት ዱዓ**

١٣٨- «أَعُوذُ بِاللهِ مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ»

*138. «አዑዙ ቢልላሂ ሚነሽሸይጧኒር ረጂም»*

«ከተረገመው ሰይጣን በአላህ እጠበቃለሁ» (ካሉ በኋላ) በግራ ጉንዎ ሦስት ጊዜ ይትፉ።» (ሙስሊም)

## 43. አንዳች አስቸጋሪ ነገር የገጠመው ሰው

١٣٩ - «اللَّهُمَّ لَا سَهْلَ إِلَّا مَا جَعَلْتَهُ سَهْلًا وَأَنْتَ تَجْعَلُ الْحَزْنَ إِذَا شِئْتَ سَهْلًا»

*139. «አልላሁምመ ላ ሰህለ ኢልላ ማ ጀዐልተሁ ሳህላ! ወአንተ ተጅዐሉል ሐዝነ ኢዛ ሺእተ ሰህላ»*

«አላህ ሆይ! አንተ ቀላል ካደረግከው ነገር ውጭ ቀላል የለም። አንተ ሀዘንን-ከሻህ- ቀላል ታደርጋለህ።» (ኢብን ሒብባን)

## 44. ወንጀል የፈፀመ ሰው ማድረግ ያለበት

140. «አንድ (የአላህ) ባሪያ ወንጀል

በሚፈፅምበት ወቅት ውዱእ በትክክል ያድርግ። ከዚያም ሁለት ረከዓዎችን ይስገድና አላህን ምህረት ይማፀን። አላህ ምህረትን ይለግሰዋል።»

(አቡዳውድና ቲርሙዝይ)

## 45. ሸይጧንን ለማባረርና ጉትጐታውን ለመቋቋም የሚደረግ ዱዓ

141. «በአላህ ከርሱ (ከሸይጧን) መጠበቅ።» (አቡዳውድና ቲርሙዝይ)

142. «አዛን (ማድረግ)»

(ቡኻሪና ሙስሊም)

143. «ዚክርና የቁርአን ንባብ።»

(ሙስሊም)

## 46. የማይፈልጉት ወይም ከአቅምዎ በላይ የሆነ ነገር ሲከሰት የሚሉት ዱዓ

١٤٤ - «قَدَرُ اللهِ وَمَا شَاءَ فَعَلَ»

*144. «ቀደሩልሏህ፣ ወማሻአ ፈዐል»*

«የአላህ ውሳኔ ነው:: አላህ ያሻውን ፈፃሚል::» (ሙስሊም)

## 47. ልጅ ለወለደ ሰው ብሥራትና ምላሹ

١٤٥- « بَارَكَ اللهُ لَكَ فِي الْمَوْهُوبِ لَكَ، وَشَكَرْتَ الْوَاهِبَ، وَبَلَغَ أَشُدَّهُ، وَرُزِقْتَ بِرَّهُ ».

*145. «ባረከልሏሁ ለከ ፊል መውሂቢ ለከ፣ ወሸከርተል ዋሂበ፣ ወበለገ አሹድደሁ፣ ወሩዚቅተ ቢርረሁ»*

«የተሰጠህን (ልጅ) አላህ ይባርክ ልህ:: ለጋሹን (አላህን) አመስጋኝ ሁን:: ለማደግ ያብቃው:: መብትህን ጠባቂ፣ ፈቃድህን ፈጻሚ ያድርግልህ::»

ብሥራት የተደረገለት ሰው እንዲህ በማለት ይመልስ:-

« بَارَكَ اللهُ لَكَ وَبَارَكَ عَلَيْكَ، وَجَزَاكَ اللهُ خَيْراً، وَرَزَقَكَ اللهُ مِثْلَهُ، وَأَجْزَلَ ثَوَابَكَ»

*«ባረከልሏሁ ለከ ወባረከ ዐለይከ፣ ወጀመዐ በይነኩማ ፊ ኸይርን፣ ወረዘቀከልሏሁ ሚንሁ፣ ወአጀዘለ ሰዋበከ»*

«አላህ ላንተም ረድኤቱን ይለግስህ። አላህ ምንዳህን አይንፈግህ። አላህ አምሳያ ውን (ልጅ) ይለግስህ። ምንዳህን ያብዛ ልህ።»

## 48. ለህፃናት የሚደረግ ዱዓ

146. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሐሰንና ሑሰይን እንዲህ በማለት (ከሸይጧን ተንኮል) የአላህን ጥበቃ ይማፀኑላቸው ነበር:-

«أُعِيذُكُمَا بِكَلِمَاتِ اللهِ التَّامَّةِ مِنْ كُلِّ شَيْطَانٍ وَهَامَّةٍ، وَمِنْ كُلِّ عَيْنٍ لاَمَّةٍ»

*«ኡዒዙኩማ ቢከሊማቲልላሂ ለትታመህ ሚን ኩልሊ ሸይጧኒን ወሐምመህ፣ ወሚን ኩልሊ ዐይኒን ላምመህ»*

«ምሉዕና ፍፁም በሆኑት የአላህ ቃላት ከሰይጣናት ሁሉና ከእኩይ ሰው (ተንኮል) እንዲሁም ጉጅ ከሆነ ዓይን ሁሉ

እጠብቃችኋለሁ::» (ቡኻሪ)

## 49. በሽተኛን በሚጠይቁበት ወቅት የሚሉት ዱዓ

١٤٧- «لَا بَأْسَ طَهُورٌ إِنْ شَاءَ اللهُ»

*147. «ላበእሰ ጠሁሩን ኢንሻአልላሁ»*

«አይዞህ:: ምንም አይደለም:: ምንአልባትም አላህ ከፈቀደ (ይህ በሽታ) የወንጀልህ ማበሻ ሊሆን ይችላል::» (ቡኻሪ)

١٤٨- «أَسْأَلُ اللهَ الْعَظِيمَ رَبَّ الْعَرْشِ الْعَظِيمِ أَنْ يَشْفِيَكَ»

*148. «አስአሉልላሀል ዐዚም ረብበል ዐርሺል ዐዚይም አን የሽፊከ»*

«የታላቁን አርሽ ጌታ ከበሽታህ ይፈውስህ ዘንድ እማፀነዋለሁ::»- ሰባት ጊዜ:: (ቲርሙዚይና አቡዳውድ)

## 50. በሽተኛን የመጠየቅ ትሩፋት

149. ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«አንድ ሰው ሙስሊም ወንድሙን ከበሽታው ለመጠየቅ ከሄደ እስኪመለስ ድረስ በገነት አፀድ ውስጥ ነው። ሲቀመጥ የአላህ እዝነት ይሰፍንበታል። ጧት ከሆነ እስኪመሽ ድረስ ሰባ ሺህ መላእክት ሶለዋት ያወርዱለታል። ምሽት ከሆነ ደግሞ እስኪነጋ ድረስ ሰባ ሺህ መላእክት ሶለዋት ያወርዱለታል።»
(ቲርሙዝይ፣ ኢብን ማጃህና አህመድ።)

## 51. ለመዳን ተስፋ የሌለው በሽተኛ የሚያደርገው ፀሎት

١٥٠- «اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي وَارْحَمْنِي وَأَلْحِقْنِي بِالرَّفِيقِ الأَعْلَى»

*150. «አልላሁምመ ኢግፊር ሊይ ወርሃምኒ ወአልሒቅኒ ቢርረፊቂል አዕላ»*

«አላህ ሆይ! ምህረትህን ለግሰኝ። እዘንልኝ። ከደጋግ ሰዎች ጐራም ፈርጀኝ።» (ቡኻሪና ሙስሊም)

151. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ለሞት በተቃረቡበት ወቅት እጃቸውን ውሃ ውስጥ በመንከር ፊታቸውን ያብሱ ነበር።

እንዲህም ይሉ ነበር:-

« لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ إِنَّ لِلْمَوْتِ لَسَكَرَاتٍ »

*«ላኢላሀ ኢልለልሏሀ ኢንነ ሊል መውቲ ለሰከራት»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: ሞት ጣእር አለው::» (ቡኻሪ)

١٥٢- لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ وَاللهُ أَكْبَرُ، لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ، لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ، لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ وَلَا حَوْلَ وَلَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللهِ»

*152. «ላኢላሀ ኢልለልሏሀ ወልላሁ አክበር፣ ላኢላሀ ኢልለልሏሀ ወሕደሁ፣ ላኢላሀ ኢልለሏሀ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ፣ ላኢላሀ ኢልለሏሀ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምድ፣ ላኢላሀ ኢልለሏሀ ወላ ሐውላ ወላ ቁወተ ኢልላ ቢልላሀ»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። አላህ ከሁሉም የላቀ ነው። ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። አንድ ነው። ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። አንድ ነው። አጋር የለውም። ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። ንግሥና ለርሱ ብቻ ነው። ምስጋናም ለርሱ ብቻ ነው። ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። ብልሃትም ኃይልም የለም- በአላህ ቢሆን እንጅ።» (ቲርሙዝይና ኢብን ማጀህ)

## 52. ጣእረ ሞት ላይ ያለን ሰው መምራት

153. «የመጨረሻ ንግግሩ :-

١٥٣- لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللهُ

« ላኢላሃ ኢለሏህ»

የሆነ ሰው ጀንነት ይገባል።»

(አቡ ዳውድ)

## 53. ችግር የገጠመው ሰው የሚያሰማው ዱዓ

١٥٤ - «إِنَّا لِلَّهِ وَإِنَّا إِلَيْهِ رَاجِعُونَ اللَّهُمَّ أْجُرْنِي فِي مُصِيبَتِي وَأَخْلِفْ لِي خَيْراً مِنْهَا»

154. «ኢንና ሊልላሂ ወኢንና ኢለይሂ ራጂዑን፣ አልሏሁምመ አጂርኒ ፊ ሙሲበቲ፣ ወአኽሊፍ ሊ ኺይረን ሚንሀ»

«እኛ የአላህ ነን። ወደርሱም ተመላሾች ነን። አላህ ሆይ! ለደረሰብኝ ችግር ምንዳ ስጠኝ። በርሷ ምትክም የተሻለ ነገር ተካልኝ።» (ሙስሊም)

## 54. የሞተን ሰው ዓደን ሲከድኑ የሚሉት ዱዓ

١٥٥ - «اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِفُلَانٍ (بِاسْمِهِ) وَارْفَعْ دَرَجَتَهُ فِي الْمَهْدِيِّينَ، وَاخْلُفْهُ فِي عَقِبِهِ فِي الْغَابِرِينَ، وَاغْفِرْ لَنَا وَلَهُ يَا رَبَّ الْعَالَمِينَ، وَافْسَحْ لَهُ فِي قَبْرِهِ وَنَوِّرْ لَهُ فِيهِ»

*155. «አልላሁምመ ኢግፊር ሊ... ወርፈዕ ደረጀተሁ ፊል መህዲዪይን ወኽሉፍሁ ፊ ዐቂቢሂ ፊል ጋቢሪይን፣ ወግፊር ለና ወለሁ ያረብበል ዐለሚን፣ ወፍሰህ ለሁ ፊ ቀብሪሂ ወነውዊር ለሁ ፊሂ»*

«አላህ ሆይ! ለእገሌ (ስሙ ይጠቀስ) ምህረትህን ለግስው። ደረጃውን ከፍ አድርግለት። ቅን ከሆኑ ሰዎች ፈርጀው። እኛንም እሱንም ይቅር በለን። የዓለማት ጌታ ሆይ! ቀብሩን ሰፊና ብርሃናማ አድርግለት።» (ሙስሊም)

## 55.ሶላተል ጀናዛ ላይ ለሟች የሚደረግ ዱዓ

١٥٦- «اللَّهُمَّ اغْفِرْ لَهُ وَارْحَمْهُ، وَعَافِهِ، وَاعْفُ عَنْهُ، وَأَكْرِمْ نُزُلَهُ، وَوَسِّعْ مُدْخَلَهُ، وَاغْسِلْهُ بِالْمَاءِ وَالثَّلْجِ وَالْبَرَدِ، وَنَقِّهِ مِنَ الْخَطَايَا كَمَا نَقَّيْتَ الثَّوْبَ الْأَبْيَضَ مِنَ الدَّنَسِ، وَأَبْدِلْهُ دَاراً خَيْراً

مِنْ دَارِهِ، وَأَهْلًا خَيْراً مِنْ أَهْلِهِ، وَزَوْجاً خَيْراً مِنْ زَوْجِهِ، وَأَدْخِلْهُ الْجَنَّةَ، وَأَعِذْهُ مِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ [وَعَذَابِ النَّارِ]»

*156. «አልላሁምመ ኢግፊር ለሁ ወርሀምሁ፣ ወዓፊሂ ወዕፉ ዐንሁ፣ ወአክሪም ኑዙለሁ፣ ወወስሲዕ ሙድኸለሁ፣ ወግሲልሁ ቢልማኢ ወስሰልጅ ወልበረዲ፣ ወነቅቂሂ ሚነል ኸጧያ ከማ ነቅቀስሰውቡል አብየዱ ሚነድደነስ፣ ወአብዲልሁ ዳረን ኸይረን ሚን ዳሪሂ፣ ወአህለን ኸይረን ሚን አህሊሂ፣ ወዘውጀን ኸይረን ሚን ዘውጂሂ፣ ወአድኺልሁልጀንነተ፣ ወአዒዝሁ ሚን ዐዛቢል ቀብር ወዐዛቢንናር»*

«አላህ ሆይ! ምህረትህን ለግሰው:: እዘንለት:: አስመቸው:: ይቅር በለውም:: መስተንግዶውን መልካም፣ የሚገባበትን ቦታ (ቀብር) ሰፊ አድርግለት:: በውሃ፣ በወርጭና በበረዶ እጠበው:: ነጭ ልብስ ከእድፍ እንደሚፀዳው እርሱንም ከወንጀል አፅዳው:: ከነበረበት የበለጠ መኖሪያ ለግሰው:: የተሻሉ ቤተሰቦችንም አድር ግለት:: የተሻለች ሚስትም ለግሰው::

ጀንነት አስገባው። ከቀብር (እና ከእሳት) ቅጣት ጠብቀው።» (ሙስሊም)

١٥٧- «اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِحَيِّنَا، وَمَيِّتِنَا، وَشَاهِدِنَا، وَغَائِبِنَا، وَصَغِيرِنَا وَكَبِيرِنَا، وَذَكَرِنَا وَأُنْثَانَا. اللَّهُمَّ مَنْ أَحْيَيْتَهُ مِنَّا فَأَحْيِهِ عَلَىٰ الإِسْلَامِ، وَمَنْ تَوَفَّيْتَهُ مِنَّا فَتَوَفَّهُ عَلَىٰ الإِيمَانِ، اللَّهُمَّ لَا تَحْرِمْنَا أَجْرَهُ وَلَا تُضِلَّنَا بَعْدَهُ»

*157. «አልሏሁምመ ኢግፊር ሊሐዪና ወመይቲና፣ ወሻሂዲና ወጋኢቢና፣ ወሰጊሪና ወከቢሪና፣ ወዘከሪና ወኡንሣና፣ አልሏሁምመ መን አሕየይተሁ ሚንና ፈአሕዪሂ ዐለል ኢስላም፣ ወመን ተወፈይተሁ ሚንና ፈተወፍፋሁ ዐለል ኢማን፣ አልሏሁምመ ላተሕሪምና አጅረሁ፣ ወላ ቱዲልለና በዕደሁ»*

«አላህ ሆይ! በህይወት ላለነውም ለሞቱትም፥ በቅርብ ለምንገኘውም ለራቁትም፥ ለትንሹም ለትልቁም፥ ለሴቶችም

ለወንዶችም ወገኖቻችን ምህረትህን ለግስ። አላህ ሆይ! ከመካከላችን በህይወት የምታቆየውን በኢስላም ላይ እንዲቆይ አድረገው። ሞት የወሰንክበትን ደግሞ በኢማን ላይ እንዳለ ለሞት አብቃው። አላህ ሆይ! (የሥራ) ምንዳችንን አትንፈገን። ከርሱ በኋላም አታጥምመን።»

(ኢብን ማጃህና አህመድ)

١٥٨- «اللَّهُمَّ إِنَّ فُلَانَ بْنَ فُلَانٍ فِي ذِمَّتِكَ، وَحَبْلِ جِوَارِكَ، فَقِهِ مِنْ فِتْنَةِ الْقَبْرِ وَعَذَابِ النَّارِ، وَأَنْتَ أَهْلُ الْوَفَاءِ وَالْحَقِّ. فَاغْفِرْ لَهُ وَارْحَمْهُ إِنَّكَ أَنْتَ الْغَفُورُ الرَّحِيمُ»

*158. «አልላሁምመ... ፊ ዚምመቲከ፣ ወሐብሊ ጂዋሪከ፣ ፈቂሂ ሚን ፊትነቲል ቀብሪ ወዐዛቢንናር፣ ወአንተ አህሉል ወፋኢ ወልሐቅቂ፣ ፈግፊር ለሁ ወርሐምሁ ኢንነከ አንተል ገፉሩርረሒም»*

«አላህ ሆይ! እገሌ የእገሌ ልጅ በጥበቃህ ሥር፣ በቁጥጥርህ ውስጥ ነው:: ከቀብር ፈተናና ከእሳት ቅጣት ጠብቀው:: አንተ ውሳኔህን የምትፈፅምና እውነተኛ ነህና:: ማረው:: እዘንለትም:: አንተ መሐሪ፣ አዛኝ ነህ::» (ኢብን ማጀህ)

١٥٩- «اللَّهُمَّ عَبْدُكَ وَابْنُ أَمَتِكَ احْتَاجَ إِلَىٰ رَحْمَتِكَ، وَأَنْتَ غَنِيٌّ عَنْ عَذَابِهِ، إِنْ كَانَ مُحْسِناً فَزِدْ فِي حَسَنَاتِهِ، وَإِنْ كَانَ مُسِيئاً فَتَجَاوَزْ عَنْهُ»

*159. «አልኣሁምመ ዐብዱከ ወብኑ አመቲከ እሕታጀ ኢላ ራህመቲከ፣ ወአንተ ገኒዩን ዐን ዐዛቢሂ፣ ኢን ካነ ሙሕሲነን ፈዚድ ፊ ሐሰናቲሂ፣ ወኢን ካነ ሙሲአን ፈተጃወዝ ዐንሁ»*

«አላህ ሆይ! ይህ ሰው ባሪያህ ነው:: የአንተ ባሪያ የሆነችው ልጅም ነው:: እዝነትህን ከጅሏል:: አንተ እርሱን ከመቅጣት የተብቃቃህ ነህ:: መልካም

ተግባር ፈፅሞ ከሆነ ምንዳውን አክልለት:: ሐጢአት ፈፅሞ ከሆነ ደግሞ ይቅር በለው::» (ሐኪም)

## 56. ለአቅመ አዳም ሳይደረሱ ህፃናት የሚደረግ የሶላተል ጀናዛ ዱዓ

١٦٠- «اللَّهُمَّ أَعِذْهُ مِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ»

*160. «አልሏሁምመ አዒዝሁ ሚን ዐዛቢል ቀብር»*

«አላህ ሆይ! ከቀብር ቅጣት ጠብቀው::» (በይሐቅይ)

«اللَّهُمَّ اجْعَلْهُ فَرَطاً وَذُخْراً لِوَالِدَيْهِ، وَشَفِيعاً مُجَاباً. اللَّهُمَّ ثَقِّلْ بِهِ مَوَازِينَهُمَا وَأَعْظِمْ بِهِ أُجُورَهُمَا، وَأَلْحِقْهُ بِصَالِحِ الْمُؤْمِنِينَ، وَاجْعَلْهُ فِي كَفَالَةِ إِبْرَاهِيمَ، وَقِهِ بِرَحْمَتِكَ عَذَابَ الْجَحِيمِ، وَأَبْدِلْهُ دَاراً خَيْراً مِنْ دَارِهِ، وَأَهْلاً خَيْراً

مِنْ أَهْلِهِ، اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِأَسْلَافِنَا، وَأَفْرَاطِنَا، وَمَنْ سَبَقَنَا بِالإِيمَانِ»

*«አልሏሁምመ ኢጅዐልሁ ፈረጠን ወዙኽረን ሊዋሊደይሂ፣ ወሸፈዐን ሙጃበን፣ አልሏሁምመ ሠቅቂል ቢሂ መዋዚነሁማ ወአዕዚም ቢሂ ኡጁረሁማ፣ ወአልሒቅሁ ቢሷሊሂል ሙእሚኒን፣ ወጅዐልሁ ፊ ከፋለቲ ኢብራሂም፣ ወቂሂ ቢራህመቲከ ዐዛበል ጀሂም፣ ወአብዲልሁ ዳረን ኸይረን ሚንዳሪሂ፣ ወአህለን ኸይረን ሚን አህሊሂ፣አልለሏሁምመ ኢግፊር ሊአስላፊና ወአፍራጢና ወመን ሰበቀና ቢል ኢማን»*

«አላህ ሆይ! ቀዳሚ ሽልማት አድርገው:: ለወላጆቹም ተቀማጭ ሀብት አድረግው:: ተቀባይነት ያለው አማላጅም (ሸፊዐ) አድርገው:: አላህ ሆይ! በርሱ ሳቢያ የወላጆቹን ሚዛን ከፍ አድርገው:: ምንዳቸውንም ጨምርላቸው:: ከደጋግ ሙእሚኖች ፈርጀውም:: በኢብራሂም ሞግዚትነት ሥርም አውለው:: በእዝነትህ ከጀሃነም ቅጣት ጠብቀው:: ከለቀቀው የተሻለ መኖሪያን ለግሰው:: ትቷቸው ከሄደው ቤተሰቦቹ የተሻሉ ቤተሰቦችን

ስጠው። አላህ ሆይ! ለአያት ቅድመ አያቶቻችን ምህረትን ለግስ። ለልጆቻች ንም። በእምነት ለቀደመን ሁሉም።» ማለቱም በላጭነት አለው።

١٦١ - «اللَّهُمَّ اجْعَلْهُ لَنَا فَرَطاً، وَسَلَفاً، وَأَجْراً»

*161.* «አልላሁምመ ኢጅዐልሁ ለና ፈረጠን ወሰለፈን ወአጅራ»

«አላህ ሆይ! ለኛ ቀዳሚ ሽልማት+ ወደፊት አልፎ የሚቆየንና ምንዳም የሚያስገኝን አድርግልን።»

## 57. የሐዘን መግለጫ ዱዓ

١٦٢ - «إِنَّ لِلَّـهِ مَا أَخَذَ، وَلَهُ مَا أَعْطَىٰ وَكُلُّ شَيْءٍ عِنْدَهُ بِأَجَلٍ مُسَمًّى. . . فَلْتَصْبِرْ وَلْتَحْتَسِبْ»

*162. «ኢንና ሊልላሂ ማአኸዘ፣ ወለሁ ማ አዕጧ ወኩልሉ ሸይኢን ዒንደሁ ቢአጀሊን ሙሰምማ ... ፈልተስቢር ወልተህተሲብ»*

«የወሰደውም የሰጠውም የአላህ ነው። ሁሉም ነገር ከርሱ ዘንድ የተወሰነ ቀን ቀጠሮ አለው። ትታገሺ፡ (ከአላህ) ምንዳዋን ትፈልግ።» (ቡኻሪ)

«أَعْظَمَ اللهُ أَجْرَكَ، وَأَحْسَنَ عَزَاءَكَ وَغَفَرَ لِمَيِّتِكَ»

*«አዕዘመልሏሁ አጅረክ፣ ወአህሰነ ዐዛአክ፣ ወገፈረ ሊመይቲክ»*

«አላህ ምንዳህን ከፍ ያድርግልህ። ሀዘንህን ያቃልልህ። ለሟቹም ምህረትን ይለግሰው።» ቢልም በላጭነት ይኖረዋል። (አዝካር ሊነወውይ )

## 58. ሟችን ቀብር ውስጥ ሲያስገቡ የሚሉት ዱዓ

١٦٣ - «بِسْمِ اللهِ وَعَلَىٰ سُنَّةِ رَسُولِ اللهِ»

*163, «ቢስሚልላህ ወዐላ ሱንነቲ ረሱሊልላህ»*
«በአላህ ስም! በአላህ መልዕክተኛ አፈጻፀም ስልት (ሱንና)።» (አቡዳውድ)

## 59. ሟች ከተቀበረ በኋላ የሚባል ዱዓ

١٦٤ - «اللَّهُمَّ اغْفِرْ لَهُ اللَّهُمَّ ثَبِّتْهُ»

*164. «አልሏሁምመ ኢግፊር ለሁ አልሏሁምመ ሠብቢትሁ»*

«አላህ ሆይ! ምህረትን ለግሰው። አላህ ሆይ! ፅናትን ለግሰው።» (አቡዳውድና ሐኪም)

## 60. በቀብር ጉብኝት ወቅት የሚባል ዱዓ

١٦٥ - «السَّلَامُ عَلَيْكُمْ أَهْلَ الدِّيَارِ، مِنَ الْمُؤْمِنِينَ وَالْمُسْلِمِينَ، وَإِنَّا إِنْ شَاءَ اللهُ بِكُمْ لَاحِقُونَ [وَيَرْحَمُ اللهُ الْمُسْتَقْدِمِينَ مِنَّا وَالْمُسْتَأْخِرِينَ] أَسْأَلُ اللهَ لَنَا وَلَكُمُ الْعَافِيَةَ»

*165. «አስሰላሙ ዐለይኩም አህለድዲያሪ፣ ሚነል ሙእሚኒይነ ወልሙስሊሚይን፣ ወኢንነና ኢንሻአል ሏሁ ቢኩም ላሒቁን፣ ወየርሐሙልሏሁ አል ሙስተቅዲሚይን ሚንና ወል ሙስተእኺሪይን፣ አስአሉልሏሀ ለና ወለኩሙል ዓፊያህ»*

«በዚህ መቃብር ውስጥ የምትገኙ ሙእሚኖችና ሙስሊሞች ሆይ! ሰላም ይስፈንባችሁ። እኛም በአላህ ፈቃድ እንከተላችኋለን። አላህ ከመካከላችን ለተቀደሙትም ወደኋላ ለቀሩትም ምህረት ይለግሳቸው። ለኛም ለናንተም ከአላህ ዘንድ ደህንነትን እጠይቅላችኋለሁ።» (ሙስሊም)

## 61. ነፋስ ሲነፍስ የሚደረግ ዱዓ

١٦٦- «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ خَيْرَهَا، وأَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّهَا»

*166. «አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ኸይረሀ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸሪሃ»*

«አላህ ሆይ! የዚህችን (ነፋስ) መልካም

ነገር እጠይቅሃለሁ:: ከክፋቷ በአንተ እጠበቃለሁ::» (አቡዳውድና ኢብን ማጀህ)

١٦٧- «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ خَيْرَهَا، وخَيْر مَا فِيهَا، وَخَيْرَ مَا أُرْسِلَتْ بِهِ وأَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّهَا، وَشَرِّ مَا فِيهَا، وشَرِّ مَا أُرْسِلَتْ بِهِ»

*167. «አልላሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ኸይረሃ ወኸይረ ማፊሃ ወኸይረ ማ ኡርሲለት ቢሂ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪሃ ወሸርሪ ማፊሃ ወሸርሪ ማ ኡርሲለት ቢሂ»*

«አላህ ሆይ! መልካሟን፥ በውስጧ የያዘችውን መልካም ነገርና የተላከችበትን መልካም ነገር እጠይቅሃለሁ:: ከክፋዋ፣ በውስጧ ከያዘችው ክፉ ነገርና ከተላከች በት ክፉ ነገር በአንተ እጠበቃለሁ::»

(ቡኻሪና ሙስሊም)

## 62. በጉርምርምታ ወቅት የሚደረግ ዱዓ

١٦٨- «سُبْحَانَ الَّذِي يُسَبِّحُ الرَّعْدُ بِحَمْدِهِ وَالْمَلَائِكَةُ مِنْ خِيفَتِهِ»

*168. «ሱብሐነልለዚ ዩሰብቢሑ አርረዕዱ ቢሐምዲሂ ወል መላኢከቱ ሚን ኺፈቲሂ»*

«ጉርምርታው በምስጋናና ውዳሴ፣ መላዕክት ደግሞ ፍርሃት በተሞላበት ሁኔታ የሚያጠሩት ጌታ ከጉድለ ባህሪያት የጠራ ነው።» (አል-ሙወጠዕ)

## 63. ዝናብ በሚጠሩበት ወቅት የሚረግ ዱዓ

١٦٩- «اللَّهُمَّ أَسْقِنَا غَيْثاً مُغِيثاً مَرِيئاً مَرِيعاً، نَافِعاً غَيْرَ ضَارٍّ، عَاجِلًا غَيْرَ آجِلٍ»

*169 «አልላሁምመ አስቂና ገይሰን ሙጊሰን መሪአን መሪዓ፣ ናፊዐን ገይረ ዷርሪን፣ ዐጂሉን ገይረ አጂሊን»*

«አላህ ሆይ! የሚበጅ፣ምሉዕ፣ ጤናማ፣ ጠቃሚና ጉጅ ያልሆነን፣ ወቅታዊና የማይዘገይ የሆነን ዝናብ አጠጣን::»
(አቡዳውድ)

١٧٠- «اللَّهُمَّ أَغِثْنَا، اللَّهُمَّ أَغِثْنَا اللَّهُمَّ أَغِثْنَا»

*170. «አልሏሁምመ አጊስና፣ አልሏሁምመ አጊስና፣ አልሏሁምመ አጊስና»*
«አላህ ሆይ! ዝናብ ለግሠን፣ አላህ ሆይ! ዝናብ ለግሠን፣ አላህ ሆይ! ዝናብ ለግሰን::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

١٧١- «اللَّهُمَّ اسْقِ عِبَادَكَ، وَبَهَائِمَكَ، وَانْشُرْ رَحْمَتَكَ، وَأَحْيِي بَلَدَكَ الْمَيِّتَ»

171. *«አልሏሁምመ አስቂ ዒባደከ ወበሐኢመከ፣ ወንሹር ራሀመቲከ፣ ወአሕይ በለደከል መይት»*
«አላህ ሆይ! ባሮችህንና እንስሳ ቶችህንም አጠጣ:: ትሩፋትህን ለግስ፣ በሞተች

ከተማህ ላይ ነፍስ ዝራ፡፡» (አቡ ዳውድ)

## 64. ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት የሚደረግ ዱዓ

١٧٢- «اللَّهُمَّ صَيِّباً نَافِعاً»

*172. «አልሏሁምመ ሰይበን ናፊዐን»*

«አላህ ሆይ! ጠቃሚ ዝናብ (አድርገው)፡፡» (ቡኻሪ)

## 65. ዝናብ ከዘነበ በኋላ የሚደረግ «ዚክር»

١٧٣- «مُطِرْنَا بِفَضْلِ اللهِ وَرَحْمَتِهِ»

*173. «ሙጢርና ቢፈድሊልላሂ ወራሕመቲሂ»*

«በአላህ ትሩፋትና እዝነት ዝናብ ለማግኘት በቃን፡፡» (ቡኻሪ)

## 66. ዝናብ ሲበዛ የሚደረግ ዱዓ

١٧٤ - «اللَّهُمَّ حَوَالَيْنَا وَلَا عَلَيْنَا . اللَّهُمَّ عَلَىٰ الْآكَامِ وَالظِّرَابِ، وَبُطُونِ الْأَوْدِيَةِ، وَمَنَابِتِ الشَّجَرِ»

*174. «አልሏሁም መ ሐዋለይና ወላ ዐለይና፣ አልሏሁምመ ዐለል አካሚ ወዝዚራቢ ወቡጡኒል አውዲየቲ ወመናቢቲሽሸጀር»*

«አላህ ሆይ! ዙሪያውን (አዝንብ፤ በኛ ላይ አታዝንበው):: አላህ ሆይ! በግጦሽ መሬቶች ላይ፣ በኮረብታዎችና በሸለቆ ዎች፥ በዛፎችም ሥር እንዲዘንብ አድር ግ::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

## 67. ጠረቃን ሲያዩ የሚሉት ዱዓ

١٧٥ - «اللهُ أَكْبَرُ، اللَّهُمَّ أَهِلَّهُ عَلَيْنَا بِالْأَمْنِ وَالْإِيمَانِ، وَالسَّلَامَةِ وَالْإِسْلَامِ، وَالتَّوْفِيقِ لِمَا تُحِبُّ رَبَّنَا وَتَرْضَىٰ، رَبُّنَا وَرَبُّكَ اللهُ»

*175. «አልሏሁ አክበር፣ አልሏሁምመ አሒልለሁ ዐለይና ቢል አምኒ ወል ኢማን፣ ወስሰላመቲ ወል ኢስላም፣ ወትተውፊቂ ሊማ ቱሒብቡ ረብበና ወተርዷ፣ ረብቡና ወረብቡከልሏሀ»*

«አላህ ከሁሉም የላቀ ነው:: አላህ ሆይ! ይህች ጨረቃ በጤና፣ በእምነት፣ በሰላም፣ በኢስላምና አንተ በምትወደውና በምታፈቅረው መልኩ በዙሪያችን እንድታበራ አድርጋት:: (ጨረቃ ሆይ!) የአንችም የኛም ጌታ አላህ ነው::»

(ቲርሙዝይ)

## 68. ጾመኛ ሲያፈጥር የሚያሰማው ዱዓ

١٧٦- «ذَهَبَ الظَّمَأُ وَابْتَلَّتِ الْعُرُوقُ، وَثَبَتَ الأَجْرُ إِنْ شَاءَ اللهُ»

*176. «ዘሐበዝዘመኡ ወብተልለቲል ዑሩቁ፣ ወሠበተል አጅሩ ኢንሻአልላሀ»*

«ጥማችን ተቆርጧል:: የደም ሥሮቻችን ረጥበዋል:: የአላህ ፈቃድ ከሆነ ምንዳም ተረጋግጦልናል::» (አቡዳውድና ሌሎችም)

١٧٧- «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ بِرَحْمَتِكَ الَّتِي وَسِعَتْ كُلَّ شَيْءٍ أَنْ تَغْفِرَ لِي»

*177. «አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ቢራሀመቲከ አልለቲ ወሲዐት ኩልለ ሸይኢን አንተግፊርሊ»*

«አላህ ሆይ! ምህረትን ትለግሰኝ ዘንድ ሁሉንም ነገር ባዳረሰችው እዝነትህ እማፀንሐለሁ።» (ኢብን ማጀህ)

## 69. ከምግብ በፊት የሚባሉ ዱዓዎች

178. ምግብ በሚጀምሩበት ወቅት :-

« بِسْمِ اللهِ »

«ቢስሚልላህ»

«በአላህ ስም» በማለት ይጀምሩ።

ከዘነጉ መሐል ላይ:-

« بِسْمِ اللهِ فِي أَوَّلِهِ وَآخِرِهِ »

*«ቢስሚልላህ! ፊ አወሊሂ ወአኺሪሂ»*

«በአላህ ስም! በመጀመሪያውም መጨረሻውም ላይ» ይበሉ።

(አቡዳውድና ቲርሙዝይ)

179. አላህ ምግብ የመገበው ሰው:-

«اللَّهُمَّ بَارِكْ لَنَا فِيهِ وَأَطْعِمْنَا خَيْراً مِنْهُ»

*«አልላሁምመ ባሪክ ለና ፊ ሂ ወአጥኢምና ኸይረን ሚንሁ!»*

«አላህ ሆይ! በለገስከን ምግብ ረድኤትህን አስፍንልን! ከርሱ የተሻለን ምግብም መግበን::» ይበል::

አላህ ወተት ያጠጣው ሰው ደግሞ:-

«اللَّهُمَّ بَارِكْ لَنَا فِيهِ وَزِدْنَا مِنْهُ»

*«አልላሁመ ባሪክ ለና ፊይሂ ወዚድና ሚንሁ»*

«አላህ ሆይ! በርሱ (ባጠጣህን ወተት) ረድኤት አትንፈገን:: ከርሱ (ከወተቱ) ጨምረንም» ይበል:: (ቲርሙዝይ)

## 70. ምግብ ሲያጠናቅቁ የሚሉት ዱዓ

١٨٠- «الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي أَطْعَمَنِي هَذَا،

وَرَزَقَنِيهِ، مِنْ غَيْرِ حَوْلٍ مِنِّي وَلَا قُوَّةٍ»

*180. «አልሐምዱ ሊልላሂልለዚ አጦዐመኒ ሐዛ ወረዘቀኒሂ ሚን ገይሪ ሐውሊን ሚንኒ ወላ ቁወህ»*

«ያለኔ ኃይልና ብልሐት ይህንን ምግብ ለሰገሰኝ አላህ ምስጋና ይገባው።»

(አስሐበ ሱነን ‐ከነሳእይ ውጭ)

١٨١ - «الْحَمْدُ لِلَّهِ حَمْداً كَثِيراً طَيِّباً مُبَارَكاً فِيهِ، غَيْرَ [مَكْفِيٍّ وَلَا] مُوَدَّعٍ،

*181. «አልሐምዱ ሊልላሂ ሐምደን ከሢረን ጠይበን ሙባረከን ፊሂ፣ ገይረ ሙክፊዪን ወላ ሙወድደዒን »*

«ለአላህ ብዙ፣ መልካምና የተባረከ የሆነ፣ የመጨረሻና የመሰናበቻ ያልሆነ ምስጋና ይገባው።» (ቡኻሪና ቲርሙዝይ)

## 71. እንግዳ ስጋባዙ የሚያደርገው ዱዓ

١٨٢ - «اللَّهُمَّ بَارِكْ لَهُمْ فِيمَا رَزَقْتَهُمْ،

وَاغْفِرْ لَهُمْ وَارْحَمْهُمْ»

*182. «አልላሁምመ ባሪክለሁም ፊማ ረዘቅተሁም፣ ወግፊር ለሁም፣ ወርሃምሁም»*

«አላህ ሆይ! በሰጣሀቸው ሲሳይ ረድኤትህን አውርድላቸው:: ምህረትን ለግሳቸው:: እዘንላቸውም::» (ሙስሊም)

**72. ውሃ ሳጠጣዎ ሰው ወይም ውሃ ሲከጅሉ የሚያሰሙት ዱዓ**

«اللَّهُمَّ أَطْعِمْ مَنْ أَطْعَمَنِي وَاسْقِ مَنْ سَقَانِي»

*183. «አልላሁምመ አጥዒም መን አጥዓመኒ ወስቂ መንሰቃኒ»*

«አላህ ሆይ! የመገበኝን መግበው፣ ያጠጣኝን አጠጣው::» (ሙስሊም)

**73. ጾመኛ ከሴላ ሰው ቤት ሲያፈጥር የሚያሰማው ዱዓ**

١٨٤- «أَفْطَرَ عِنْدَكُمُ الصَّائِمُونَ، وَأَكَلَ طَعَامَكُمُ الأَبْرَارُ، وَصَلَّتْ عَلَيْكُمُ

«الْمَلَائِكَةُ»

*184. «አፍጠረ ኢንደኩምሷኢሙን፣ ወአከለ ጣዐሙኩሙል አብራር፣ ወሰልለት ዐለይኩሙል መላኢከህ»*

«ከናንተ ዘንድ ጾመኞች ያፍጥሩ:: ምግባችሁን በጐ ሰዎች (ብቻ) ይመገቡት:: መላኢኮች ከአላህ ምህረትን ይማፀኑላችሁ::»

(አቡዳውድ፣ ኢብን ማጀህና ነሳኢይ)

## 74. ጾመኛ ምግብ ቀርቦለት ካላፈጠረ የሚያደርገው ዱዓ

185. ከናንተ አንዳችሁ ግብዣ በሚጠራበት ወቅት ግብዣውን ይቀበል:: ጾመኛ «ከሆነ ዱዓ ያድርግ::ጾመኛ ካልሆነ ደግሞ ይመገብ::» (ሙስሊም)

## 75. አንድ ጾመኛ በሚሰደብበት ወቅት ማለት ያለበት

186. «እኔ ጾመኛ ነኝ! እኔ ጾመኛ ነኝ::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

## 76.የፍራፍሬ እሸት በሚመለከቱበት ወቅት የሚያሰሙት ዱዓ

١٨٧ - «اللَّهُمَّ بَارِكْ لَنَا فِي ثَمَرِنَا، وَبَارِكْ لَنَا فِي مَدِينَتِنَا وَبَارِكْ لَنَا فِي صَاعِنَا، وَبَارِكْ لَنَا فِي مُدِّنَا»

*187. «አልላሁምመ ባሪክ ለና ፊሰመሪና፣ ወባሪክ ለና ፊመዲነቲና፣ ወባሪክ ለና ፊሷዒና ወባሪክ ለና ፊሙድዲና»*

«አላህ ሆይ! ከፍሪያችን ላይ ረድኤትህን አውርድልን:: ከከተማችን ላይ ረድኤትህን አውርድልን:: ሷዐችንን ባርክልን፤ ሙዳችንንም[1] ባርክልን::» (ሙስሊም)

## 77. ያነጠሰ ሰው የሚለው ዱዓ

188. ከናንተ አንዳችሁ በሚያነጥስበት ወቅት:-

1- «ሷዕ»ና «ሙድ» የመስፈሪያ ዓይነቶች ናቸው::

« الْحَمْدُ لِلَّهِ »
«አልሐምዱሊላህ»

«ለአላህ ምስጋና ይገባው» ይበል::
ወንድሙ ወይም ባልደረባው ደግሞ:-

« يَرْحَمُكَ اللهُ »
«የርሐሙካላሁ»

«አላህ ይዘንልህ» ይበለው::
እርሱም:-

« يَهْدِيكُمُ اللهُ وَيُصْلِحُ بَالَكُمْ »
«የሕዲኩሙሏሁ ወዩስሊሕ ባለኩም»

«አላህ ቅኑን ጉዳና ይምራችሁ፣ ያላችሁበትን ሁኔታም ያሻሽልላችሁ፣ የልብን ጸእድነት ይለግሳችሁ» በማለት ይመልስ:: (ቡኻሪ)

## 78. አንድ ካፊር አላህን ካመሰገነ የሚሰጠው ምላሽ

١٨٩- «يَهْدِيكُمُ اللهُ وَيُصْلِحُ بَالَكُمْ»

189. «አላህ ቅኑን መንገድ ይምራህ:: ያለህበትን ሁኔታም ያሻሽልልህ:: የልቦናን ጸእድነት ይለግስህ::» (ቲርሙዚይና አህመድ)

## 79. ላገባ ሰው የሚደረግ ዱዓ

١٩٠- «بَارَكَ اللهُ لَكَ، وَبَارَكَ عَلَيْكَ؛
وَجَمَعَ بَيْنَكُمَا فِي خَيْرٍ»

*190. «ባረከልሏሁ ለከ፣ ወባረከ ዐለይከ፣ ወጀማዐ በይነኩማ ኸይር»*

«አላህ (ባለቤትህን) ይባርክልህ:: አንተንም ይባርክህ:: በመካከላችሁ የሚኖረው ትስስርም መልካም ይሁን::»

(አስሐበ ሱነን- ከነሳኢይውጭ)

## 80. ያገባ ወይም እንስሳት የገዛ ሰው የሚያደርገው ዱአ

191. ከናንተ አንዳችሁ ሚስት በሚያገባበት ወቅት:-

١٩١- «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ خَيْرَهَا
وَخَيْرَ مَا جَبَلْتَهَا عَلَيْهِ وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ

شَرِّهَا وَشَرِّ مَا جَبَلْتَهَا عَلَيْهِ،

*«አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ኸይረሃ ወኸይረ መጀበልተሐ ዐለይሒ! ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪሐ ወሸርሪ ማጀበልተሐ ዐለይሒ»*

«አላህ ሆይ! የዚህችን ሴት መልካም ነገር እና እንድታዘነብል ያመላከትካትን መልካም ነገር እጠይቅሃለሁ:: ከተንኮሏና ከአዘነበለችበት መጥፎ ነገርም በአንተ እጠበቃለሁ::» ይበል:: ግመል ሲገዛም ሻኛዋን በመያዝ ይህንኑ ዱዓ ያድረግ:: (አቡዳውድና ኢብን ማጃህ)

## 81. ከወሲባዊ ተራክቦ በፊት የሚደረግ ዱዓ

١٩٢ - «بِسْمِ اللهِ. اللَّهُمَّ جَنِّبْنَا الشَّيْطَانَ، وَجَنِّبِ الشَّيْطَانَ مَا رَزَقْتَنَا»

*192. «ቢስሚልላህ! አልሏሁምመጀንኒብናሸ ሸይጧን ወጀንኒቢሸይጧነ ማረዘቅተና»*

«በአላህ ስም! አላህ ከሸይጧን (ተንኮል) ጠብቀን:: የምትለገሰንን (ልጅም)

ከሸይጧን (ተንከል) ጠብቀው።» (ቡኻሪና ሙስሊም)

## 82. በቁጣ ወቅት የሚደረግ ዱዓ

١٩٣ - «أَعُوذُ بِاللهِ مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ»

*193. «አዑዙ ቢልላሂ ሚነሽሸይጧኒር ረጂም»*

«እርጉም ከሆነው ሸይጧን በአላህ እጠበቃለሁ።» (ቡኻሪና ሙስሊም)

## 83. የተሞከረ (ወንጀል ላይ የወደቀ) ሰው በሚያዩበት ወቅት የሚያደርጉት ዱዓ

١٩٤ - «الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي عَافَانِي مِمَّا ابْتَلَاكَ بِهِ وَفَضَّلَنِي عَلَىٰ كَثِيرٍ مِمَّنْ خَلَقَ تَفْضِيلاً»

*194. «አልሐምዱ ሊልላሂልለዚ ዐፋኒ ሚምመብተላከ ቢሂ ወፈድደለኒ ዐላ ከሢረን ሚምመን ኸለቀ ተፍዲላ»*

«አንተን ከሞከረህ ነገር ለጠበቀኝ፣ ከፍጡራኖቹ ከብዙዎች ላላቀኝ አላህ ምስጋና ይገባው:: (ቲርሙዝይ)

## 84. ስብሰባ (መጅሊስ) ላይ የሚባል ዱዓ

195. ኢብን ዑመር (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከአንድ ስብሰባ ላይ ከመቆ ላላነሰ ጊዜ :- «رَبِّ اغْفِرْ لِي وَتُبْ عَلَيَّ إِنَّكَ أَنْتَ التَّوَّابُ الغَفُورُ»

*«ረብቢ ግፊርሊ ወቱብ ዐለይየ ኢንነከ አንተ ተዋቡል ገፉር»*

«ጌታዬ ሆይ! ምህረት ለግሰኝ ፀፀቴን ተቀበለኝ:: አንተ ፀፀትን ተቀባይ አዛኝ ነህና» (ቲርሙዝይ)

## 85. ከስብሰባ ሲነሱ የሚሉት ዚክር

١٩٦ - «سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ وَبِحَمْدِكَ، أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَهِ إِلَّا أَنْتَ، أَسْتَغْفِرُكَ وَأَتُوبُ إِلَيْكَ»

*196. «ሱብሐነከልሏሁምመ ወቢ ሐምዲከ፣ አሽሐዱ አንላኢላሃ ኢልላ አንተ፣ አስተግፊሩክ ወአቱቡ ኢለይክ»*

«አላህ ሆይ! ጥራትና ምስጋና ይገባሀ:: ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ:: ምህረትህን እለምንሃለሁ:: ወደአንተ በፀፀት እመለሳለሁ::
(አስሐበ ሱነን)

## 86. «አላህ ምህረቱን ይለግስህ» ሳልዎት ሰው የሚሰጡት ምላሽ

١٩٧- «وَلَكَ»

*197. «ወለከ»*

«ላንተ ምህረቱን አይንፈግህ»
(አህመድና ነሳእይ)

## 87. መልካም ውለታ ለዋለልዎት የሚያደርጉት ዱዓ

١٩٨- «جَزَاكَ اللهُ خَيْراً»

*198. «ጀዛከልሏሁ ኸይረን»*

«አላህ መልካም ምንዳ ህን ይክፈልህ::»
(ተ:ርሙዝይ)

## 88. አላህ ከደጃል የሚጠብቅባቸው (ዚክሮች)

*199.* «ከአል-ከህፍ ምዕራፍ የመጀመሪያዎቹ አናቅፅ አሥሮቹን በአይምሮው ያጠና ከደጃል ይጠበቃል።» (ሙስሊም)

ከየሰላቱ ማጠናቀቂያ ላይ ተሸሁድን ካነበቡ በኋላ ከደጃል ፈ.ተና ይጠብቅዎ ዘንድ አላህን ዘውትር ይማፀኑ።

## 89. «ለአላህ ብዬ እወድሀለሁ» ባልዎ የሚያደርጉት ዱዓ

٢٠٠- «أَحَبَّكَ الَّذِي أَحْبَبْتَنِي لَهُ»

*200. «አሐብበከልለዚ አሕበብተኒ ለሁ»*

«ለርሱ ስትል የወደድከኝ (አምላክ) ይውደድህ።» (አቡዳውድ)

## 90. ገንዘብ ለሰገሰም ሰው የሚያደርጉት ዱዓ

٢٠١ - «بَارَكَ اللهُ لَكَ فِي أَهْلِكَ وَمَالِكَ»

*201. «ባረከልሏሁ ለከ ፊ አሕሊከ ወማሊከ፡.»*

«አላህ በገንዘብህም በቤተሰቦችህም ላይ ረድኤቱን ያውርድልህ፡፡» (ቡኻሪ)

## 91. የተበደረ ሰው ገንዘብ ሲመልስ ለበዳሪው የሚያደርገለት ዱዓ

٢٠٢ - «بَارَكَ اللهُ لَكَ فِي أَهْلِكَ وَمَالِكَ ، إِنَّمَا جَزَاءُ السَّلَفِ الْحَمْدُ وَالْأَدَاءِ»

*202. «ባረከልሏሁ ለከ ፊ አሕሊከ ወማሊከ፣ ኢ.ንነማ ጀዛኡስሰለፊ አልሐምዱ ወል አዳአ»*

«አላህ በገንዘብህም በቤተሰቦችህም ላይ ረድኤቱን ያውርድልህ፡፡ የብድር ምንዳ ምስጋናና የወሰዱትን መመለስ ነው፡፡» (ነሳኢይ)

## 92. ሽርክ ሲያሰጋዎ የሚሉት ዱዓ

٢٠٣- «اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ أَنْ أُشْرِكَ بِكَ وَأَنَا أَعْلَمُ، وَأَسْتَغْفِرُكَ لِمَا لَا أَعْلَمُ»

*203. «አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ አን ኡሽሪከ ቢከ ወአን አዕለሙ፣ ወአስተግፊሩከ ሊማላ አዕለሙ»*

«አላህ ሆይ! እያወቅኩ በአንተ ላይ ከማሻረክ በአንተ እጠበቃለሁ:: ሳላውቅ ለምፈፅመው የሽርክ ተግባር ምህረትህን እጠይቅሃለሁ::»

## 93. «አላህ ረድኤቱን ይለግስህ» ላለዎ ሰው የሚያደርጉለት ዱዓ

٢٠٤- «وَفِيكَ بَارَكَ اللهُ»

*204. «ወፊከ ባረከልሏሁ»*

«ላንተም አላህ ረድኤቱን ይለግስህ::»

## 94. በገድ ያስማመንን ስማመልከት የሚባል ዚክር

٢٠٥- «اللَّهُمَّ لَا طَيْرَ إِلَّا طَيْرُكَ، وَلَا خَيْرَ إِلَّا خَيْرُكَ، وَلَا إِلَـٰهَ غَيْرُكَ»

*205. «አልሏሁምመ ላጠይረ ኢልላ ጠይሩክ፣ ወላ ኸይረ ኢልላ ኸይሩክ፣ ወላ ኢላሃ ገይሩክ»*

«አላህ ሆይ! አንተ ከወሰንከው ውጭ ገድ የለም። አንተ መልካም ካልከው ውጭ መልካም የለም። ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም።» (አህመድ)

## 95. መጓጓዣ ላይ ሲወጡ የሚሉት ዱዓ

٢٠٦- بِسْمِ اللهِ، الْحَمْدُ لِلَّـهِ ﴿سُبْحَٰنَ ٱلَّذِى سَخَّرَ لَنَا هَٰذَا وَمَا كُنَّا لَهُۥ مُقْرِنِينَ ۞ وَإِنَّآ إِلَىٰ رَبِّنَا لَمُنقَلِبُونَ﴾ «الْحَمْدُ لِلَّـهِ،

الْحَمْدُ لِلَّـهِ، الْحَمْدُ لِلَّـهِ، اللهُ أَكْبَرُ، اللهُ أَكْبَرُ، اللهُ أَكْبَرُ، سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ إِنِّي ظَلَمْتُ نَفْسِي فَاغْفِرْ لِي، فَإِنَّهُ لَا يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلَّا أَنْتَ»

*206. «ቢስሚልላሂ አልሐምዱ ሊላህ! ሱብሐነለዚ ሰኸረ ለና ሐዛ ወማ ኩንና ለሁ ሙቅሪኒን፣ ወኢንና ኢላ ረብቢና ለሙንቀሊቡን! አልሐምዱ ሊልላህ፣ አልሐምዱ ሊልላህ፣ አልሐምዱ ሊልላህ፣ ፣ አልሏሁ አክበር፣ አልሏሁ አክበር፣ አልሏሁ አክበር፣ ሱብሐነከልሏሁምመ ኢንኒ ዘለምቱ ነፍሲ ፈግፊር ሊ፣ ፈኢንነሁ ላየግፊሩ ዝዙኑበ ኢልላ አንተ»*

«በአላህ ስም፤ ምስጋና ለአላህ የተገባ ይሁን:: 'ይህን (መጓጓዣ) ያገራልን ጌታ ጥራት ይገባው:: እኛ ለመፈፀም የምንችል አልነበርንም:: እኛ ወደጌታችን ተመላሾች ነን::' ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው:: ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው:: ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው:: አላህ

ከሁሉም የላቀ ነው። አላህ ከሁሉም የላቀ ነው። አላህ ከሁሉም የላቀ ነው። አላህ ሆይ! ጥራት ይገባህ። እኔ በነፍሴ ላይ ግፍ ፈፅሚ ያለሁ። ማረኝ። ከአንተ ውጭ ወንጀልን የሚምር የለም።» (አቡዳውድና ቲርሙዝይ)

## 96. ጉዞ ሲወጡ የሚያደርጉት ዱዓ

٢٠٧- اللهُ أَكْبَرُ، اللهُ أَكْبَرُ، اللهُ أَكْبَرُ، ﴿ سُبْحَانَ ٱلَّذِى سَخَّرَ لَنَا هَٰذَا وَمَا كُنَّا لَهُۥ مُقْرِنِينَ * وَإِنَّآ إِلَىٰ رَبِّنَا لَمُنقَلِبُونَ ﴾ «اللَّهُمَّ إِنَّا نَسْأَلُكَ فِي سَفَرِنَا هَـٰذَا الْبِرَّ وَالتَّقْوَىٰ، وَمِنَ الْعَمَلِ مَا تَرْضَىٰ، اللَّهُمَّ هَوِّنْ عَلَيْنَا سَفَرَنَا هَـٰذَا وَاطْوِ عَنَّا بُعْدَهُ، اللَّهُمَّ أَنْتَ الصَّاحِبُ فِي السَّفَرِ، وَالْخَلِيفَةُ فِي الْأَهْلِ، اللَّهُمَّ إِنِّي

أَعُوذُ بِكَ مِنْ وَعْثَاءِ السَّفَرِ، وَكَآبَةِ الْمَنْظَرِ، وَسُوءِ الْمُنْقَلَبِ فِي الْمَالِ وَالأَهْلِ»

*207. «አልላሁ አክበር፣ አልሏሁ አክበር፣ አልሏሁ አክበር ፤ሱብሐነለዚ ሰኸረ ለና ሐዛ ወማ ኩንና ለሁ ሙቅሪኒን ወኢንና ኢላ ረብቢና ለሙንቀሊቡን፤ አልላሁምመ ኢንና ነስአሉከ ፊ ሰፈሪና ሐዛ፣ አል ቢርረ ወትተቅዋ፣ ወሚነል ዓመሊ ማተርዷ፣ አልሏሁምመ ሀውዊን ዓለይና ሰፈረና ሐዛ ወፕዊ ዐንና ቡዕደሁ፣ አልሏሁምመ አንተስሳሂቡ ፊስሰፈሪ፣ ወልኸሊፈቱ ፊል አህሊ፣ አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ወዕሳኢስሰፈሪ፣ ወካበቲል መንዟሪ፣ ወሱኢል ሙንቀለቢ ፊል ማሊ ወልአህሊ»*

«አላህ ከሁሉም የላቀ ነው:: አላህ ከሁሉም የላቀ ነው:: አላህ ከሁሉም የላቀ ነው::'ይህን (መጓጓዣ) ያገራልን ጌታ ጥራት ይገባው:: እኛ ይህን ለመፈፀም የምንችል አልነበርንም:: ወደ ጌታችን ተመላሾች ነን::' አላህ ሆይ! በዚህ በጉዟችን መልካም ነገርንና ጥንቁቅነትን ትለግሰን ፣ አንተን የሚያረካህን ተግባር እንድንፈፅም ታስችለን ዘንድ እንማፀ

ንሃለን:: አላህ ሆይ! ይህን ጉዟችንን ቀላል አድርግልን:: ርቀቱን አሳጥርልን:: አላህ ሆይ! የጉዞ ወቅት ባልደረባችን፣ ለቤተሰ ባችንም ወኪል (ምትክ) አንተ ነህ:: አላህ ሆይ! ከጉዞ ጣጣ፣ ከአመለካከት ለውጥና በቤተሰብም ሆነ በንብረት ላይ ከሚደርስ መጥፎ ነገር በአንተ እጠበ ቃለሁ::»

ከጉዞ ሲመለሱ ይህንን ካሉ በኋላ ተከታዮቹን ያክሉበት:-

«آيِبُــونَ، تَائِبُــونَ، عَابِدُونَ، لِرَبِّـنَا حَامِدُونَ »

*«አዩቡነ፣ ታኢቡነ፣ ዐቢዱነ፣ ሊረብቢና ሓሚዱነ»*

«ተውበት አድርገን፣ አላህን እያመለክንና እያመሰገንም ሆነን ተመ ልሰናል::» (ሙስሊም)

## 97. ወደ አንድ ሰፈር ወይም ከተማ ሲገቡ የሚያደርጉት ዱዓ

٢٠٨- «اللَّهُمَّ رَبَّ السَّمٰوَاتِ السَّبْعِ

وَمَا أَظْلَلْنَ، وَرَبَّ الْأَرَضِينَ السَّبْعِ وَمَا أَقْلَلْنَ، وَرَبَّ الشَّيَاطِينِ وَمَا أَضْلَلْنَ، وَرَبَّ الرِّيَاحِ وَمَا ذَرَيْنَ. أَسْأَلُكَ خَيْرَ هَـٰذِهِ الْقَرْيَةِ وَخَيْرَ أَهْلِهَا، وَخَيْرَ مَا فِيهَا، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّهَا، وَشَرِّ أَهْلِهَا، وَشَرِّ مَا فِيهَا»

*208. «አልሏሁምመ ረብበሰሰማዋቲስ ሰብዒ ወማ አዝለልነ፣ ወረብበል አረዲነስ ሰብዒ ወማ አቀለልነ፣ ወረብበሸሸያጢኒ ወማ አድለልነ ወረብበርሪያሒ ወማ ዘረይነ፣ አስአሉከ ኸይረ ሐዚሂል ቀርየህ ወኸይረ አህለሓ ወኸይረ ማፊሃ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪሐ ወሸርሪ አህሊሃ ወሸርሪ ማፊሐ»*

«የሰባቱ ሰማያትና ያጠለሉት፥ የሰባቱ ምድሮችና የተሸከሙት፥ የሰይጣናትና ያጠመሙት፥ የንፋስና የሚነፍሱበት አካባቢ አምላክ የሆንከው አላህ ሆይ! የዚህችን ስፈረና የነዋሪዎቿን፣ ከውስጧ

ያለውንም መልካም ነገር እጠይቅሃለሁ:: ከክፋቷ፣ ከነዋሪዎቿና በውስጧካሉ ነገሮች ክፋት በአንተ እጠበቃለሁ::»
(ሐኪም)

## 98. ወደ አንድ የገበያ ቦታ ሲገቡ የሚሉት ዱዓ

٢٠٩- «لَا إِلَـهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ، يُحْيِي وَيُمِيتُ وَهُوَ حَيٌّ لَا يَمُوتُ، بِيَدِهِ الْخَيْرُ، وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ»

*209. «ላኢላሀ ኢልለልላሁ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ፣ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ፣ ዩሕዪ ወዩሚቱ ወሁወ ሐዩን ላየሙት፣ ቢየዲሂል ኸይሩ፣ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸየኢን ቀዲር»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አንድ ነው::አጋር የለውም:: ንግሥና የርሱ ብቻ ነው:: ምስጋናም የርሱ ብቻ

ነው:: ህይወትን ይለግሳል:: ይገድላልም:: ህያው ነው:: አይሞትም:: መልካም ነገር ሁሉ በእጁ ነው:: እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው::» (ቲርሙዝይና ሐኪም)

## 99. መጓጓዣዎ ሲደክም የሚያደርጉት ዱዓ

٢١٠- «بِسْمِ اللهِ»

*210. «ቢስሚልላሂ»*
«በአላህ ስም::» (አቡ ዳውድ)

## 100. መንገደኛ ለቤተሰቦቹ ወይም ለሚኖርበት አገር ሰዎች የሚያደርገው ዱዓ

٢١١- «أَسْتَوْدِعُكُمُ اللهَ الَّذِي لَا تَضِيعُ وَدَائِعُهُ»

*211. «አስተውዱሁዑኩሙልላሀ ለለዚ ላተዲዑ ወዳኢዑሁ»*
«ለአላህ አደራ ትቻችኋለሁ:: ለአላህ የተተወ አደራ አይጠፋም::» (አህመድናኢብንማጀህ)

## 101. መንገደኛ ያልሆነ (ሙቂም) ለመንገደኛ (ሙሳፊር) የሚያደረገው ዱዓ

٢١٢- «أَسْتَوْدِعُ اللهَ دِينَكَ، وَأَمَانَتَكَ، وَخَواتِيمَ عَمَلِكَ»

212. *«አስተውዲዑልሏሀ ዲነከ ወአማነተከ ወኸዋቲመ ዐመሊከ»*

«ዲንህን፣ ታማኝነትህንና የተግባርህን ፍጻሜ በጥበቃው ሥር ያደርግ ዘንድ ለአላህ አደራ እተዋለሁ።»

(አህመድና ቲርሙዚይ)

٢١٣- «زَوَّدَكَ اللهُ التَّقْوَى، وَغَفَرَ ذَنْبَكَ، وَيَسَّرَ لَكَ الْخَيْرَ حَيْثُ مَا كُنْتَ»

213. *«ዘውወደከልሏሁት ተቅዋ ወገፈረ ዘንበከ፣ ወየስሰረለከል ኸይረ ሃይሱ ማኩንት»*

«አላህ የጥንቁቅነትን (ተቅዋ) ስንቅ ይለግስህ። ሐጢአትህን ይማርልህ።የትም

ሆነህ መልካሟን ነገር ቀላል ያድርግልህ።»
(ቲርሙዚይ)

## 102. በጉዞ ላይ «ተስቢሕ» እና «ተክቢር» ማድረግ

214. ጃቢር እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:- ከፍታ ቦታ ስንወጣ «አላሁ አክበር»፣ ወደ ዝቅተኛ ቦታ ስንወረድ ደግሞ «ሱብሓነላህ » እንል ነበር። (ቡኻሪ)

## 103. አንድ ሰው ጧት ለጉዞ ሲወጣ የሚለው ዱዓ

٢١٥- «سَمَّعَ سَامِعٌ بِحَمْدِ اللهِ، وَحُسْنِ بَلَائِهِ عَلَيْنَا. رَبَّنَا صَاحِبْنَا، وَأَفْضِلْ عَلَيْنَا عَائِذاً بِاللهِ مِنَ النَّارِ»

215. *«ሰሚዐ ሣሚዑን ቢሐምዲላሂ ወሑስኒ በላኢሂ ዐለይና፣ ረብበና ሷሒብና ወአፍዲል ዐለይና፣ ዓኢዘን ቢልላሂ ሚነንናር»*

«የአላህን ምስጋና፣ በኛ ላይ መልሶም ውለታ መዋሉንም ሰሚ ሰማ ። ጌታዬ ሆይ! ባልደረባ ሁነን፣ ትሩፋትህን ለግሰን ከእሳት ቅጣት በአላህ እንጠበቃለን።» (ሙስሊም)

## 104. በጉዞ መካከል ለእረፍት ቆይታ በሚያደርጉበት ቦታ የሚሉት ዱዓ

٢١٦- «أَعُوذُ بِكَلِمَاتِ اللهِ التَّامَّاتِ مِنْ شَرِّ مَا خَلَقَ»

*«አዑዙ ቢከሊማቲላሂት ታማቲ ሚን ሸርሪ ማኸለቅ»*

216. «ምሉዕ በሆኑት የአላህ ቃላት ከፍጡራኑ ክፋት እጠበቃለሁ።» (ሙስሊም)

## 105. ከጉዞ ሲመለሱ የሚሉት ዚክር

217. (መልዕክተኛው) በዋና ዋና በታዎች ላይ ሲደርሱ ሦስት ጊዜ «አላሁ አክበር» ይሉ ነበር። ከዚያም እንዲህ ይላሉ:-

٢١٧- « لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ

لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ، وَلَهُ الْحَمْدُ، وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ، آيِبُونَ، تَائِبُونَ، عَابِدُونَ، لِرَبِّـنَا حَامِدُونَ، صَدَقَ اللهُ وَعْدَهُ، وَنَصَرَ عَبْدَهُ، وَهَزَمَ الْأَحْزَابَ وَحْدَهُ»

*«ላኢላሀ ኢልለሏሀ ዋህደሁ ላ ሸሪከ ለሁ፣ ለሁል ሙልኩ፣ ወለሁል ሐምዱ፣ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር፣ አዩቡን፣ ታኢቡን፣ ሊረብቢና ሃሚዱን፣ ሰደቀሏሁ ዋዕደሁ፣ ወነሠረ ዐብደሁ፣ ወሐዘመል አህዛበ ዋህደሁ»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። አጋር የለውም። ንግሥና የርሱ ብቻ ነው። ምስጋናም የርሱ ብቻ ነው። እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው። ተውበት ያደረግን፣ ጌታችንን አምላኪዎችና አመስጋኞች ሆነን ተመልሰናል። አላህ ቃሉን ፈፅሟል። ባሪያውን ረድቷል። ብቻውን (የጠላትን) ኃይል ድል ነስቷል።» (ቡኻሪ)

## 106. የሚያስደስተው ወይም የሚጠላው ነገር የገጠመው ሰው የሚለው ዱዓ

218. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) አንድ የሚያስደስታቸው ነገር ሲገጥማቸው፡-

«الْحَمْدُ لِلَّـهِ الَّذِي بِنِعْمَتِهِ تَتِمُّ الصَّالِحَاتُ»

*«አልሐምዱ ሊላሂለዚ ቢኒዕመቲሂ ተቲሙስሷሊሓት»*

«ለአላህ ምስጋና ይገባው፡፡ በፀጋው መልካም ነገሮች ምሉዕ ይሆናሉ፡፡» ይሉ ነበር፡፡

እንዳች የሚጠሉት ነገር በሚገጥማቸው ወቅት ደግሞ፡-

«الْحَمْدُ لِلَّـهِ عَلَىٰ كُلِّ حَالٍ»

*«አልሐምዱ ሊላሂ ዓላ ኩሊ ሓል»*

«በማናቸውም ሁኔታ ለአላህ ምስጋና ተገቢው ነው፡፡» ይላሉ፡፡ (ኢብን ሰንይ)

## 107. በነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ላይ ሶለዋት የማውረድ ትሩፋት

219. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) :-

٢١٩- قَالَ ﷺ «مَنْ صَلَّىٰ عَلَيَّ صَلَاةً صَلَّىٰ اللهُ عَلَيْهِ بِهَا عَشْراً»

*«መን ሶላ ዓለየ ሶላተን ሶለልኣሁ ዐለይሂ ቢሃ ዐሽራ»*

«በኔ ላይ አንድ ጊዜ ሶላዋት ያወረደ አላህ በርሱ ላይ አስር ጊዜ ሶለዋት ያወርድለታል» ብለዋል:: (ሙስሊም)

220. ነብዩ(ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«መቃብሬን የባዕል ማዕከል አታድርጉት:: በኔ ላይም ሶለዋት አውርዱ:: የትም ሆናችሁ ሶለዋት ብታወርዱ ይደርሰኛል::» (አቡ ዳውድና አህመድ)

221. እንዲህ ሲሉም ተናግረ ዋል:-

«ስስታም ማለት ከርሱ ዘንድ እኔ እየተወሳሁ በኔ ላይ ሶለዋት ያላወረደ ነው::» (ቲርሙዚይ)

222..«ለአላህ ተጓዥ መላኢኮች አሉት:: ምድር ላይ ከኡመቴ የሚላክ፣.ኝን

ሰላምታ ለኔ ያደርሳሉ::» (ነሳእይና ሐኪም)

223. «አንድ ሰው ሰላምታ ሲልክልኝ አላህ ነፍስ ይዘራብኝና ምላሽ እሰጠዋለሁ::» • (አቡዳውድ)

## 108. ሰላምታን ማብዛት

224. የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«እስከታምኑ ድረስ ጀንነት አትገቡም:: እስከትፋቀሩ ድረስም አታምኑም:: ስትፈፅሙት ፍቅር የሚያደረጅላችሁን ነገር ላመላከታችሁን? በመካከላችሁ ሰላምታን አብዙ::» (ሙስሊም)

225. «ተከታዮቹ ሦስት ባህሪያት ያሉት ሰው ኢማን አለው፣ ፍትሃዊነት፣ ለማንኛውም ሰው ሰላምታ ማቅረብና እጅ እያጠረው መመፅዎት::» (ቡኻሪ)

226. አብዱላህ ኢብን ዑመር (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉተ አንድ ሰው መልዕክተኛውን:- «ኢስላም ውስጥ ከመልካም ሥራ ከንውኖች በላጩ የትኛው ነው?» በማለት ጠየቃቸው:: «ትመግባለህ፣ ለምታውቀውም ሆነ ለማታውቀው

ሰላምታን ታቀርባለህ?» አሉት:: (ቡኻሪ)

## 109. ካፊር ሰላምታ በሚያቀርብበት ወቅት የሚሰጡት ምላሽ

227. «የመፅሐፉ ባለቤቶች (አህላል ኪታብ) ሰላምታ ሲያቀርቡላችሁ «ወዐለይኩም» (በናንተም ላይ) የሚል ምላሽ ስጧቸው::» (ቡኻሪ)

## 110. አውራ ዶሮ ሲጮህና አህያ ሲያናፋ የሚደረጉ ዱዓዎች

228. «የአውራ ዶሮ ጮሆት ስትሰሙ አላህን ከትሩፋቱ ጠይቁት:: መላኢካ ስላየች ነው (የጮህችው):: አህያ ሲያናፋ በምታደምጡበት ወቅት ደግሞ አላህን ከሸይጧን ይጠብቃችሁ ዘንድ ተማፀኑት:: እህያው ሸይጧን በመመልከቱ ነው (የጮሀው)» (ቡኻሪና ሙስሊም)

## 111. ውሾች በሌሊት በሚጮሁበት ወቅት የሚደረግ ዱዓ

229. «በሌሊት የውሻ ጩሆት ወይም አህያ ሲያናፋ ከሰማችሁ ከነርሱ የአላህን ጥበቃ ተማፀኑ፡፡ እናንተ የማታዩትን እነርሱ ያያሉና፡፡» (አቡዳውድ)

## 112. ለሰደቡት ሰው የሚያደርጉት ዱዓ

٢٣٠- قال ﷺ: «اللَّهُمَّ فَأَيُّمَا مُؤْمِنٍ سَبَبْتُهُ فَاجْعَلْ ذٰلِكَ لَهُ قُرْبَـةً إِلَيْكَ يَوْمَ الْقِيَامَةِ»

*«አልላሁምመ ፈአዩማ ሙእሚኒን ሰበብቱሁ ፈጅዐል ዛሊከ ለሁ ቁርበተን ኢለይከ የውመል ቂያማህ»*

230. «አላህ ሆይ! ለማንኛውም ለሰደብኩት ሙእሚን ስድቤን የቂያማ ዕለት ወደአንተ መቃረቢያ አድርግለት፡፡»
(ቡኻሪና ሙስሊም)

## 113. ሙስሊም ሙስሊምን በሚያወድስበት ወቅት ማለት ያለበት

231. የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)

እንዲህ ብለዋል:-
«ከናንተ አንዳችሁ ባልደረባውን ማሞገስ ካለበት፥እገሌ እንዲህ ነው ብዬ እስባለሁ:: እውነተኛ ማንነቱን የሚያውቀው አላህ ነው:: ስለማንም መልካምነት ከአላህ ዘንድ ምስክርነት አልሰጥም:: እንዲህ እንዲህ ነው ብዬ ግን እስባለሁ» ይበል:: (ሙስሊም)

## 114. አንድ ሙስሊም ሲወደስ ማለት ያለበት

٢٣٢- «اللَّهُمَّ لَا تُؤَاخِذْنِي بِمَا يَقُولُونَ، وَاغْفِرْ لِي مَا لَا يَعْلَمُونَ [وَاجْعَلْنِي خَيْراً مِمَّا يَظُنُّونَ]»

232. «አላህ ሆይ! እነሱ በሚሉት አትያዘኝ፤የማያውቁትን (ሐጢአቴን) ማርልኝ:: እነርሱ ከሚገምቱኝ በላይ አድርገኝ::» (ቡኻሪ)

**115. ከሐጅ ወይም ዑምረህ ሥርዓት ውስጥ ያለ ሰው የሚያሰማው ዚክር (ተልቢያ)**

٢٣٣- «لَبَّيْكَ اللَّهُمَّ لَبَّيْكَ، لَا شَرِيكَ لَكَ لَبَّيْكَ، إِنَّ الْحَمْدَ، وَالنِّعْمَةَ، لَكَ وَالْمُلْكَ، لَا شَرِيكَ لَكَ»

«ለብበይክ አልላሁምመ ለብበይክ፣ ላሸሪከ ለከ ለብበይክ፣ ኢንነል ሐምደ፣ ወንኒዕመተ፣ ለከ ወልሙልክ፣ ላሸሪከለክ»

233. «አቤቱ አላህ ሆይ! አቤቱ ጥሪህን ተቀብዬ እዚህ ተገኝቻለሁ:: አላህ ሆይ! አቤቱ ጥሪህን ተቀብዬ እዚህ ተገኝቻለሁ:: አቤቱ አጋር የለህም:: ምስጋና፣ ግርማዊነትም፣ ንግሥናም ለአንተ የተገባ ነው:: አጋር የለህም::»

(ቡኻሪና ሙስሊም)

**116.«ሩክነል አስወድ» ሳይ ሲደርሱ የሚሉት ዚክር**

234. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የአላህን ቤት ጉበኙ:: ግመል ላይ ሆነው:: «ሩክነል አስወድ» ላይ ሲደርሱ ወደርሱ በአንዳች ነገር በማመላከት «አላሁ አክበር»አሉ:: (ቡኻሪ)

**117. በ«ሩክነል የማኒ»ና በ«ሐጀርል አስወድ» መካከል የሚደረግ ዱዓ**

٢٣٥- « رَبَّنَآ ءَاتِنَا فِى ٱلدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِى ٱلْأَخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ »

*«ረብበና አቲና ፊድዱንያ ሐሰነተን ወፊል አኺረቲ ሐሰነተን ወቂና ዐዛበንናር»*

235. «ጌታችን ሆይ! በዚህች ዓለም መልካምን፣ በቀጣዩ ዓለምም መልካም ነገር ለግሠን:: ከእሳት ቅጣ ትም ጠብቀን::» (አቡዳውድና አህመድ)

**118. ሶፋና መርዋህ ላይ ሲቆሙ የሚያደርጉት ዱዓ**

236. ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) ወደ ሶፋ ሲቀርቡ :-

﴿ ۞ إِنَّ ٱلصَّفَا وَٱلْمَرْوَةَ مِن شَعَآئِرِ ٱللَّهِ ﴾

«ኢንነስሶፋ ወልመርወተ ሚን ሸዐኢሪላህ»

«ሶፋና መርዋህ የአላህ አምልኮ መፈፀሚያዎች ናቸው፤ አላህ በጀመረበት እጀምራለሁ።» ይሉ ነበር።

እናም በሶፋህ ይጀምራሉ። የአላህ ቤት እስኪታያቸው ድረስ ሶፋ ላይ ይዘልቃሉ። ከዚያም ወደ ቂብላ አቅጣጫ በመዞር የአላህን አንድነት ይመሰክራሉ። ልዕልናውን ይናዘዛሉ። እንዲህ ይላሉም፡-

«لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ وحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ، لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ، أَنْجَزَ وَعْدَهُ، وَنَصَرَ عَبْدَهُ، وهَزَمَ الْأَحْزَابَ وَحْدَهُ،

«ላኢላሃ ኢለልሏህ ዋህደሁ ላሸሪከለሁ፣ ለሁል

ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር፤ ላኢላሃ ኢልለላሁ ዋሀደሁ፤ አንጀዘ ዋዕደሁ፤ ወነሰረ ዐብዳሁ፤ ወሐዘመል አሁዛበ ዋሁዳሁ»

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አንድ ነው:: አጋር የለውም:: ንግስና ለርሱ የተገባ ነው:: ምስጋናም ለርሱ የተገባ ነው:: እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው:: ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አንድ ነው:: ቃልኪዳኑን ሞልቷል:: ባሪያውን ረድቷል:: (የጠላትን) ኃይል ብቻውን አንኮታኩቷል::»

ከዚያም ዱዓ ያደርጋሉ:: ይህንኑ ሦስት ጊዜ ይደጋግማሉ:: ሰፋ ላይ የፈፀሙትን መርዋም ላይ ይደግሙታል::

## 119. በዐረፋ ቀን የሚደረግ ዱዓ

237. «ከዱዓዎች ሁሉ በላጩ የዐረፋህ ዕለት የሚደረግ ዱዓ ነው:: እኔና ከኔ በፊት የነበሩ ነብያት ከተናገሯቸው ሁሉ በላጩ :-

لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ"

*«ለኢላሃ ኢልለላሁ ዋህደሁ ላሸሪክ ለሁ ፣ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። አንድ ነው። አጋር የለውም። ንግሥና የርሱ ብቻ ነው። ምስጋናም ተገቢነቱ የርሱ ነው።» (ቲርሙዚይ)

## 120. የ«መሽዐረል ሐራም» ዕለት የሚባል ዚክር

238. «ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ግመል ላይ ሆነው መሽዐረል ሐራም ደረሱ። ወደ ቂብላ በመዞርም ዱዓ አደረጉ። «አላሁ አክበር»፣ «ላኢላሃ ኢለላህ» አሉ። የአላህን አንድነት መሰከሩ። እስኪነጋ ድረስ እዚያው ቆመው ቆዩ። ፀሐይ ከመውጣቷ በፊትም ተንቀሳቀሱ።

## 121. በጥንጫ ውርወራ ሥርዓት ወቅት «ተክቢራ» ማድረግ

239. «እያንዳንዱን ጭንጫ በሚጠረ ውሩበት ወቅት «አላሁ አክበር» ይበሉ።

በሦስቱም የውርወራ ሥርዓቶች:: ከዚያም ወደፊት ይንቀሳቀሱ:: ቆም በማለትም ፊትዎን ወደ ቂብላ አዙረው ዱዓ ያድር ጉ:: እጅዎን ወደ ላይ በማንሳት በመጀመ ሪያውና በሁለተኛው የውርወራ ሥርዓ ት:: የመጨረሻውን የውርወራ ሥርዓት ሲፈፅሙ እያንደንዱን ጭንጫ ሲወረውሩ «አላህ አክበር» ይበሉ:: ግና እንዳጠናቀቁ መቆም የለብዎትም:: ወዲያውኑ ዞወር ይበሉ::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

## 122. አንድ የሚያስደንቅ ወይም የሚያስደስት ነገር ሲገጥምዎ

٢٤٠- «سُبْحَانَ اللهِ!» «ሱብሀነሏህ»

240. «ለአላህ ጥራት ይገባው!::»
(ቡኻሪና ሙስሊም)

٢٤١- «اللهُ أَكْبَرُ» «አልሏሁ አክበር»

241. «አላህ ከሁሉም የላቀ ነው»
(ቡኻሪ)

## 123. አስደሳች ዜና የሰማ ሰው የሚፈፅመው

242. «ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) አስደሳች ዜና በሚደ ርሳቸው ወቅት አላህን ለማመስገን ሱጅድ ያደረጉ ነበር።» (አህለሱነን- ከነሳኢይ ውጭ)

## 124. ከአካሉ ላይ ህመም የተሰማው ሰው የሚለው

243. «እጅዎን ህመሙ ከሚሰማዎ የአካል ክፍልዎ ላይ በማስቀመጥ ሦስት ጊዜ :-

بِسْمِ اللهِ،

*«ቢስሚልላህ»*

«በአላህ ስም» ይበሉ። ሰባት ጊዜ ደግሞ :-

أَعُوذُ بِاللهِ وَقُدْرَتِهِ مِنْ شَرِّ مَا أَجِدُ وَأُحَاذِرُ»

*«አዑዙ ቢልላሂ ወቁድረቲሂ ሚንሸርሪ ማአጂዱ ወኡሀዚሩ»*

«ካገኘኝና ወደፊት እንዳያገኘኝ ከምፈራው መጥፎ ነገር በአላህና በችሎታው እጠበቃለሁ» ይበሉ:: (ሙስሊም)

## 125. በዓይኑ ጉዳት እንዳያደርስ የሰጋ ሰው የሚያሰማው ዱዓ

245. «ከናንተ አንዳችሁ ከወንድሙ፣ ከራሱ ወይም ከገንዘቡ የሚያስደንቀው ነገር ሲገጥመው አላህ ረድኤቱን ያሰፍንለት ዘንድ ዱዓ ያድርግ:: ዓይነ ጥላ (የሰውዓይን) እውነት ነው::»

(አህመድ፣ኢብን ማጀህና ማሊክ)

## 126. በድንጋጤ ወቅት የሚባል ዚክር

«لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللَّهُ» -٢٤٥

«ላኢላሃ ኢልለሏህ»

245. «ከአላህ ውጭሌላ አምላክ የለም!::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

## 127. እንስሳትን በሚያርዱበት ወቅት ማለት ያለብዎ

٢٤٦- «بِسْمِ اللهِ وَاللهُ أَكْبَرُ [اللَّهُمَّ مِنْكَ وَلَكَ] اللَّهُمَّ تَقَبَّلْ مِنِّي»

*«ቢስሚላሂ ወላሁ አክበር! አልላሁም ሚንክ ወለክ! አሏሁመ ተቀበል ሚንኒ»*

246. «በአላህ ስም:: አላህ ከሁሉም የላቀ ነው:: አላህ ሆይ! ካንተ (የተሰጠንን) ላንተው (ሰውተናል):: አላህ ሆይ! ተቀበለኝ::» (ሙስሊምና በይሐቅይ)

## 128. የሸይጧንን ተንኮል ለመመከት የሚደረግ ዱዓ

٢٤٧- «أَعُوذُ بِكَلِمَاتِ اللهِ التَّامَّاتِ الَّتِي لَا يُجَاوِزُهُنَّ بَرٌّ وَلَا فَاجِرٌ مِنْ شَرِّ مَا خَلَقَ، وَبَرَأَ وَذَرَأَ، وَمِنْ شَرِّ مَا يَنْزِلُ

مِنَ السَّمَاءِ، وَمِنْ شَرِّ مَا يَعْرُجُ فِيهَا، وَمِنْ شَرِّ مَا ذَرَأَ فِي الْأَرْضِ، وَمِنْ شَرِّ مَا يَخْرُجُ مِنْهَا، وَمِنْ شَرِّ فِتَنِ اللَّيْلِ وَالنَّهَارِ، وَمِنْ شَرِّ كُلِّ طَارِقٍ إِلَّا طَارِقاً يَطْرُقُ بِخَيْرٍ يَارَحْمٰنُ»

*«አዑዙ ቢከሊማቲልላሂ ታማቲ ለቲ ላ ዩጃዊዙሁንነ በሩን ወላ ፋጂሩን ሚንሸርሪ ማኸለቅ፣ ወበረአ ወዘረአ፣ ወሚንሸርሪ ማየንዚሉ ሚነሰሰማኢ፣ ወሚንሸርሪ ማየዕሩጁ ፊሃ፣ መሚንሸርሪ መዘረአ ፊል አርድ፣ ወሚንሸርሪ ማየኽሩጁ ሚንሐ፣ ወሚንሸርሪ ፊተኒ ለይሊ ወንነሐር፣ ወሚንሸርሪ ኩሊ ጧሪቂን ኢላ ጧሪቀን የጥሩቁ ቡኸይሪን ያረሀማን»*

247. «ጽድቅም ይሁን አመፀኛ በማያልፋቸው ምሉዕ የሆኑ የአላህ ቃላት ከፍጡራኑ፣ ተንኮል፣ ከሰማይ ከሚወርድ፣ ወደሰማይ ከሚወጣ፣ መሬት ላይ ከበቀለ፣ ከርሷ ከሚወጣ ተንኮል፣ ከሌሊትና ከቀን ተንኮል፣ ከሚከሰት ነገር ሁሉ፥ በመልካም ካልሆነ በቀር፥ እጠበቃለሁ።

አዛኝ የሆንከው (አምላክ) ሆይ! ይህንን እማፀንሀለሁ::» (አህመድ)

## 129. አላህን ምህረት መማፀን (ኢስቲግፋር) እና በፀፀት ወደርሱ መመለስ (ተውባህ)

248. የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«በአላህ ይሁንብኝ! እኔ በየቀኑ ከሰባ ጊዜ በላይ አላህን ምህረት እማፀናለሁ:: ወደርሱም ተውባ አደር ጋለሁ::» (ቡኻሪ)

249. ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«እናንተ ሰዎች ሆይ! ወደ አላህ በፀፀት ተመለሱ:: እኔ በየቀኑ ከመቶ ጊዜ ያላነሰ ተውበት አደር ጋለሁ::» (ሙስሊም)

250. መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዩን ተናግረዋል:-

أَسْتَغْفِرُ اللهَ الْعَظِيمَ الَّذِي لَا إِلَـٰهَ إِلَّا هُوَ الْحَيُّ الْقَيُّومُ وَأَتُوبُ إِلَيْهِ،

*«አስተግፍሩላህ አልዐዚም አለዚ ላኢላሀ ኢላ ሁወል ሐዩል ቀዩም ወአቱቡ ኢለይሀ»*

«ከርሱ ውጭ ሌላ አምላክ የሌለ ህያውና ራሱን ቻይ የሆነውን አላህን ምህረት እለምነዋለሁ፤ ወደር ሱም ተውበት አደርጋለሁ» ያለ+ ወንጀሉን ይምርለታል - ከውጊያ መሐል የመሸሸት (ጥፋት) ቢፈፅም እንኳ:: (አቡ ዳውድና ቲርሙዝይ)

251. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«አላህ ለባሪያው ይበልጥ ቅርብ የሚሆነው ከመጨረሻው የሌሊቱ ክፍል ላይ ነው:: በዚያ ወቅት አላህን ከሚያወሱት ለመሆን ከቻልክ ሁን::»

(ቲርሙዝይ፣ነሳእይና አህመድ)

252. የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«ሰውየው ለአላህ ይበልጥ ቅርብ የሚሆነው ሱጁድ ላይ ነው:: (ሱጁድ ላይ) ዱዓ አብዙ::» (ሙስሊም)

253. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ስለ ተናግረዋል:-

«በቀን መቶ ጊዜ አላህን ምህረት የመለመን ፍላጎት ልቦናዬ ውስጥ ያድራል።» (ሙስሊም)

## 130.የ«ተስቢሕ»፣ «ተሕሚድ»፣ «ተህሊል» እና «ተክቢር» ትሩፋቶች

254. የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«በቀን መቶ ጊዜ «*ሱብሐነላህ ወቢሐምዲሂ*» (ለአላህ ምስጋናና ጥራት ይገባው።) ያለ ሐጢአቱ የባህር አረፋ ያክል እንኳ ቢሆን ይታበስለታል።» (ቡኻሪና ሙስሊም)

255. ነቢዩ(ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

٢٥٥- لَا إِلَٰهَ

إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ، وَلَهُ الْحَمْدُ، وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ

*«ላኢላሀ ኢልለሏላ ዋህደሁ ላሸሪከለሁ፣ ለሁል ሙልኩ፣ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። አንድ ነው። አጋር የለውም። ንግሥና የርሱ ብቻ ነው። ምስጋናም ተገቢነቱ ለርሱ ነው። እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው» የሚለውን አሥር ጊዜ ያለ ከኢስማኤል ልጆች አራት ያህሉን ነፃ እንዳወጣ ይቆጠርለታል። (ቡኻሪና ሙስሊም)

**256.** ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«ሁለት ንግግሮች አሉ። ምላስ ላይ ቀላሎች፣ ሚዛን ላይ ደግሞ ከባዶች ናቸው። ከአላህ ዘንድም ተወዳጅነት አላቸው። (እነሱም):-

سُبْحَانَ اللهِ وَبِحَمْدِهِ سُبْحَانَ اللهِ الْعَظِيمِ »

*«ሱብሃነላህ ወቢሐምዲሂ ሱብሐነላህ ለዐዚም»*

«ለአላህ ጥራትና ምስጋና ይገባው። ለታላቁ አላህ ጥራት ይገባው» የሚሉት ናቸው።» (ቡኻሪና ሙስሊም)

257. የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

سُبْحَانَ اللهِ، وَالْحَمْدُ لِلَّٰهِ، وَلَا إِلَٰهَ إِلَّا اللهُ، وَاللهُ أَكْبَرُ،

*«ሱብሃነላህ! ወልሐምዱ ሊላህ! ወላኢላሃ ኢልለሏህ ወላሁ አክበር»*

«ለአላህ ጥራት ይገባው:: ምስጋናም ለአላህ ተገቢው ነው:: ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም:: አላህ ከሁሉም የላቀ ነው» በማለት (አላህን ማወደስ) ፀሐይ ከምትወጣበት (ቦታና ሃብት) ሁሉ ይበልጥ ከኔ ዘንድ ተወዳጅ ነው:: (ሙስሊም)

258. መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) :- «ከናንተ አንዳችሁ በየቀኑ አንድ ሺህ የመልካም ሥራ ምንዳ (ሐሰና) ማግኘት ይሳነዋልን?» በማለት ጠየቁ:: ከታዳሚ ዎች አንዱ :- «እንዴት በየቀኑ አንድ ሺህ ምንዳዎችን ማግኘት ይቻላል?» በማለት ጠየቀ:: «መቶ ተስቢሕ» ያድርግ:: አንድ ሺህ ምንዳ ይጻፍለታል:: ወይንም አንድ ሺህ ሐጢአቶች ይታበሱለታል::» አሉ::

٣ سُبْحَانَ اللهِ الْعَظِيمِ وَبِحَمْدِهِ!!

*«ሱብሃነላሂ ኣልዐዚም ወቢ ሃምዲሂ»*

259. «ታላቅ ለሆነው አላህ ጥራትና ምስጋና ይገባው፥ ያለ ጀንነት ውስጥ አንድ የተምር ዛፍ ይተከልለታል።»

(ቲርሙዝይና ሐኪም)

260. መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) :-

«ዓብደላህ ኢብን ቀይስ ሆይ! ከጀንነት ድልቦች አንዱን ልጠቁምህን?» አሉ። «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አዎ (ይጠቁሙኝ) አላቸው።

«لاَ حَوْلَ وَلاَ قُوَّةَ إِلاَّ بِاللهِ»

*«ላሐውላ ወላ ቀውወተ ኢልላ ቢላህ»*

«ብልሐትም ኃይልም በአላህ ቢሆን እንጅ የለም» በል አሉ። (ቡኻሪና ሙስሊም)

261. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«ከአላህ ዘንድ ተወዳጅ የሆኑ ንግግሮች አራት ናቸው፤ *ሱብሐነላህ፣ ወልሐምዱ ሊላህ፣ ወላ ኢላሃ ኢለላህ፣ ወላሁ አክበር።* በየትኛውም ብትጀምር ልዩነት የለውም።» (ሙስሊም)

262. አንድ በደዊን ከመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ በመምጣት ፦ «ዘወትር የምላቸውን ቃላት ያስትምሩኝ» አላቸው፡፡

« لَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، اللهُ أَكْبَرُ كَبِيراً، وَالْحَمْدُ لِلَّـٰهِ كَثِيراً، سُبْحَانَ اللهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ، لَا حَوْلَ ولَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللهِ الْعَزِيزِ الْحَكِيمِ »

*«ላኢላሃ ኢልለኋሁ ዋህደሁ ላሸሪከ ለሁ አልኋሁ አክበር ከቢራ፣ ወልሃምዱሊላሂ ከሢራ፣ ሱብሃነላሂ ረብቢል ዐለሚን፣ ላሃውላ ወላ ቁወተ ኢልላ ቢልላሂል ዓዚዚል ሐኪም»*

«ከአላህ ውጭ ሌላ አምላክ የለም፡፡ አንድ ነው፡፡ አጋር የለውም፡፡ አላህ ከሁሉም የላቀ ነው፡፡ ለአላህ ምስጋና በብዙው ይገባዋል፡፡ የዓለማት ጌታ ሆይ! ጥራት ይገባህ፡፡ ብልሐትም ኃይልም የለም፤ ሐያልና ጥበበኛ በሆነው አላህ ቢሆን እንጅ፤ በል» አሉት፡፡

«እነኝህ ለአምላኬ ናቸው:: ለኔስ?» ሲል ጠየቃቸው::

« اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي، وَارْحَمْنِي، وَاهْدِنِي، وَارْزُقْنِي»

*«አልላሁምመ ኢግፊርሊ ወርሐምኒ ወሀዲኒ ወርዘቅኒ»*

አላህ ሆይ! ምህረትህን ለግሰኝ:: እዘንልኝ:: ምራኝ:: ሲሳይን ለግሰኝ ፥ በል» አሉት:: (ሙስሊም)

263. አንድ ሰው ኢስላምን በሚቀበልበት ወቅት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሶላትን ያስትምሩታል:: በተከታዮቹ አባባሎች አላህን እንዲማፀንም ይነግሩታል:-

«اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي، وَارْحَمْنِي، وَاهْدِنِي وَعَافِنِي وَارْزُقْنِي»

*«አልላሁምመ ኢግፊርሊ ወርሐምኒ ወሀዲኒ ወዐፊኒ ወርዘቅኒ»*

«አላህ ሆይ! ምህረትህን ለግሰኝ::

እዘንልኝ:: ቀጥተኛውን መንገድ ምራኝ:: ጤናማ አድርገኝ:: ሲሳይንም ለግስ ኝ::» (ሙስሊም)

264. «ከዱዓዎች ሁሉ በላጩ «አልሐምዱ ሊላህ» ሲሆን፥ ከዚክሮች ሁሉ በላጩ ደግሞ:- «ላኢላሃ ኢለላህ» ነው:: (ቲርሙዝይ፣ ኢብን ማጃህና ሐኪም)

265. (ተከታዮቹ ዚክሮች) የመጭው ዓለም ድልቦች (ናቸው)፣

«سُبْحَانَ اللهِ، وَالْحَمْدُ لِلَّـٰهِ، وَلَا إِلَـٰهَ إِلَّا اللهُ، وَاللهُ أَكْبَرُ، وَلَا حَوْلَ وَلَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللهِ»

«ሱብሐነላህ፣ ወልሐምዱ ሊላህ፣ ወላኢላህ ኢለላህ፣ ወላሁ አክበር፣ ወላሀውለ ወላቁወተ ኢላ ቢላህ» (አህመድ)

## 131. የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የተስቢሕ አደራረግ ስልት

266. አብደላህ ኢብን ዐመር እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

«ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተስቢሕን በቀኝ (እጃቸው) ሲቆጥሩ አይቻለሁ::» (አቡዳውድና ቲርሙዝይ)

## 132. አጠቃላይ የሆነ ሥርዓት

267. «ምሽት (መግሪብ ወቅት) ላይ ልጆቻችሁን ወደቤት ውስጥ አስገቡ:: ወደ ውጭ እንዳይወጡ ከልክሏቸው:: ሸይጧን በዚያ ወቅት ይሰራጫልና:: ይህ ወቅት ካለፈ በኋላ ግን ቢንቀሳቀሱ ችግር የለ ውም:: በራፎቻችሁንም ዝጉ:: የአላህን ስም አውሱ:: ሸይጧን የተዘጋን በር አይከፍትም:: የውሃ ቀርበታችሁን ክደኑ:: የአላህን ስም አውሱ:: እቃዎቻችሁን ክደኑ:: የአላህንም ስም አውሱ:: የምትከድኑበት ባታገኙ እንኳ አንዳች ነገር ከላዩ ላይ አስቀምጡ:: የተቀጣጠሉ ኩራዞቻችሁን አጥፉ::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

وَصَلَّى اللهُ وَسَلَّمَ وَبَارَكَ عَلَى نَبِيِّنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَى آلِهِ وَأَصْحَابِهِ أَجْمَعِينَ.

አላህ በነብዩ ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቹ ላይ ረድኤቱን ያስፍን:: ረድኤቱን ይለግስ::

ተፈፀመ

ح سعيد بن علي بن وهف القحطاني ، ١٤٢٠ هـ

فهرسة مكتبة الملك فهد الوطنية أثناء النشر

القحطاني ، سعيد بن علي بن وهف

حصن المسلم. ـ الرياض

٢٣٢ ص ؛ ٨,٥ × ١٢ سم

ردمك : ٠-٢٩٤-٣٦-٩٩٦٠

(باللغة الأمهرية)

١ ـ الأدعية والأوراد　٢ ـ القرآن ـ أدعية　أ ـ العنوان

ديوي ٢١٢,٩٣　٢٠/٢١٤٧

رقم الإيداع : ٢٠/٢١٤٧

ردمك : ٠-٢٩٤-٣٦-٩٩٦٠

الطبعة الأولى : ١٤٢٠هـ - ٢٠٠٠م

حقوق الطبع محفوظة

إلا لمن أراد طبعه وتوزيعه مجاناً، بدون حذف أو إضافة أو تغيير، فله ذلك وجزاه الله خيراً . . .

مطابع الحميضي ت 4581000 ف 4592217 الرياض

# حصن المسلم

## من أذكار الكتاب والسنة


الفقير إلى الله تعالى

سعيد بن علي بن وهف القحطاني



مراجعة : عبد الله خضر بن أحمد

جامعة الإمام محمد بن سعود الإسلامية

( د. عليا - الرياض )